# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 145 ጥር 25 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር




በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አልሸባብን የመዋጋት ዘመቻን ለማጠናከር በተካሄደው ቀጣናዊ መድረክ ተሳተፉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በምሥራቅ አፍሪካ አልሸባብን የመዋጋት ዘመቻን ለማጠናከር በተካሄደው ቀጣናዊ መድረክ ላይ ተሳተፉ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በምስራቅ አፍሪካ አልሸባብን የመዋጋት ዘመቻን ለማጠናከር በሶማሊያ በሚካሄደው ቀጠናዊ መድረክ ለመሳተፍ ሞቃዲሾ ሲገቡ የሀገሪቱ ባለስልጣናት አቀባበል አድርገውላቸዋል።

የመሪዎቹ ውይይት ለቀጣናዊ ችግሮች ቀጠናዊ መፍትሔ ለመስጠት ያለመ መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስታውቋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በሶማሊያ ቆይታቸው ከተለያዩ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት መሪዎች ጋር ውይይት አድርገዋል። በተለይም ከኬንያ፣ከጂቡቲና ሶማሊያ መሪዎች ጋር በሁለትዮሽና ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ መምከራቸው ታውቋል።

በሶማሊያ ከተካሄደው ቀጣናዊ የፀረ ሽብር ውይይት መድረክ ጎን ለጎን ከኬንያው ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ ጋር በመሠረተ ልማት ትብብር፣ በንግድና ኢንቨስትመንትን በማሳደግ እንዲሁም በቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ ስለሚኖር የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት መክረናል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማኅበራዊ የትስስር ገጻቸው አስፍረዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሶማሊያ በአፍሪካ ኅብረት ስር በመሆን አልሸባብን እየተዋጉ ከሚገኙ የኢትዮጵያ ወታደሮች ጋር መወያየታቸውን አስታውቀዋል።

የመሪዎቹ ውይይት ለቀጣናዊ ችግሮች ቀጣናዊ መፍትሔ ለመስጠት ያለመ መሆኑ ነው የተገለጸው። በተጨማሪም መድረኩ የአሸባሪውን አልሸባብ እንቅስቃሴ ለመግታት የቀጣናውን ሀገራት ትብብር ማጠናከርን መሠረት ያደረገ እንደሆነ ታውቋል።



የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ
Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

ሲዳማ ባንክ
Sidama Bank
Bank for All!
ባንካችን የተሟላ የባንክ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ቅድመ-ሁኔታዎችን አጠናቅቆ በቅርቡ ሥራ ለመጀመር መዘጋጀቱን ስንገልፅ በታላቅ ደስታ ነው
አድራሻ
+25146 220 4704
+251944119303
565
+251462204704
info@sidamabanksc.com
www.sidamabanksc.com
ሲዳማ ባንክ አ.ማ.
Sidama Bank S.C.
የሁሉም ባንክ!


# ስንዴን ጨምሮ አምስት ምርቶች ወደ ምርት ገበያ ሥርዓት ገቡ

**ማርቆስ በላይ**



አዲስ አበባ፡- የስንዴ ምርትን ጨምሮ ግብጦ፣ ኮረሪማ፣ ባቄላና ሩዝ ወደ ምርት ገበያ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት መግባታቸውን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ አቶ ነፃነት ተስፋዬ ትናንት እንዳስታወቁት፤ አምስት ምርቶችን በዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ ጥራት ያለው ምርት እንዲበራከትና ከምርቶቹ ተገቢው ዋጋ እንዲገኝ ይረዳል።

አሁን ላይ ወደ ዘመናዊ ግብይት ሥርዓት ከገቡት መካከል አንዱ የሆነው የስንዴ ምርት ቀድሞ በምርት ገበያ ሥርዓት ውስጥ እንደነበር ገልጸው፤ በመሐል ምርትና ምርታማነቱ እየቀነሰ በመምጣቱ ለውጪ አገር ገበያ ማቅረብ ሳይቻል ከምርት ገበያ ሥርዓት መውጣቱን ገልጸዋል።

ስንዴን ጨምሮ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

## "ከጎረቤት ሃገራት ጋር ያለውን የድንበር ችግር በቋሚነት የሚከታተል አካል ማደራጀት ያስፈልጋል"

- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ ፡- ከጎረቤት ሃገራት ጋር ያለውን የድንበር ችግርና ድንበር ተሻጋሪ ሃብቶችን በተመለከተ

"ከጎረቤት ሃገራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
Adama Steel Factory
Our Products



Tel: 0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80
0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06


## የፋይናንስ ተቋማት ሀብት 2 ነጥብ 9 ትሪሊዮን ብር መድረሱ ተገለጸ

- 71 የፋይናንስ ተቋማት በምሥረታ ሂደት ላይ ሲሆኑ
- የተበዳሪዎች ቁጥር በ 7 ነጥብ 8 በመቶ ቀንሷል



ገጽ 4



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

ዶክተር እንዳለ ኃይሌ

# ማሻሻያ አዋጁ የተቋሙን ነጻነት እና ገለልተኛነት የበለጠ የሚያጠናክር መሆኑን ቋሚ ኮሚቴው ገለጸ

**ዘላለም ግዛው**

<u>አዲስ አበባ</u>፦ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አዋጅ ቁጥር 1142/2014 ዓ.ም ረቂቅ ማሻሻያ አዋጅ የእያንዳንዱን ጉዳይ የሚመለከት፣ በየቤቱ የሚደርሰውን በደል ጭምር የሚያይ፣ የተቋሙን ነጻነትና ገለልተኛነት የበለጠ የሚያጠናክር መሆኑን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ገለጸ።

ቋሚ ኮሚቴው ትናንት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አዋጅ ቁጥር 1142/2014 ዓ.ም ረቂቅ ማሻሻያ ላይ ባካሄደው ሕዝባዊ ውይይት ረቂቅ አዋጁ መንግሥትና ዜጋውን የሚያገናኝ መሆኑ ተጠቁሟል።

አዋጁ ቢሻሻል ሁሉንም ዜጎች ተደራሽ ለመሆን ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር፣ የተቋሙን ነጻነትና ገለልተኛነት የበለጠ እንደሚያጠናክርም ዋና ዕንባ ጠባቂ ዶክተር እንዳለ ኃይሌ አመልክተዋል። ለተቋም ግንባታ አስተዋጽኦ በማድረግ ጠንካራ መንግሥት ለመመሥረት የሚደረገውን ሂደት እንደሚያግዝም ዶክተር እንዳለ ጠቁመዋል።

ማሻሻያው ቢጸድቅ ለመልካም አስተዳደርና ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው የተናገሩት ዋና እንባ ጠባቂው ለአዋጁ መሻሻል በዋናነት አምስት ጉዳዮች ምክንያት መሆናቸውን ገልፀዋል።

በማሻሻያ አዋጁ የዕንባ ጠባቂ ሹመት በውድድርና ብቃት ላይ መሠረት እንዲሆን፣ በግል ተቋማት የሚደርሱ አስተዳደራዊ በደሎችን እንዲመረምር፣ የተቋሙን ሠራተኞች ጥቅማ ጥቅም ጥያቄ መወሰን እንዲችል፣ የሚጠይቅ ሃሳብ አካትቷል።

ለተቋሙ የቀረበ አቤቱታ በአቤቱታ አቅራቢ የማይመለስ ወይንም የማይተካ ጉዳት ያደርሳል ብሎ ዋና ዕንባ ጠባቂው ካመነ ቢበዛ እስከ 30 ቀናት ማገድ የሚያስችለውን ሥልጣን የሚፈቅድ ሃሳብ እንዲካተትለትም ይጠይቃል።

‹‹ዲያስፖራዎች ወደ ሃገር እንዲገቡ ጎትጉተን ባለአራት እና ባለአስራ አንድ ሕንጻ ከገነቡ በኋላ ቦታው ለሪል እስቴት ለአልሚዎች ይሰጣል፤ አፍርሳችሁ ሂዱ የሚባልበት ሁኔታም አለ›› ሲሉ አብራርተዋል። የእግድ ሥልጣን ቢሰጥ ይህንን ሁኔታ ያገናዘበ ሥራ ለመሥራት ያስችላል። ነገር ግን የተገደበ ሊሆን እንደሚገባው እናምናለን ብለዋል።

የቅርንጫፍ ዕንባ ጠባቂ ምደባ ሹመትን መሠረት ያደረገው አሠራር ተቀይሮ የትምህርት ዝግጅት፣ ውድድርና ብቃት ላይ መሠረት ማድረግ ለአዋጁ መሻሻል በቀዳሚ ምክንያትነት ያቀረቡት ጉዳይ ነው።

ተቋሙ አቅም በፈቀደ መጠን ለኅብረተሰቡ ተደራሽ መሆን ይኖርበታል ያሉት ዋና ዕንባ ጠባቂው፤ ባለው አሠራር ተሿሚዎችን ለማንሳትም ለመመደብም በምክር ቤቱን ውሳኔ ቢቀጥልና ምክር ቤቱ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ውስጥ የሚገባ ከሆነ ጫና ሊፈጥርበት ይችላል ሲሉም ስጋታቸውን ጠቁመዋል።

ሂደቱ ግምት ውስጥ ገብቶ ውድድርና ብቃትን መሰረት ማድረግ ተገቢ መሆኑን አንስተዋል። በድንበር የተገደበውን የተቋሙንም አገልግሎት እንደሚፈታም ነው የገለጹት።

በመንግሥት አስፈጻሚ ተቋማትና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ብቻ ተወስኖ የቆየውን የተቋሙን ሥልጣንና ተግባራት በማስፋት በትላልቅ የግል ተቋማት ላይ የሚደርሱትን በደሎችን መመርመር እንዲችል ማድረግ ሌላው ለአዋጁ መሻሻል ምክንያት ነው።

የዕንባ ጠባቂዎችን እና የምርመራ ባለሙያዎችን ያለመከሰስ መብት በአዋጁ እንዲካተት የሚጠይቅ ሃሳብም አዋጁ አካትቷል። ተቋሙ ነጻና ገለልተኛ መሆኑ የሚረጋገጠው ከተጽዕኖ ነጻ ሲሆኑ ነው፤ ሁለት፣ ሦስት ጊዜ የተቋማችን ሠራተኞች የሚታሠሩበት ሁኔታ አለ፣ ከዋናው መሥሪያ ቤት ጭምር ፖሊስ ሠራተኞችን ያሰረበት ሁኔታ አለ ብለዋል።

የተቋሙን ሠራተኞች ጥቅማ ጥቅም የመወሰን ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 1142/2014 ዓ.ም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠውን ሥልጣን የነበረ ሲሆን ረቂቁ የምክር ቤቱ ስልጣን ተሻሽሎ ለዕንባ ጠባቂ ጉባኤ እንዲሰጥ የሚጠይቅ ድንጋጌም አካትቷል።

ተወያዮች እግድ የዳኝነት ሥልጣን እንደመሆኑ ለአፈጻጸም አዳጋች እንዳይሆን ለፍርድ ቤት ሊተው እንደሚገባ አመልክተዋል። የግል ተቋማት ተብሎ የተቀመጠው ጥቅል በመሆኑና ለተቋሙ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ሰፍተው ከተቋሙ አቅም እንዳይበልጡና በአሠራር ላይ ጫና እንዳይፈጥሩ ገደብ ቢበጅ የሚሉና መሰል ምክረ ሃሳቦችና ጥያቄዎች ቀርበዋል።

ያለመከሰስ መብትን አስመልክቶ የቀረበው የሕግ ማሻሻያ ሃሳብ ያለግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል በጥንቃቄ መታየት እንዳለበትም ነው የተመለከተው።

# “ሰላምን ማስፈንና ሕግን የማስከበር ተግባራት ተጣጥመው መሄድ ይኖርባቸዋል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

**መዓዛ ማሞ**



<u>አዲስ አበባ</u>፡ ሰላምን በሚመለከት ማስተማር እና ሕግ ማስከበር ተጣጥመው መሄድ እንዳለባቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት በሰላም እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በሰጡት ማብራሪያ ላይ እንደገለጹት ሰላም በሕግ የሚከበር ነው። ሰላም በችሮታ እና በፍቃድ የሚረጋገጥ ቢሆን ሕግም ፖሊስም እንደማያስፈልግ ጠቁመው ሰላምን በሚመለከት ለአብዛኛው ሰው የአመለካከት ግንባታ የሚያስፈልግ ሲሆን ከዚያ ወጣ ላለው ደግሞ ሕግ አስከባሪ እና ሕግ አስፈላጊ በመሆኑ ማስተማሩ እና ሕግ ማስከበሩ ተጣጥመው መሄድ እንዳለባቸው ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ሰላም ያለው ህሳቤ ትንሽ ችግር እንዳለበት የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አጀንዳ በመፍጠር ሰው እንዲገዳደል በማድረግ እና በማኅበራዊ ሚዲያ ይህንን በማራገብ መንግሥትን እንጥላለን፤ እናዳክማለን የሚሉ ሰዎች እንደሚጠቀሙበት ጠቁመዋል። የፖለቲካ ገበያው መበላሸት እምነትን፣ ዘርንና ሰፈርን መጠቀሚያ አድርጎ በንጹሐን ሰዎች ደም ወደ ሥልጣን ለመምጣት መፈለግ እንደሆነም ተናግረዋል።

በከተማ ውስጥ ግርግር እና ብልጽግና ውስጥ ሁለት ሦስት ሰው በመቅጠር መንግሥትን ማፍረስ አይቻልም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መንግሥት ሥራ እንዳይሠራ በየቦታው አጀንዳ መፍጠር እና ማገዳደል የማያዋጣ በመሆኑ ሃገር ከማፍረስ እና የንጹሐንን ደም ከማፍሰስ መጠበቅ እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል።

በመንግሥት በኩል ሕዝብን የማወያየት ሥራዎች እንደሚሠሩ እና ያሉ እውነታዎች እና ግዴታዎችን ለሕዝብ እንደሚገለጹ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአሠራር መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች ካሉ እንደሚስተካከሉ፤በቅጥርና በሹመት የሚነሱ ጉዳዮች ካሉ ሕግ በማውጣት ሁሉም ሰው እኩል የሚጠቀምባቸው ሥርዓቶች እንደሚገነቡም ገልጸዋል።

የሚዲያ ተቋማት በኃላፊነት እና በሕግ አግባብ መሥራት መቻላቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ እንደሆነ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ሕዝብን ከሕዝብ፣ ዕምነትን ከዕምነት ማባላት የሚፈቀድ እንዳልሆነ ጠቁመዋል። ይህንን የሚያደርጉ ሚዲያዎችን በሚመለከትም መንግሥት በመጀመሪያ በማስተማር፣ በመምከር እና በመገሰጽ እንዲሁም በሕግ አግባብ እንደሚጠይቅም ተናግረዋል።

በጠብመንጃ ኃይል ፍላጎት ማሳካት እንደማይቻል የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተደጋጋሚ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከአንዳንድ አካላት ጋር በመቀናጀት ግድያ ለመፈጸም የሚንቀሳቀሱ አካላት መኖራቸውን ጠቁመው እየታደኑ እንደሚያዙ ጠቁመዋል። የሰላምን ዋጋ በእጅጉ በመገንዘብ ለሰላም የማይሠራ ከሆነ ውጤቱ መጠፋፋት እንደሆነም ገልጸዋል።

በሕግ አግባብ ሰዎች የሚጠየቁበትን እና ሕግ የሚከበርበትን መንገድ መከተል እንደሚያስፈልግ የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በመደማመጥ እና በመከባበር በጋራ መኖር አስፈላጊ እንደሆነም አስረድተዋል።

አቅም በፈቀደ መልኩ መንግሥት ለሁሉም እኩል እንደሚያገለግል ገልጸው ሁሉም ቡድን ይህንን በመገንዘብ ተጋግዞ እና ተደጋግፎ መሄድ እንዳለበት ጠቁመዋል። ለንግግር በመዘጋጀት፤ ለይቅርታም ልባችንን በመክፈት የተጀመረውን አብሮ መሥራት እና ዲሞክራሲን ማስፋፋት እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል።

# የወባ ወረርሽኝ ስርጭትን ለመግታት 10 ሚሊዮን አጎበር ተሰራጭቷል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ስርጭቱ እየተስፋፋ የመጣውን የወባ ወረርሽኝ ለመቆጣጠር 10 ሚሊዮን አጎበር ለተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መሰራጨቱን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጤና፣ ማኅበራዊ፣ ባሕልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የጤና ሚኒስቴርን የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ገምግሟል።

በወቅቱ የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ እንደተናገሩት፤ የወባ በሽታን ለመግታት 10 ሚሊዮን አጎበሮች ወረርሽኙ በተስፋፋባቸው ሰባት ክልሎች እንዲሰራጭ ተደርጓል። በሰባቱ ክልሎች የሚገኙ 263 ወረዳዎች የወባ መከላከያ አጎበር ዘጠኝ ሚሊዮን ለሚደርሱ አባወራና እማዎራዎች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ለ6 ነጥብ 3 ሚሊየን ለሚሆኑ የወባ ምልክት ለታየባቸው ግለሰቦች ፈጣን የላብራቶሪ ምርመራ መደረጉን ሚኒስትሯ ገልጸዋል። ምርመራ ከተደረገላቸው ሰዎች ውስጥም 1 ነጥብ 3 ሚሊየን ያህሉ የወባ በሽታ ሕክምና የተሰጣቸው መሆኑንም አስታውቀዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት 22 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ የሕክምና ቁሳቁሶች በግዥና በዕርዳታ መልክ ወደ ሀገር ውስጥ ገብተዋል፡፡ አብዛኛው የሕክምና ግብዓት የሚገባው ከውጭ ሀገራት ነው። እንደ ሚኒስትሯ ገለፃ፤ ከአጠቃላዩ 5 ነጥብ 7 በመቶው ብቻ ከሀገር ውስጥ ተገዝቷል ብለዋል።

በስድስት ወራት ውስጥ 12 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር የሚገመቱ ጤና ነክ ቁሳቁሶች በዕርዳታ መልክ ገብቷል ያሉት ዶክተር ሊያ አንድ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር የሚያወጡ የሕክምና ቁሳቁሶች ከማዕከል ወደ ተለያዩ ክልሎች ተሰራጭተዋል።

በጤና ተቋማት ላይ የሚሰጡት አገልግሎቶች የጥራት ደረጃቸውን እንዲጠብቅ የማድረግ ሥራ በሰፊው እየተከናወነ ይገኛል።

ከሰላም ስምምነቱ በኋላ በተለይ በሽሬ፣አድዋና አክሱም እንዲሁም አላማጣና ኮረም አካባቢዎች ለሕክምና የሚያስፈልጉ ግብዓቶችና ባለሙያዎችን በመላክ ሰፊ ሥራ መከናወኑን ተናግረዋል።

በነበረው ጦርነት ምክንያት ጉዳት፤ በትግራይ፣ አማራና አፋር ክልሎች የሚገኙ የጤና ተቋማት ወደ ሥራ እንዲገቡ አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጓል፤ በዚህም አገልግሎት መስጠት የጀመሩ የሕክምና ተቋምት በርካታ ናቸው ሲሉ አስረድተዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘም የጤና ተቋማቱን ድጋፍ በዘላቂነት ለማጠናከር የሚረዳ ጥናት ተዘጋጅቶ በገንዘብ ሚኒስቴር የሚመራ ፕሮጀክት መነደፉን ጠቁመዋል። በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የነፃ ሕክምና በሰፊው ተከናውኗል። በዚህም አንድ ሚሊዮን ሰዎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል ነው ያሉት፡፡ የወጣቶችና ጨቅላ ሕጻናትን ጤና ከማሻሻል አንፃር አገልግሎቱ 70 በመቶ መድረሱን አስታውቀዋል።

ከአጋር አካላት የሚመጡ በጀቶች መዘግየት፤ በተፈለገው ልክ የሕክምና አገልግሎት እንዳይሰጥ አድርጓል ያሉት ዶክተር ሊያ፤ የነፃ ሕክምና አገልግሎቶች ወጪ ማን እንደሚሸፍነው ግልጽ አለመሆን ችግር መሆኑን ገልጸዋል።

የውጪ ምንዛሪ እጥረት እንደ ሀገር የጤና ዘርፉ አፈጻጸም ይበልጥ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጓል ሲሉ አስረድተዋል።

ዜና

# መንግስት ስጤና መድህን 1 ቢሊዮን ብር ድጎማ በማድረጉ 9 ሚሊዮን ሰዎች ተጠቃሚ ሆነዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት አንድ ቢሊዮን ብር ድጎማ በማድረጉ 9 ሚሊዮን የሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች የጤና መድሕን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ጤና መድሕን አገልግሎት አስታወቀ። ከጤና መድሕን አገልግሎት ምዝገባና እድሳት 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ገቢ ተገኝቷል፡፡።

የኢትዮጵያ ጤና መድሕን አገልግሎት የኮሙኒኬሽን ክፍል ኃላፊ አቶ ዘመድኩን አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ በመንግሥት የድጎማ በጀት የጤና መድሕን አገልግሎቱ በ916 ወረዳዎች ላይ ለሚገኙ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰዎች ተሰጥቷል።

የጤና መድሕን አገልግሎቱ ዜጎች የኢኮኖሚ አቅማቸው አስቻይ ባልሆነበት ሁኔታ አስፈላጊውን የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚረዳ ነው። በተጨማሪ መንግሥት በጀት በማዘጋጀት የጤና መድሕን ክፍያን መክፈል ለማይችሉ የሕክምና ወጪያቸውን ይሸፍናል ሲሉ አስረድተዋል።

በአገልግሎቱ በየጊዜው የተለያዩ ተግዳሮቶች እንደሚያጋጥሙ ያነሱት ኃላፊው በተለይም ድርቅና ሰው ሰራሽ አደጋ በሚከሰትባቸው አካባቢዎች ላይ የጤና መድሕን አገልግሎቱን ለማስፋት እክል እንደሚፈጠር ጠቁመዋል።

ድርቅ በተከሰተበት ኦሮሚያ ክልል ቦረና አካባቢ የጤና መድሕን ወጪን መሸፈን ያልቻሉ ዜጎች በመኖራቸው የጤና መድሕን የአባልነት መዋጫቸውን ሊሸፈን የሚችልበትን ሁኔታ የሚያመቻች ክፍል ተቋቁሞ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህ ባለፈ በዘንድሮው ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ በ894 ወረዳዎች ላይ ይሰጥ የነበረውን የጤና መድሕን አገልግሎት ወደ 950 ወረዳዎች ለማሳደግ ታቅዶ ወደ ሥራ መገባቱን አቶ ዘመድኩን አንስተዋል።

በ22 አዲስ ወረዳዎች ላይ የአገልግሎት ምዝገባ ማስጀመር መቻሉን ገልጸው፤ በአሁኑ ሰዓት 916 ወረዳዎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በቀጣይ ደግሞ በአክሱምና መቀሌ ቅርንጫፎች የሚገኙ 36 ወረዳዎች በአዲስ መልክ የጤና መድሕን አገልግሎቱን እንዲያገኙ ከጤና ሚኒስቴርና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እየተሠራ ነው፡፡ በዚህም የጤና መድሕን አገልግሎቱን ወደ 955 ወረዳዎች ለማሳደግ ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

በሚጨመሩ ወረዳዎች ላይ አዲስ የጤና መድሕን ተመዝጋቢዎች እንደሚኖሩ ስለሚጠበቅ በቁጥሩ ልክ የአገልግሎት ክፍያቸውን መክፈል የማይችሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ታሳቢ ያደረገ የመንግሥት ጤና መድሕን ድጎማ መጨመሩ እንደማይቀር አስረድተዋል።

እንደ አቶ ዘመድኩን ገለፃ፣ በ2014 ዓ.ም ከ45 ሚሊዮን በላይ አባወራዎችንና እማወራዎችን በጤና መድሕን አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ የተጀመረው የአዳዲስ አባላት ምዝገባና እድሳት አገልግሎት የካቲት ወር መጨረሻ ላይ ሲገባደድ አጠቃላይ የጤና መድሕን ተጠቃሚዎች ቁጥር 50 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይጠበቃል ብለዋል።

በግማሽ ዓመቱ አፈጻጸም 8 ነጥብ 3 ሚሊዮን አባወራዎችና እማወራዎች ለጤና መድህን አገልግሎት ምዝገባና ዕድሳት መፈጸማቸውን ገልጸው፤ ከጤና መድህን አገልግሎት ከአባላት ምዝገባና እድሳት መርሃግብር 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ገቢ መደረጉን አስታውቀዋል፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ ደብረማርቆስ፣ ደሴ፣ አዲስአበባ፣ ደብረብርሀን እና አዳማ ከተሞች የተሻለ የጤና መድህን አገልግሎት አፈጻጸም አሳይተዋል ሲሉ አቶ ዘመድኩን ገልጸዋል፡፡



# ፋብሪካዎች ከ400 ሺህ ኩንታል በላይ ስኳር አምርተዋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- አራት ስኳር ፋብሪካዎች በሦስት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ከ400 ሺህ ኩንታል በላይ ስኳር ማምረት መቻላቸውን የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ የሕዝብ ግንኙነትና ተሳትፎ ክፍል ኃላፊ አቶ ረታ ደመቀ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ፋብሪካዎቹ ከታኅሳስ ወር መጨረሻ ጀምሮ እስከ ጥር ወር አጋማሽ ባሉት ሦስት ሳምንታት ያመረቱት ስኳር 40 ሚሊዮን ኪሎ ግራም ነው።

አቶ ረታ እንዳስታወቁት፤በአሁኑ ወቅት ምርት ላይ የሚገኙት አራቱ የስኳር ፋብሪካዎች ፊንጫ፣ ወንጂ፣ ኦሞ ኩራዝ ሁለትና ሶስት ናቸው። በአጠቃላይ ወደ ሥራ እንዲገቡ የታቀዱት ስምንቱ የስኳር ፋብሪካዎች ቢሆኑም በአሁኑ ወቅት አራቱ ብቻ በተወሰነ አቅማቸው ምርት እየሰጡ ይገኛሉ። በቀጣይ ወደ ምርት እንደሚገቡ የሚጠበቁት ጣና በለስ፣ ከሰም፣ አርጆ ዴዴሳና መተሐራ ስኳር ፋብሪካዎች የጥገና ሥራቸውን በማጠናቀቃቸው ከጥር ወር መጨረሻ አንስቶ ወደ ማምረት ሥራቸው ይመለሳሉ፡፡

ኮቪድ-19 ወረርሽን መከሰት፣የሰሜኑ ጦርነት፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንዲሁም ከውጭ ወደ ሀገር የሚገቡ ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚጠቅሙ የተለያዩ ግብዓቶች እጥረት ባለፉት ሦስት ዓመታት የስኳር ምርት የአቅርቦት እጥረት እንዲከሰት ምክንያት ሆነዋል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም በ2014 ዓ.ም የማዳበሪያ፣ የኬሚካልና የፀረ-አረም ግብዓቶች እጥረት ተከስቶ ነበር ያሉት አቶ ረታ፤ በዚህም ምክንያት ለፋብሪካዎቹ ዋነኛ ግብዓት የሆነው የሸንኮራ አገዳ ዘግይቶ በመድረሱ የፋብሪካዎች ምርት ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ገልጸዋል።

አሁን ላይ በተወሰነ መልኩ ችግሮቹ በመቃለላቸው የስኳር ፋብሪካዎቹን ወደ ሥራ ማስገባት መቻሉን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ረታ ገለጻ፤ በሀገሪቱ ያለውን የስኳር አቅርቦት እጥረት ለመቀነስ ያሉት ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ማምረት እንዲችሉ የመፍትሔ አቅጣጫ ተቀምጦ ወደ ተግባር ተገብቷል።

በዘርፉ ላይ ያለውን ችግር ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሚከናወኑ ሥራዎች ምርት ለማሳደግ ጥረት ይደረጋል ያሉት አቶ ረታ፤ በዓመት ከ2 ሚሊዮን 270 ሺህ ኩንታል በላይ ስኳር ለማምረት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በሀገሪቱ ያለውን የስኳር እጥረት በጊዜያዊነት ለመቀነስ ደግሞ 110 ነጥብ 4 የአሜሪካን ዶላር ወጪ የተደረገበት ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ስኳር በቅርቡ ወደ ሀገር ውስጥ ይገባል ብለዋል፡፡

ከብራዚል ተገዝቶ የሚመጣው ስኳር በአራት ዙር ወደ ሀገር ውስጥ እንደሚገባ የሕዝብ ግንኙነትና ተሳትፎ ክፍል ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

# በሲዳማ ክልል በ116 ሺህ ሄክታር መሬት ሳይ የተፋሰስ ልማት ሥራ እየተከናወነ ነው

**ገመቹ ከድር**



**አቶ መስፍን ቃሬ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ በጀት ዓመት 116 ሺህ ሄክታር መሬት በተፋሰስ ልማት ለመሸፈን እየተሠራ መሆኑን የሲዳማ ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ አስታወቀ። የተፋሰስ ልማት ሥራው ሀዋሳ ሐይቅንና ጊዳቦ ግድብን ከደለል መከላከል ላይ ትኩረት እንደሚያደርግም ተገልጿል ።

የሲዳማ ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ኃላፊ አቶ መስፍን ቃሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ ዘንድሮ በተፋሰስ ልማት 44 ሺህ ኪሎ ሜትር እርከንና ሌሎች የተፋሰስ ሥራዎችን በመሥራት 116 ሺህ ሄክታር መሬት ወደ ልማት እንዲገባ ለማድረግ እየሠራ ነው። ተፋሰስ ልማቱ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የሰባት በመቶ ጭማሪ እንዳለውም ገልጸዋል።

እንደ አቶ መስፍን ገለፃ፣ ለ30 ቀናት ተግባራዊ የሚደረገው የተፋሰስ ልማት ከመጀመሩ በፊት ክልላዊ የንቅናቄ መድረኮችን በማዘጋጀት አስፈላጊ ዝግጅቶች ተደርገዋል። ከዚህ በፊት በክልሉ ተግባራዊ ከተደረጉ ሥራዎች በመነሳት ዳገታማ እና ተራራማ አካባቢዎችን በጠረጴዛማ እርከኖች ወደ ነበሩበት ቦታዎች የመመለስ ተሞክሮዎችን ወደ ሌሎች ወረዳዎች የማስፋት ሥራ ይሠራል ብለዋል ።

ጥራት ያለው እርከን ሥራ መሥራት እንደ አቅጣጫ ተቀምጧል ያሉት አቶ መስፍን፤ ክልሉ በቡና ምርት ስለሚታወቅ በቡና ማሳ ውስጥ የቡና ምርት እና ምርታማነት ለመጨመር የሚያስችሉ የጉድጓድ ዝግጅት እና መሰል ሥራዎች ተያይዘው እንደሚሠሩ ገልጸዋል ።

ተፋሰስ ልማት ከአረንጓዴ አሻራ ጋር በማስተሳሰር ለቀጣዩ አረንጓዴ አሻራ ልማት 300 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም አያይዘው ገልጸዋል። በተራቆቱ መሬቶች ላይ የእንስሳት መኖ ማልማትን ጨምሮ ሀዋሳ ሐይቅ እና ጊዳቦ ግድብን ከደለል ለመከላከል በሚያስችሉ ሥራዎች ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራ አብራርተዋል።

ከዚህ በፊት በተሠሩ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች እርጥበት ማቆየት ተችሏል። ከዚህም የተነሳ ምርት እና ምርታማነት ጨምሯል፣ የመሬት መሸርሸር ቀንሷል። ከልማት ውጪ የነበሩ መሬቶች ወደ ልማት ተመልሰዋል፤ ምንጮችም እየጎለበቱ ነዉ ብለዋል ።

እንደ አቶ መስፍን ማብራሪያ፤ ቀጣይ ሥራዎች በጠረጴዛማ እርከን ኮረብታማ እና ተራራማ አካባቢዎችን ወደ ልማት እንዲገቡ በማድረግ ምርትና ምርታማነት በሚጨምሩ ሥራዎች ላይ ትኩረት ይደረጋል። ከቡና ምርት ጋር በተያያዘ ኮምፖስት ማዘጋጀት፣ ህዳጎችን በመሥራት የእንስሳት ምርት እና ምርታማነት እንዲጨምሩ በማድረግ የአረንጓዴ አሻራን ልማት ማስቀጠል ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው ሲሉ ተናግረዋል።

# የፋይናንስ ተቋማት ሀብት 2 ነጥብ 9 ትሪሊዮን ብር መድረሱ ተገለጸ

- 71 የፋይናንስ ተቋማት በምሥረታ ሂደት ላይ ሲሆኑ
- የተበዳሪዎች ቁጥር በ 7 ነጥብ 8 በመቶ ቀንሷል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት የፋይናንስ ተቋማት ሃብት መጠን ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ትሪሊዮን የደረሰ ሲሆን የተበዳሪዎች ቁጥር ደግሞ በሰባት ነጥብ ስምንት በመቶ እንደቀነሰና 71 የፋይናንስ ተቋማት በምሥረታ ሂደት ላይ እንዲሆኑ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በፋይናንስ ዘርፉ የስድስት ወራት አፈፃጸም እና በቀጣይ ሊሠሩ የሚገቡ ሥራዎች ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተወያይቷል። የፋይናንስ ዘርፉን ስድስት ወራት አፈፃጸም አስመልክቶ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዢ አቶ ሰለሞን ደስታ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

እንደ አቶ ሰለሞን ገለፃ፤ ባለፉት ስድስት ወራት የፋይናንስ ተቋማት ሃብት ብር ሁለት ነጥብ ስምንት ትሪሊዮን ደርሷል። ይህም የሠላሳ በመቶ እድገት ነው። ከዚህ ውስጥ የባንኮች ሁለት ነጥብ ስምንት ትሪሊዮን፤ የኢንሹራንስ ብር ዜሮ ነጥብ ዜሮ አራት ትሪሊዮን ነው። የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ደግሞ ብር ዜሮ ነጥብ ዜሮ አምስት ትሪሊዮን ሲሆን የሌሎች ተቋማት ሃብት ብር ዜሮ ነጥብ ዜሮ ሁለት ትሪሊዮን ነው።

የፋይናንስ ተቋማቱ ተቀማጭ ብር 2 ትሪሊዮን ደርሷል። ከዚህ ውስጥ የባንኮች ተቀማጭ ብር አንድ ነጥብ ዘጠኝ ስምንት ሲሆን የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ደግሞ ዜሮ ነጥብ ዜሮ ሁለት ትሪሊዮን ነው። በምሥረታ ላይ ያሉና ፍቃድ ያልወሰዱ የፋይናንስ ተቋማት ቁጥር ደግሞ 71 ናቸው። ከነዚህም ውስጥ ደግሞ 8 ባንኮች፣ 54 አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት፣ 9 ሲስተም ኦፕሬተሮች ይገኙበታል።

የፋይናንስ ተቋማት ቁጥር መቶ ዘጠኝ በመድረሱ ይህም የ27 በመቶ እድገት አሳይቷል። ከመቶ ዘጠኙ የፋይናንስ ተቋማት ውስጥ 31 ባንኮች፣ 18 ኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ 44 አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ሲሆኑ የተቀሩት 16ቱ ደግሞ በፋይናንስ ዘርፉ የሚገኙ አካላት ናቸው ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ባለፉት ስድስት ወራት የተበዳሪዎች ቁጥር አራት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ነው። ይህም በሰባት ነጥብ ስምንት በመቶ ቀንሷል።

ባለፉት ስድስት ወራት በዘርፉ እድገት ተመዝግቧል ያሉት ደግሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ አቶ ማሞ ምህረቱ ናቸው። እንደ አቶ ማሞ ገለፃ፤ ባለፉት ስድስት ወራት በፋይናንስ ዘርፉ ጥሩ ውጤት ተመዝግቧል። የባንክ ዘርፉ የገዛው ከመቶ ሃምሳ ሰባት ቢሊዮን ብር


ፎቶ - እዮብ ተፈሪ

**አቶ ማሞ ምህረቱ**

በላይ የግምጃ ቤት ሰነድ የበጀት ጉድለትን በመሙላት የፋይናንስ ዘርፉን አስተዋጽዖ እንዲጨምር አድርጓል።

ባንኮች የሚያሰባስቡት ተቀማጭና ሪሶርስ በየዓመቱ በአማካኝ የ30 በመቶ እድገት እያመጣ ነው ያሉት ገዢው፤ ይህ ካለፈው በጀት ዓመት ሲነፃጸር ወደ አራት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ተቀማጭ ገንዘብ ባንኮች ማንቀሳቀስ ችለዋል። ባንኮች የሚሰጡት ብድር ከዓመት ዓመት እየጨመረ ነው። ይህም በአዎንታ የሚያታይ ነው። ምክንያቱም የኢኮኖሚውን እድገት ለማገዝና ቀጣይነት እንዲኖር ባንኮች የሚሰጡት ብድር ወሳኝ ነውና።

የብሔራዊ ባንክ ገዢው አቶ ማሞ ምህረቱ በቀጣይ የብሔራዊ ባንክ የትኩረት አቅጣጫዎችን ተናግረዋል። በቀጣይ የሚደረጉ የገንዘብ ፖሊሲ አንደኛ የዋጋ ንረቱን እንዳያባብስ በተቻለ መጠን ጥረት ይደረጋል። ሁለተኛ ባንኮች የሚከተሉት የብድር ፖሊሲ አጠቃላይ ልማቱን የሚደግፍና የግል ዘርፉን የሚያበረታታ እንዲሆን ይደረጋል።

የሀገሪቱ የፋይናንስ ተቋማት በዓለም አቀፍ መመዘኛ መሠረት ሥራቸውን እያከናወኑ እንደሆነ የማወቅና የቁጥጥር ሥራ ይሠራል። የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲ የውጭ ንግዱን የሚያበረታታ እና ገቢ ምርቶችን ለመተካት የሚያግዝ መሆኑን የማረጋገጥ እና የውጭ ምንዛሪ ክምችት ተገቢውን ደረጃ ይዞ እንዲቀጥል የሚያግዝ ሥራ ይሠራል። እነዚህን ጉዳዮች ለማሳካት ጊዜ የሚያስፈልግ መሆኑን መረዳት ይገባል ብለዋል።

# በሰሜን ወሎ ዞን ከ19 ሺህ በላይ ዜጎች የሥራ እድል ተፈጥሯል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት ለ19 ሺህ 880 ዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን የሰሜን ወሎ ዞን ሥራና ሥልጠና መምሪያ አስታወቀ።

የሰሜን ወሎ ዞን ሥራና ሥልጠና መምሪያ ምክትል ኃላፊ ወይዘሮ እህትዬ ታረቀ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበጀት ዓመቱ ለ78 ሺህ 518 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ባለፉት ስድስት ወራት በተደረገው ጥረት 19 ሺህ 880 የሥራ ዜጎች የሥራ እድል ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል 12 ሺህ 460 ወንዶች እንዲሁም 7 ሺህ 420 ሴቶች ናቸው፡፡

የሥራ እድሉ የተፈጠረው በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በኢንዱስትሪ፣ በአገልግሎት ፣ በኮንስትራክሽን እና ማዕድን ዘርፎች ነው ያሉት ምክትል ኃላፊዋ፤ በግብርና ዘርፍ ብቻ ለ7 ሺህ 823 ሰዎች የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል ብለዋል፡፡

በኢንዱስትሪው፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በኮንስትራ ክሽን እና ማዕድን ዘርፎች ደግሞ ለ8 ሺህ 14 ዜጎች የሥራ እድል የተፈጠረ ሲሆን፤ በአገልግሎትና ንግድ ዘርፎች ለ3ሺህ 895 የሥራ እድል መፍጠር እንደተቻለ አስረድተዋል።

መምሪያው ከስደት ተመላሽ ሴቶችን በሥራ እድል ተሳታፊ እንዲሆኑ እየሠራ ነው ያሉት ወይዘሮ እህትዬ፤ በስድስት ወር አፈጻጸም ከስደት ለተመለሱ 210 ዜጎችና ለ49 የአካል ጉዳተኞች የሥራ እድል መፈጠሩን ጠቁመዋል። በተጨማሪም ሴቶችን በተለያዩ ኢንተርፕራይዞች አሰልጥኖ የሥራ ቦታ እና የብድር አገልግሎት እንዳመቻቸ ገልጸዋል።

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት የሥራ እድል ፈጠራው ተዳክሞ መቆየቱንና አሁን ላይ



**ወይዘሮ እህትዬ ታረቀ**

መነቃቃቶች እንደተፈጠሩ ገልጸዋል።

አሁን ላይ የተፈጠረውን ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም ተቀዛቅዞ የነበረውን ኢኮኖሚ የማካካስ ተግባር ይፈጸማል። የሥራ እድል ፈጠራውን በተደራጀ አግባብ ለመምራትና እቅዱን ለማሳካት ጥረት እየተደረገ ይገኛል ሲሉ ምክትል ኃላፊዋ ተናግረዋል።

በዞኑ የሚገኙትን ማሰልጠኛዎች መልሶ ለማቋቋምና የሥራ ዕድል ፈጠራውን ለማጠናከር የግልና የመንግሥት አካላት እንዲሁም ሰብዓዊ ድጋፍ አቅራቢ ተቋማት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

# ስንዴን ጨምሮ አምስት ምርቶች ወደ ምርት...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

የምርት ገበያው ከ15 ዓመት በፊት ሥራ ሲጀምር ያገበያያቸው ከነበሩ ሁለት ምርቶች ስንዴ አንዱ እንደነበር አቶ ነፃነት አንስተዋል።

የስንዴ ዘመናዊ ግብይት ከተቋረጠ በኋላ አሁን ላይ በኢትዮጵያ የስንዴ ምርትና ምርታማነት እያደገ በመምጣቱ ከአገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ለውጪ ሀገር ገበያ ማቅረብ የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ብለዋል።

የስንዴ ምርት ግብይት ሕጋዊና ተጠያቂነት ባለበት በቴክኖሎጂ ሥርዓት መመራት ስላለበት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት ግብይት ኮንትራት ውል ማዘጋጀቱን ጠቁመዋል።

ከስንዴ በተጨማሪ ግብጦ፣ ኮረሪማ፣ባቄላና ሩዝ ወደ ምርት ገበያ ሥርዓት እንዲገቡ መደረጉ ምርታማነታቸው መጨመሩን ያሳያል ሲሉ ተናግረዋል። አጠቃላይ የግብይቱ ሥርዓቱ በሕግ እንዲመራ በማድረግ ጥራቱን የጠበቀ ምርት ወደ ግብይት ሥርዓቱ እንዲቀርብና አርሶ አደሩ የምርቱን ዋጋ አውቆ፣ተደራድሮ መሸጥ የሚችልበትን ዕድል የሚፈጥር መሆኑን ጠቁመዋል። በምርት ገበያው መገበያየቱ ለአርሶ አደሩም ሆነ ለአገሪቱ የግብይት ሥርዓት ጠቀሜታው የጎላ ነው መሆኑን አቶ ነፃነት ገልጸዋል።

በዘመናዊ ሥርዓቱ አማካኝነት የዱቄት፣ ማካሮኒና ፓስታ አምራች ድርጅቶች እንዲሁም የተለያዩ ፋብሪካዎች ለግብዓትነት የሚጠቀሙበትን የስንዴ፣ ሩዝ፣ ባቄላና በምርት ገበያው በኩል እንዲገበያዩ የሚያስችል ዕድል መፈጠሩን አቶ ነፃነት አስታውቀዋል።

ምርት ገበያው በግብይት ሥርዓቱ ምርት በሚቀበልባቸው 25 ቅርንጫፎች ውስጥ የዘመናዊ ግብይቱን ሥርዓት ያከናወናል፡፡ በዚህም አርሶ አደሮች ላቀረቡት ምርት የሚቀበሉትን ገንዘብ ያለምንም ችግር በባንክ አካውንታቸው እንዲገባላቸው ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

የአምስቱ ምርቶች ግብይት እስካሁን በምርት ገበያ ሥርዓቱ መረጃ ያልነበረው በመሆኑ ላኪዎችና ፋብሪካዎች ደረጃውን የጠበቀ ምርት ለማግኘት ተቸግረው ነበር፤ አሁን ላይ ግን ችግሩን የሚቀርፍ ሕጋዊ ሥርዓት በመፈጠሩ ተጠቃሚነታቸውን እንደሚያሳድግ አቶ ነፃነት ገልጸዋል።

ስንዴንና ሌሎቹን ምርቶች በግብዓትነት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችም ሕጋዊ የምዝገባ ሂደቱን አሟልተው ሲገኙ በምርት ገበያው በኩል መግዛት እንደሚችሉ አቶ ነፃነት አሳውቀዋል።

ምርቶቹን ወደ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ለማስገባት የተደረገውን ጥረት የተባበሩት መንግሥታት የምግብና እርሻ ድርጅት /ፋኦ/ የ2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ማድረጉ ተገልጻል፡፡ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወደ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ያስገባቸውን ምርቶች ቁጥር ወደ 22 ከፍ ማድረግ ችሏል።

# "ከጎረቤት ሃገራት ጋር ያለውን የድንበር...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በቋሚነት የሚከታተል አካል ማደራጀት አስፈላጊ መሆኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን አስታወቁ።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የ2015 በጀት ዓመት የ6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ትናንትና ውይይት አካሂዷል።

በወቅቱ ከሱዳን፣ከጂቡቲና ከሌሎች ጎረቤት ሀገራት ጋር የሚስተዋሉ የድንበር ማካለል ችግሮችን እንዲሁም የተለያዩ የድንበር ተሻጋሪ ሃብቶችን ጉዳይ በተመለከተ በመሠረታዊነት ክትትል የሚያደርግ አካል ያስፈልጋል ሲሉ አቶ ደመቀ መኮንን ገልጸዋል።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በየአራት ዓመቱ ከሚቀያየሩ አምባሳደሮች ባለፈ በቋሚነት የድንበር ጉዳዮችን መከታተልና አስፈላጊውን መረጃና ማስረጃ የሚያቀርብ አካል ማቋቋም አስፈላጊ ነው ብለዋል።

አሁን ላይ ከሱዳንና ጅቡቲ ጋር የድንበር ጉዳዮችና ተሻጋሪ ሃብቶች ላይ በትብብር ለመሥራት የሚያስችል የድንበር ኮሚሽን ለማቋቋም ሁኔታዎች ተመቻችተዋል ብለዋል።

ከዚህ ባለፈ ግን የኢትዮጵያ መንግሥት በተለይ በውጭ ጉዳይ በዋናነት ድንበራችንን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ አካል ማቋቋምና የሰው ኃይል መመደብ ጠቀሜታ አለው ሲሉ አቶ ደመቀ ገልጸዋል።

ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለንን ግንኙነት በማጠናከር ረገድ ሰፊ ሥራ ተከናውኗል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ከኬንያ፣ ከሱዳን፣ ከሶማሊያና ከሌሎች ጎረቤት ሃገራት ጋር ምክክር በማድረግ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተሻለ መግባባት መፍጠር እንደተቻለ አስታውቀዋል።

የዓለም ፖለቲካ ሁኔታ በየወሩ ሳይሆን በየ24 ሰዓቱ የሚለዋወጥበት ሁኔታ በመኖሩ ፤ ሁኔታውን ተከትሎ የሚሄድ የዲፕሎማሲ ሥራ ያስፈልጋል ሲሉ አቶ ደመቀ መኮንን ተናግረዋል።

አቶ ደመቀ አክለውም የኃያላን አገራት ፍጥጫ በመጣ ቁጥር አንዱን ወግነን የምንቆምበት ሁኔታ አይኖርም፤ ተለዋዋጭ ጉዳዮችን መሠረት አድርገን የሃገራችንን ጥቅም ለማስከበር የሚረዳ ጠንካራ ዲፕሎማሲ መንገድ እንከተላለን ብለዋል።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ሃገራት የሚገኙ 53 ሚሲዮኖች እንዳሏት የገለጹት አቶ ደመቀ፤ ሁሉም ሚሲዮኖች በየሳምንቱ በሚቀርብላቸው አቅጣጫ መሠረት የሃገራቸውን ዲፕሎማሲ ሥራ እንዲያጎለብቱ የክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን አስታውቀዋል።

የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ዶክተር ዲማ ነገዎ በበኩላቸው፤ ከቀይ ባሕር ጋር ተያይዞ በሌሎች ሀገራት የተቋቋመው ፎረም ኢትዮጵያን ያላካተተበት መንገድ ጥያቄ የሚያስነሳ መሆኑን ገልጸው፤ ኢትዮጵያን በፎረሙ በማካተት በቀይ ባሕር ላይ ያለንን ሚና ማሳደግ የሚቻልበት ዕድል መፍጠር እንደሚገባ ተናግረዋል።

ለዚሁ አስተያየት ምላሽ የሰጡት አቶ ደመቀ መኮንን፤ ኢትዮጵያን ያላካተተ የቀይ ባሕር ፎረም ውጤታማ እንደማይሆን ኢትዮጵያ በተለያዩ መድረኮች አቋሟን ማሳወቋን ገልጸው፤ ፎረሙ የቀይ ባሕር ቀጣናዊ ሚና ያላትን ኢትዮጵያን ያካተተ እንዲሆን የሚያስችሉ የተለያዩ ጥረቶች እየተከናወኑ መሆኑን ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ለፈተና የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት አስችሏል!

ባለፉት አራት ዓመታት ኢትዮጵያ እንደ አገር ስር ነቀል የሚባል ለውጥ ውስጥ ገብታለች፡፡ አገሪቱ ከሴራና ከመገፋፋት ፖለቲካ ወጥታ አሳታፊና አካታች የፖለቲካ ሥርዓት ለመገንባት ካደረገችው ጥረት ባሻገር በኢኮኖሚ ዘርፉም በራሷ መንገድ ተጉዛ በርካታ መሻሻሎች ተመዝግበዋል፡፡

ከለውጡ በፊት በነበሩ ዓመታት ኢትዮጵያ ስትከተለው የነበረው የኢኮኖሚ ሥርዓት የውጭ ብድርና ዕርዳታን መሠረት ያደረገ ስለነበረ አገሪቱን ከፍተኛ ለሆነ የብድር ዕዳ ጫና ዳርጓታል፡፡ ከገንዘብ ሚኒስቴር በተገኘው መረጃ መሠረትም በለውጡ ማግስት የኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ብድር ጫና 1 ነጥብ 5 ትሪሊዮን ብር ወይም 52 ነጥብ 57 ቢሊዮን ዶላር ደርሶ ነበር፡፡ ይህ የብድር መጠን ደግሞ አገሪቱ ተጨማሪ ብድሮችን ከአበዳሪ አገራትና ተቋማት እንዳታገኝ ከማድረጉም ባሻገር የተገኘውን ሀብት ሁሉ ለዕዳ ክፍያ እንዲውል አስገድዷል፡፡

በርካታ የልማትና የሥራ ዕድል ጥያቄ ባለባት አገር ውስጥ ለትውልድ የሚተላለፍን ዕዳ እያከማቹ መሄድ በቀጣይ አገሪቱ የማትወጣው አጣብቂኝ ውስጥ እንደሚከታት መንግሥት በመረዳቱ በአፋጣኝ በዓይነቱ አዲስ የሆነ አገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመተግበር እንደአገር ከተገባበት አጣብቂኝ ውስጥ ኢትዮጵያን ለማውጣት ተችሏል፡፡

አገር በቀል የኢኮኖሚው ማሻሻያው አገር በቀል ዕሳቤን በመያዝ ዜጎች ያላቸውን ሀብት እንዲያለሙ፤ ኢትዮጵያ ስትወስድ የነበረውን ከፍተኛ ብድር እንድታቆም የሚያስገድድና የውጭ ባለሀብቶችን በስፋት እንዲገቡ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ የኢኮኖሚ ማሻሻያውም በመቆም ሂደት ላይ የነበረውን የኢኮኖሚ ዕድገት እንደገና እንዲያንሰራራ ከማድረጉም ባሻገር በምሥራቅ አፍሪካ ትልቁን የኢኮኖሚ አቅም መፍጠር ያስቻለ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት ዓመታት በውስጣዊ ችግሮችና ውጫዊ ጫናዎች ከፍተኛ ፈተና ገጥሟት የነበረ ቢሆንም ኢኮኖሚው ዕድገት ከማስመዝገብ ወደ ኋላ አላለም፡፡ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ አጣብቂኝ ውስጥ በገባበት ወቅት እንኳን ኢትዮጵያ 6 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ ኢኮኖሚዋን መታደግ ችላለች፡፡ ባለፉት ሁለት አመታት በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የነበረው ጦርነት በርካታ ቁሳዊና ሰብአዊ ጉዳት ቢያስከትልም ቀደም ሲል ለፈተና የማይበገር ኢኮኖሚ በመገንባቱ እንደ አገር የከፋ ጉዳት ሳያስከትል ችግሩን ማለፍ ተችሏል፡፡

ይኼው ዕድገት ቀጥሎም በተያዘው በጀት አመት ግማሽ አመትም ኢኮኖሚው በርካታ ፈተናዎችን ተቋቁሞ የ8 ነጥብ 2 በመቶ እድገት አስመዝግቧል። ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ምንጮች የሚገኘው የአገር ውስጥ ገቢም ከፍተኛ አፈጻጸም ካስመዘገቡት መካከል ይጠቀሳል። በስድስት ወራት ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ምንጮች 222 ቢሊዮን ብር የአገር ውስጥ ገቢ ተገኝቷል፡፡ ይህም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ28 ነጥብ 9 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል።

በወጪ ንግድ አፈጻጸም ከዘርፉ 1 ነጥብ 8 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ከእቅዱ ጋር ሲነጻጸር 77 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በዓለም ገበያ ያለው የምርቶች ዋጋ ተገማች አለመሆን፤ የሕገ-ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ መስፋፋት፤ በንግድ ሰንሰለቱ ያሉ ማነቆዎችና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች የወጪ ንግድ ዘርፍ ፈተናዎች ቢሆኑም በበጀት ዓመቱ አጋማሽ 1 ነጥብ 9 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ ተችሏል። ይህም በተለይ የኢንዱስትሪ ዘርፉን በማነቃቃት ረገድ ከፍተኛ ሚና አበርክቷል።

ኢኮኖሚው በፈጠረው ምቹ ሁኔታም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት በአገር አቀፍ ደረጃ በአጠቃላይ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል።

እንደ አጠቃላይ መተግበር የጀመረው አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ኢኮኖሚውን ከውድቀት ከመታደጉም ባሻገር አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ የነበረውን ኢኮኖሚ በማነቃቃት የቀጥታ ኢንቨስትመንትን ስበት ጨምሯል፤ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን ብዛትና በዓይነት በማበራከት ከውጭ የሚገኘውን ገቢ አሳድጓል፤ የሥራ ዕድልንም አበራክቷል፡፡ ይሄ ደግሞ በዓለም አቀፍ ተቋማትም ጭምር የተመሰከረና በችግር ውስጥም ሆኖ የማይበገር ኢኮኖሚንም መፍጠሩን የሚያረጋግጥ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## የትምህርት ሥርዓቱን መውደቅ እና የአገር ህልውና አደጋ ውስጥ መግባቱን የጠቆመው የፈተና ውጤት

**ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ**

የ2014 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና ውጤት ከቀናት በፊት ይፋ መደረጉ ይታወሳል። የትምህርት ሚኒስቴር በገለፀው መሠረት፣ ፈተናውን ከወሰዱ 899ሺ520 ተማሪዎች መካከል ከግማሽ በላይ ውጤት (ከ350 በላይ) ማስመዝገብ የቻሉት 29ሺ909 (3.3%) ብቻ ናቸው። ከ50 በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ አዲስ አሠራር ለመከተል መታቀዱንም ሚኒስቴሩ ገልጿል።

በዚህ አሠራር ከግማሽ በላይ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብተው የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች ይሆናሉ፤ ቀሪዎቹ ደግሞ የዩኒቨርሲቲዎችን የመቀበል አቅም መሠረት በማድረግ የተሻለ ውጤት ያመዘገቡት ተማሪዎች ተመርጠው ወደ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲገቡ ይደረጋል፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ተማሪዎች በቀጥታ የአንደኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አይሆኑም፤ ተማሪዎቹ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡባቸውን የትምህርት ዓይነቶች ለአንድ ዓመት በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እየተማሩ ከቆዩ በኋላ፣ በዓመቱ መጨረሻ ፈተና ተፈትነው ካለፉ በዩኒቨርሲቲዎች የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች ሆነው ይቀጥላሉ።

ውጤቱ ይፋ ከተደረገ በኋላ ብዙ ዓይነት አስተያየቶችን አስተናግዷል። አንዳንዶች ከግማሽ በላይ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች ቁጥር እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ የትምህርት ጥራት አለመኖሩን የሚያመለክት እንደሆነ ሲገልፁ፣ ሌሎች ደግሞ «የፈተና ሥርዓቱ ኩረጃንና ሌሎች ሕገ ወጥ የፈተና ተግባራትን ለማስቀረት ያስቻለ የአፈታተን ሥርዓት ነው» ብለውታል። የሆነው ሆኖ፣ የፈተና ውጤቱ አስደንጋጭና አስገራሚ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። ከአጠቃላይ ተፈታኞች መካከል አራት በመቶ ያህሉ እንኳ ከግማሽ በላይ ውጤት አለማስመዝገባቸው «አገር ተረካቢ ነው» ስለሚባለው ትውልድ በእጅጉ እንድንጨነቅ ያስገድደናል።

የ2014 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና አፈታተን ከዚህ ቀደም ከነበሩት የፈተና ሥርዓቶች የተለየ እንደነበር ይታወሳል። ተፈታኞች ፈተናውን የወሰዱት በአቅራቢያቸው ወደሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ገብተው ነበር፤ ፈታኝ መምህራንም ፈተናውን እንዲፈትኑ የተደረገው መምህራኑ ያስተምሩባቸው ከነበሩ ዩኒቨርሲቲዎች ወደ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በመሄድ ነበር።

ይህ የአፈታተን ሥርዓት ኩረጃንና መሰል ሕገ ወጥ የፈተና ተግባራትን ለማስቀረት እንደሚያግዝ ሲነገርም ነበር። የፈተናው ውጤት ሲገለፅ የታየውን እውነት (ከግማሽ በላይ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች ቁጥር ማነስን) ይዘን «ይህ ዓይነት ውጤት የተመዘገበው ኩረጃ ስላልነበር ነው» የሚሉ ወገኖችን ሃሳብ ስናሰላስል፣ «ከዚህ ቀደም በነበሩት ዓመታት የተመዘገቡት ውጤቶች ካለፈው ዓመት የተሻሉ የሆኑት በኩረጃ ነበር ማለት ነው?» ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን።

በሌላ በኩል የፈተናው ውጤት በምን ዓይነት የትምህርት ሥርዓት ውስጥ እያለፍን እንደምንገኝ በግልፅ አሳይቷል። አራት ከመቶ ተፈታኞች እንኳ ከግማሽ በላይ ውጤት አለማስመዝገባቸው ትምህርትን እንዴት እየቀለድንበት እንደሆነ ጥሩ ማሳያ ነው። ይህ ደግሞ የአገር ግንባታ ዋነኛ መሠረት የሆነው አምድና የአገሪቱ ህልውና እጅግ አስደንጋጭ አደጋ ውስጥ እንደገባ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው።

የኢትዮጵያ የትምህርትና ስልጠና ሥርዓት ለትምህርት ዘርፍ መሻሻልና የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራት አዎንታዊ አስተዋፅዖዎችን እንዳበረከተ ባይካድም፣ ዓይነተ ብዙና ውስብስብ ችግሮችም አሉበት። የትምህርትና ስልጠና ሥርዓቱ በንድፈ ሀሳብ እንጂ የተግባር ክህሎትና ፈጠራ ላይ ያተኮረ አይደለም። የምዘና ሥርዓቱም ለተግባራዊ እውቀት ትኩረት አልሰጠም። ሥራ ፈላጊ እንጂ ሥራ ፈጣሪ ትውልድ እየተፈጠረ አይደለም።

የምርምርና የቴክኖሎጂ ሥራው ጎልብቶ ኢኮኖሚውን በሚፈልገው መጠን እያገዘም አይደለም። በዚህ ምክንያት ኅብረተሰቡ በትምህርትና ስልጠና ሥርዓቱ የጥራትና የተገቢነት ጥያቄ እያነሳ ይገኛል። ከትምህርትና ስልጠናው እውቀት፣ ክህሎትና የሥራ ፈጣሪነት አመለካከት በበቂ ሁኔታ ይዞ ከመገኘት ይልቅ ትውልዱ ዲግሪና ዲፕሎማ (ወረቀት) አምላኪ ሆኗል።

ኩረጃና መሰል ሕገ ወጥ የትምህርትና ፈተና ተግባራት እየጎለበቱ በመምጣታቸው የትምህርት ሥርዓቱ የአገር ፍቅር፣ የብዝኃነት፣ የመቻቻልና አብሮ የመኖርና ግብረገብነት እሴቶችን በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት በተጨባጭ ማስረፅ ባለመቻሉ ግለኝነት እያየለ፣ የጎሳ ብሔርተኝነት እየገነነ፣ የአገር ፍቅር እየደበዘዘ መጥቷል። ይህም አገሪቱ የምትፈልገውን ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማፍራት በኩል አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል።

የአንድ አገር የትምህርት ሥርዓት መበላሸት የአገሪቱ ህልውና አደጋ ውስጥ እንደገባ ሁነኛ ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል። ሰላም የሰፈነባት፣ ማኅበራዊ መረጋጋት ያለባት፣ ምጣኔ ሀብቷ ያደገና ፖለቲካዋ የሰከነ አገር እውን ማድረግ የሚቻለው ጥራት ባለው የትምህርት ሥርዓት በተገነባ ትውልድ ነው። ጥራት በሌለውና በወደቀ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ያለፈ ትውልድ ለአገር ህልውና ትልቅ አደጋ ይሆናል።

በሥነ ምግባር ያልታነፀና ኩረጃን መሣሪያ ያደረገ ተማሪ የአገር ሸክምና አደጋ እንጂ የአገርና የሕዝብ መኩሪያና መመኪያ ሊሆን አይችልም። ለዚህም ነው «አንድን አገር ለማፍረስ ጦር ማዝመት ሳያስፈልግ፣ የአገሪቱን የትምህርት ሥርዓት ማበላሸት በቂ ነው» የሚባለውን ሃሳብ በተደጋጋሚ የምንሰማው።

በራሳቸው የሚተማመኑ፣ በምክንያታዊ ትንተና የሚያምኑ፣ በሙያቸው ብቃት ያላቸው፣ ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂዎች፣ ጠንካራ የሥነ ምግባርና ግብረገባዊ እሴቶችን የተላበሱ፣ ለሕግ ዘብ የቆሙ፣ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ብቁ ዜጋ ሆነው አጠቃላይ ሰብእናቸው የተገነባ ዜጎችን ማፍራት የሚቻለው ጥራት ባለው የትምህርት ሥርዓት ነው።

አንዲት አገር ሁለንተናዊ እድገትን በማምጣት የሕዝቦቿን ኑሮ ማሳደግ የምትችለው በሚኖራት የሰው ኃይል እምቅ አቅም ነው። የሰው ኃይል መገንቢያው ዋነኛው መሣሪያ ደግሞ ትምህርት ነው። አስተማማኝና ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት ብቸኛው መንገድ ጥራት ያለው የትምህርት ሥርዓትን መዘርጋት ነው።

ከቀናት በፊት ይፋ የተደረገው የ2014 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና ውጤት፣ የትምህርት ሥርዓቱን ክፍተቶች አሳይቷል። ውጤቱ የትምህርት ሥርዓቱ መውደቅ ለአገሪቱ ህልውና ትልቅ አደጋ እንደሆነም አመላክቷል። ስለሆነም ከዚህ ችግር ለመውጣት የሚያስችሉ የመፍትሄ አማራጮችን በፍጥነት መመልከትና መተግበር ያስፈልጋል።

የትምህርት ጥራትን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ተማሪዎችን ያማከለ ዘመናዊና አሳታፊ የመማር ማስተማር ሂደት መከተል፤ የመምህራን ጥራትና ተነሳሽነት ማጎልበት፤ ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደትን መከተል፤ ተማሪዎችን ማነቃቃት፤ ጠንካራ የትምህርት ቤት አመራርን ማብቃት፤ ምቹና ጤናማ የትምህርት አካባቢ መፍጠር፤ የማስተማሪያ ግብዓቶች ማሟላት እንዲሁም የተማሪዎች ሥነ ምግባርን ማሳደግ ይገባል።

የተማሪዎች ትምህርታቸውን በሚገባ የመከታተል፤ የመምህራን በጥራት የማስተማር፤ የትምህርት አመራር ስትራቴጂካዊ አመራር የመስጠት እንዲሁም የወላጆች ልጆቻቸውን በንቃት የመከታተልና የመደገፍ ተግባራት በቅንጅት ሊከናወኑ ይገባል።

በትምህርትና ስልጠና በቂ የሰው ኃይል ለማፍራት ባለፉት ዓመታት የትምህርትን ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ አግባብነትና ጥራትን ለማጎልበት የተሠሩ ሥራዎች ያስገኙትን ውጤት መገምገምም ይገባል።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ በሥነ ምግባር፣ በመልካም እሴትና በብቃት የታነጸ ዜጋን ለማፍራት በሚያስችል መንገድ የተቀረፀ፣ የአገሪቱን ዕድገትና አንድነት በሚያስቀጥልና ለአገር በቀል እውቀቶች ተገቢውን ትኩረት የሰጠ መሆኑን በሚገባ መፈተሽና ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

# ነፃ ሃሳብ



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የወደቅነው ሁላችንም ነን ፤

(ክፍል አንድ)

የዘንድሮው የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤት እንደ ሀገር ፣ ሕዝብና ተቋማት ገመናችንን አደባባይ በማስጣት አንገታችንን አስደፍቶናል። አሸማቆናል። ከዚህም ባሻገር ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ እኛም እንደ ሀገር ፣ ሕዝብና ተቋማት ከተፈታኞች ጋር መውደቃችንን አርድቶናል ። የዘራነውን አሳጭዶናል። በዚህ አሳፋሪ ውጤት የተማሪዎች ፣ የአስተማሪዎች ፣ የወላጆችና አጠቃላይ የትምህርት ማህበረሰቡ ቅስም ተሰብሯል ። በሌላ በኩል የመጣንበትን መንገድ ቆም ብለን እንድናብሰለስል አድርጎናል ።

የትምህርት ስርዓቱ ወሳኝ መታጠፊያ ላይ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ አሳይቶናል ። በእልህና በቁጭት በመነሳሳት ድክመታችንን በማረም የወደቀውን የትምህርት ጥራት በአንድነት ማሻሻል የመጀመሪያው ወሳኝ መታጠፊያ ሲሆን ፤ መጭውን ጊዜ ራስን ከተጠያቂነት ለማሸሽ ጣት በመቀሳሰር ማሳለፍ እና ሌላ ትውልድ ይዞ እንደገና መውደቅ ሁለተኛው ወሳኝ መታጠፊያ ነው ።

መቼም የአብዛኛዎቻችን ምርጫ የመጀመሪያው ወሳኝ መታጠፊያ ነውና በእልህና በቁጭት በመነሳት ይሄን ሀገራዊ ስብራት አክመን ውጤታማ እናደርገዋለን ብዬ አምናለሁ ። ለመግቢያ ያህል ይሄን ካልሁ መጀመሪያ አመዳችንን ቡን ወዳደረገው የዘንድሮ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ፤ በማስከተል ደግሞ ለዚህ ውጤት የዳረገንን መንገዳችንን መለስ ብዬ እቃኛለሁ ።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የ2014 ዓም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ውጤትን በማስመልከት አዲስ አበባ ውስጥ በዚያ ሰሞን በሰጡት መግለጫ ላይ ለፈተናው ከተቀመጡት አጠቃላይ ተማሪዎች መካከል ከግማሽ በላይ ውጤት ያስመዘገቡት ከአራት በመቶ በታች ናቸው ። የተመዘገበውን ውጤት “አስደንጋጭ” ያሉት ሚኒስትሩ ፈተናውን ከወሰዱት ከ980 ሺህ በላይ ተማሪዎች መካከል ወደ 30 ሺህ የሚጠጉት ብቻ ናቸው ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ማግኘት የቻሉት ።

በተደጋጋሚ በብሔራዊው ፈተና ይከሰታል ሲባል የቆየውን የፈተና ስርቆት ለማስወገድ በሚል የትምህርት ሚኒስቴር ባዘጋጀው ዕቅድ መሠረት ተማሪዎቹ ፈተናውን ለመጀመሪያ ጊዜ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ መውሰዳቸው ይታወሳል ።በተጨማሪም ቀደም ሲል ከነበረው የፈተና አሰጣጥ በተለየ የተፈጥሮ ሳይንስ እና የማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ተማሪዎች በተለያየ ጊዜ በተናጠል ፈተናውን ወስደዋል።

ሚኒስትሩ እንደተናገሩት ተግባራዊ በተደረገው አዲስ አሠራር መሠረት በፈተና ወቅት ምንም ዓይነት ስርቆት አልተፈጸመም ። ባለፈው ሐሙስ ጥር 18 ቀን 2015 ዓም ይፋ የተደረገው ውጤትም በፈተና ወቅት የኮረጁ ተማሪዎችን ሳያካትት በሥርዓቱ መሠረት የተፈኑ ተማሪዎች ውጤት ብቻ ነው ።

ለፈተናው ለመሳተፍ በአጠቃላይ 985,384 ተማሪዎች ተመዝግበው ተፈትነው ውጤት የተያዘላቸው ተማሪዎች ደግሞ 896,520 ናቸው ። ከእነዚህም ውስጥ ለፈተናው ተመዝግበው ያልተፈተኑ 77,098 ተማሪዎች እንዲሁም 20,170 የሚሆኑት ደግሞ በፈተናው ላይ ተገኝተው “በተለያዩ የደንብ ጥሰቶች እንዳይፈተኑ የተደረጉ እና ፈተናውን ትተው የሄዱ” መሆናቸውን ፕሮፌሰር ብርሀኑ ገልጸዋል ። በአማራ ክልል በፈተናው ወቅት የተለያዩ ምክንያቶችን በማቅረብ 12 ሺህ የሚሆኑ ተማሪዎች ፈተናውን ላለመውሰድ ወስነው ትተው የወጡትንም ያካትታል ።

ከ50 በመቶ በታች ያመጡ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ እንደማይገቡ ሚንስትሩ ገልጸው ፤ ነገር ግን የዩኒቨርሲቲዎችን የመቀበል አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት በውጤታቸው መሠረት ተጨማሪ ተማሪዎችን በመቀበል ለቀጣይ ዓመት ዩኒቨርሲቲ መግባት የሚያስችላቸውን ውጤት እንዲያገኙ ይሠራል። በመቶኛ ሲሰላ የ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል የተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ ተፈታኞች ከ50 በመቶ ባላይ ውጤት በማስመዝገብ ከማኅበራዊ ሳይንስ አቻዎቻቸው የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል ።

ከ339,642 የተፈጥሮ ሳይንስ ተፈታኞች መካከል 6.8 በመቶው እንዲሁም የማኅበራዊ ሳይንስ ፈተናን ከወሰዱት 556,878 ተማሪዎች መካከል ደግሞ 1.3 በመቶው ብቻ ከ50 በመቶ በላይ ነጥብ አግኝተዋል። በዚህም መሠረት ከ50 በመቶ በላይ ነጥብ ያስመዘገቡ 30 ሺህ የሚሆኑ ተማሪዎች በቀጥታ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ገብተው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ይሆናል ።

ከዚህ ባሻገር ደግሞ የአገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች የመቀበል አቅምን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት “የተሻለ ውጤት ያመጡት ተመርጠው ወደ ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ የሚደረግ ቢሆንም እነዚህ ተማሪዎች በቀጥታ የዩኒቨርሲቲ የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች እንደማይሆኑ” ተናግረዋል ። ከዚያ ይልቅ ተማሪዎቹ ደካማ ውጤት ያስመዘገቡባቸውን የትምህርት ዓይነቶች ለአንድ ዓመት በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንዲማሩ ተደርገው፤ የሚሰጣቸውን የመመዘኛ ፈተና የሚያልፉ ከሆነ የአንደኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ይጀምራሉ ።

የትምህርት ሚንስትሩ አሁን ለታየው የተማሪዎች የውጤት ማሽቆልቆል “ለዓመታት ሲንከባለል የቆየ የበርካታ ችግሮች መገለጫ እና ተሸፍኖ የቆየውን እውነተኛ የትምህርት ሥርዓት ያለበትን ደረጃ ያመለከተ ነው” ብለዋል ።ለዚህም ከመንግሥት እና ሁሉም የትምህርት ማኅበረሰቡ መሆኑን በመግለጽ፣ ለዚህ ችግር መፍትሄ ይሆን ዘንድ አጠቃላዩን የአገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ለመለወጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ለማዘጋጀት ዕቅድ እንዳለ ጠቁመዋል።

አበው ፣ ”ተምሮ የማይፅፍ ፣ አክፍሎ ማይገድፍ፤” የሚል ወርቅ ይትበህል ፤ ፍልስፍና አላቸው ። አዎ ! ተምሮ ... ተምሮ ... ካልፃፈ ፤ ካላነበበ ፤ ፈተና ካላለፈ ፣ በተጠየቅ ፣ በአመክንዮ ፣ በጥበብ ካልተጓዘ ፤ ካልተመላለሰ ፤ ማሰብ ማሰላሰል ከተሳነው ፤ ምኑን ተማረው ! ? ፊደል መቁጠሩ ፤ መማር መመራመሩ መና ቀረ ፤ ፉርሽ ሆነ ፤ ቀኑን ሙሉ ፆሞ ፣ አክፍሎ ማይገድፍ ፣ ፆም ማይፈታ ከሆነ ደግሞ የከፋ ነው ።

በመንፈሳዊ አውድ ካየነውም ፀሎቱ ፣ ልመናው ፤ አልሰመረም ፤ ወደሚል እሳቤ ይወስዳል ። የተማሪውም ፤ የአክፋዩም ቃል ኪዳን ፣ ውል በምክንያትና በውጤት የታሰረ ነው ። ከተማረ ፈተና በማለፍ / ከተማረ በመፃፍ ፤ ካከፈለ በመግደፍ ። ተማሪውም አጠቃላይ የትምህርት ማህበረሰብም ይሄን ቃል ኪዳን ባለመጠበቁ ከፍ ብሎ የተገለጸውን አሳፋሪ ውጤት አስመዝግቧል ።

ባለፉት 20 አመታት በብዙ መቶ ቢሊዮን ብር የሚገመት የሀገር የሕዝብ ሀብት በማፍሰስ ወደ ሀምሳ የሚጠጉ ዩኒቨርሲቲዎች ፤ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ የ1ኛና የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገንብተዋል ። ለመምህራን ስልጠና ፣ ለመፅሐፍ ሕትመት ፣ ለቤተ መፅሐፍትና ሙከራ ግንባታም ቀላል የማይባል የሀገር ሀብት ባክኗል ።

ከዚህ ሁሉ ጊዜ ፣ ድካምና ሀብት ብክነት በኃላ ግን ከ1ኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ በየደረጃው ካሉ የትምህርት ተቋማት የሚወጡ ተማሪዎች ፣ ሰልጣኞች መመዘኛው ፣ መስፈርቱ የሚጠይቀውን ያህል የማይፅፉ ፣ የማያነቡ ፣ የማያገናዝቡ፣ የማያንሰላስሉና የማያመዛዝኑ ናቸው ። የአንዳንድ ጥናቶች ግኝትም ይሄን ከማረጋገጥ አልፎ የሚያስደነግጥ ነው ።

ቢዘገይም የትምህርት ፍኖተ ካርታ ተነድፎ ፤ ስራዎች እዚህም እዚያም እየተሞካከሩ ይገኛል ። የችግሩን መነሻ ማወቅ የመፍትሔው አካል ነውና አንድ ሁለት ነጥቦችን ላነሳሳ ፤

የተደራሽነት ታሪክ ፡- ለሀገራችን ትምህርት ጥራት መውደቅ ግንባር ቀደም ምክንያት ጥራትን ወደ ጎን ገሸሽ አድርጎ ተደራሽነትን ብቻ የሙጥኝ ብሎ በፓለቲካ ቅኝት ሲመራ የኖረው የተንጋደደ የመንግስት የትምህርት ፓሊሲ ነው ። ትምህርትን ተደራሽ ከማድረጉ ጎን ለጎን ጥራት ላይ አለመሰራቱ ዛሬ በየደረጃው ለተከሰተው ሀገራዊ የትምህርት ጥራት ቀውስ ዋናው ምክንያት ነው።

መንግስት በማህበራዊ ሚዲያዎች የታዘብናቸውን የዛፍ ጥላ ፣ የጎጆና የሰቀላ እንዲሁም በየ"ቀበሌው ተሰሩ " የተባሉ ት/ቤቶችን እንዲሁም ተማሪዎቻቸውን እየቆጠረ በአኃዝ ሲዘናጋ ጥራቱን ለተደራሽነት መስዋዕት አድርጓል ። የጥራት ጉዳይ ከተደራሽነት ጎን ለጎን ሊሰራ ሲገባው ይሄን ያህል አመታት ችላ መባሉ ቀውሱን አባብሶታል ።

እንደ አንዳንድ የትምህርት ጥናት ጥቆማዎች ፤ የጥራት ጉዳይ ቢያንስ ከአስር አመታት በፊት ትኩረት ሊያገኝ ይገባ ነበር ። ሆኖም ዛሬ ከሁለት አስርት አመታት በኃላ የትምህርት ጥራት ጉዳይ ትኩረት ያገኘ ይመስላል ። ኩረጃን ባስቀረ አግባብ የተሰጠው የዩኒቨርሲቲ መግቢያና ሰሞኑን ይፋ የሆነው ውጤት፤ ከፈተና ውጤትነት በላይ የስርዓተ ትምህርቱ የሲቲ ስካን ምርመራ ውጤት አድርጌ ነው የወሰድኩት ። የበሽታውን ደረጃ ቁልጭ አድርጎ አሳይቶናልና ። ይሄን የሚያክም መድኀኒት መቀመም የሁላችንም ኃላፊነት ነው ።

2ኛ . የጥራት ጉዳይ ፡- የቁጥር ፣ ጨዋታ በራሱ የጥራት መለኪያ ፤ የጥራት መገለጫና ግብ ባይሆንም እንደ ጥራት መመዘኛ ተደርጎ ተወስዷል ።የትምህርት ጥራትን በተለይ የሚለካ ፣ የሚመዝን ሳይንሳዊ ስነ ዘዴ መሬት ላይ አልነበረም ። ቢኖርም በአግባቡ ስራ ላይ አልዋለም ነበር ። ወጥነት በጎደለውና በተዝረከረከ ሁኔታ አልፎ አልፎ ጥራትን ለማስጠበቅ የሚደረግ ጥረት ቢኖርም አልዘለቀም ።

አንድ ተማሪ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ለመዘዋወር ምን ማሟላት ፤ ምን ያህል ዕውቀት መገብየት እንደሚጠበቅበት የሚለካበት ፣ የሚመዝንበት ስልት አልነበረም ። ቢኖርም ስራ ላይ አልዋለም ። ምንም እንኳ የተማሪዎች የፈተናውጤት ከጥራት መስፈርቶች አንዱ ቢሆንም ፤ ተቋማዊ አስተዳደራዊ እየሆነ በመጣው ኩረጃ የተነሳ መመዘኛነቱ አፈር ድሜ በልቷል ።

ኩረጃው ሲቀር ውጤቱ ምን እንደሆነ ደግሞ ዘንድሮ በአይናችን በብረቱ አየነው ። ምክንያቱም ት/ቤቶች ይወዳደሩት የነበረው ባሳለፉት ተማሪ ብዛት እንጅ በሚሰጡት የትምህርት ጥራት ደረጃ ስላልሆነ ፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መምህራን ፣ የትምህርት አመራሩ ከፍ ሲልም የአስተዳደር አካሉ የተሳተፉበት የተደራጀና ተቋማዊ የሆነ ኩረጃ በተማሪዎች መካከል እንዲካሄድ ፤ ከፍ ሲልም መምህራን የፈተና መልስ ሰርቶ በማደል ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተማሪ በማሳለፍ ትምህርት ቤታቸውን ተሸላሚ ለማድረግ የሚካሄድ " ከንቱ ውድድር ! " ጥራቱን ይባስ ሲገድለው ኖሯል ።

በትምህርቱ ደከም ያለን ተማሪ ክፍል ማስደገም ሀብት እንደማባከን እና እንደመምህራን ድክመት ስለሚቆጠር መምህራን ተማሪዎችን ለማስደገም አይደፍሩም ። ተማሪ እንዲደግም ያደረጉ አንዳንድ" ደፋር... " መምህራንም እንደ ድክመት ተቆጥሮባቸው ይገመገሙ ነበር ። እንዲሸማቀቁም ተደርጓል ። ከፍ ሲልም በትምህርት አመራሩ ግፊትና አስገዳጅነት የደገሙ ተማሪዎችን እንዲያሳልፉ ይታዘዛሉ ፤ ይህን ትዕዛዝ የማይቀበሉ መምህራን ደግሞ ስራቸውን እንዲለቁ ጫና ይደረግባቸው ነበር ።

3ኛ . የትምህርት ነፃነት አለመኖር ፡- በሀገራችን በየደረጃው ለተፈጠረው የትምህርት ጥራት ማሽቆልቆል አንዱ ምክንያት በትምህርት ተቋማቱ የቀለም ትምህርት ነፃነት ስላልነበር

(violation of acadamic freedom ) ነው። የትምህርት ስራውን በነፃነት ከመምራት ይልቅ በየደረጃው ፓለቲካዊ ጣልቃ ገብነት ይስተዋልበት ነበር ። የትምህርት አስተዳደር አመራሩ ፣ ርዕሰ መምህሩ ፣ የፈረቃ መሪው ሳይቀር ፤ በየደረጃው የሚመደበው በብቃቱ ተወዳድሮ ሳይሆን በፓለቲካ ታማኝነቱ ነበር።

መምህራን በት/ቤቱ በነፃነት ሀሳባቸውን እንዲገልፁ፣ እንዲጠይቁ ፣ እንዲሞግቱ ምቹ ሁኔታ አለመኖሩ ፤ ተማሪዎች ስለትምህርታቸውም ሆነ ስለሀገራቸው በነፃነት እንዲመክሩ አለመፈቀዱ ፤ በትምህርት ስራ ማህበረሰቡ ላይ ተጭኖ የነበረው መዋቅራዊ አፈና መምህሩ ፣ የትምህርት ስራ አመራሩ ፣ ተማሪው የትምህርት ፓሊሲውንም ሆነ ፤ ስርአተ ትምህርቱን በነፃነት ከስር ከስር እንዲተች እንዲታረም ስለማይደረግ ችግሩ እየተሸፋፈነ እና በፈጠራ የአፈፃፀም ሪፓርት እየተኳኳለ ዛሬ ለደረስንበት ቀውስ ዳርጎናል ።

በተለይ ከ1997 ዓም ምርጫ ወዲህ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አካዳሚያዊ ነፃነት ሙሉ በሙሉ ተጨፍልቋል ማለት ይቻላል ። በነፃነት የመማር ማስተማር ፣ የምርምር ፣ የመሰብሰብ ፣ የመወያየት ፣ ነፃነት ከሌለበት ዩኒቨርሲቲ እንዴት ብቃት ፣ ጥራት ያለው ምሩቅ ማፍራት ይቻላል ?።

ብቁ መምህራን በሌሉበት ፣ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ዝግጁነት የሌለው ተማሪን ይዞ ፤ የመማሪያ መፅሐፍት የይዘት ጥራት ባልተሟላበት ፤ የትምህርት መሰረተ ልማት በአግባቡ ባልተሟሉበት ፤ የወላጅ ተሳትፎ ዝቅተኛ በሆነበት ፤ በተለያዩ ምክንያቶች የተከሰቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች መባባስ ፤ ለምሩቃን ምቹ የስራ ዕድል አለመመቻቸት የችግሩ በአንድ አካል ነው።

በዚህም ማህበረሰቡ ስለ ትምህርት የነበረው በጎ አመለካከት መሸርሸሩ ፤ በየደረጃው ለሕብረተሰቡ ምሳሌ ፣ አርኣያ ሊሆኑ የሚችሉ ዜጎች አለመፈጠራቸው ፤ ተምሮ ጥሮ ሳይሆን በአቋራጭ ዘርፎ መበልፀግ እንደ ጀግና የሚቆጠርበት ዘመን መፈጠሩ በአንድም በሌላ በኩል ለሀገራችን የትምህርት ጥራት ማሽቆልቆል ሌላኛው ምክንያት ነው ።

ከፍ ብሎ የትምህርት ሚንስትሩ እንዳሳሰቡት በሀገራችን የትምህርት ጥራት ላይ የተከሰተውን አሳሳቢ ቀውስ ለመቀልበስ ስር ነቀልና ከፓለቲካዊ ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ፤ መላ ሕዝቡን ያሳተፈ ሀገራዊና ሁሉን አካታች የትምህርት ዘርፍ መዋቅራዊ ክለሳ ሊካሄ ይገባል ።

ሻሎም ! አሜን ።

# ወቅታዊ



# «የፖለቲካው ገበያ ብልሽት አንዱ ውጤት እምነትን፣ ዘርን እና ሰፈርን መጠቀሚያ አድርጎ በንፁሃን ሰዎች ደም ወደ ስልጣን መምጣት መፈለግ ነው »

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

**(ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሰላምና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከትናንት በስቲያ የሰጡት ማብራሪያ ሙሉ ቃል)**

የሰላም ግንባታ አቲቲውድ ነው። ለሰላም የሚሰጥ ዋጋ ነው። የሰላም እሳቤ እንዲያድግ ዋነኛው መሠረታዊ ሥራ አቲቲውድ ላይ የሚሠራ ሥራ ነው። ሁለተኛው ሕግ ማስከበር ነው። የትኛውም ዓለም ሰላም በችሮታ፣ በፈቃድ የሚረጋገጥበት ምድር የለም፤ ቢኖር ኖሮ ሕግ አያስፈልግም፤ ፖሊስም አያስፈልግም። ሰላም በሕግ ነው የሚከበረው። ለአብዛኛው ሰው አቲቲውድ ግንባታ ያስፈልጋል። ከዚያ ወጣ ለሚለው ሰው የሕግ አስከባሪና ሕግ ያስፈልጋል። ሁለቱ ነገሮች ተጣጥመው መሄድ አለባቸው።

ሰላምን በሚመለከት ማስተማሩም፤ ሕግ ማስከበሩም። ሞር ጎልቶ የወጣው ከሃይማኖት ጉዳይ ጋር የሚያያዘው ስለሆነ የእኔ መረጃና ኦብዘርቬሽን፤ የሃይማኖት ተቋማት ከሦስት ነገር ቢጠበቁ ከብዙ ችግር ነፃ ይሆናሉ። አንደኛው ከፖለቲካ፤ ሃይማኖት ተቋም የፖለቲካ እሳቤዎች መሸከሚያ ቦታ ባይሆኑ፣ ሁለተኛ ሌብነት ዓለምን ያስቸገረው ሌብነት እነሱን ባያስቸግራቸው። ሦስተኛ ዘር የሃይማኖት ተቋማት ሁሉም ፖለቲካን፣ ሌብነትን እና ዘርን ከውስጣቸው ቢያጠፉ፤ ቢቀንሱ አብዛኛው ችግር ይፈታል። ይሄ ጉዳይ የአንድ ሃይማኖት ተቋም ችግር አይደለም። ሁሉም ጋር ዘር አለ፤ ሌብነት አለ፤ ፖለቲካ አለ።

ሌብነቱ ያስፈራል፤ ሲሰማ ያስደነግጣል። ሦስቱም አያስፈልጋቸውም የሚባለው ዋናው ምክንያት እነሱ አላማቸው ዘላለማዊ ነው። ኢንተርናል ነው። ፖለቲካ ጊዜያዊ ነው። የሌብነት ጥቅም ጊዜያዊ ነው። ዘር እዚሁ የሚቀር ነው። ከእነሱ እሳቤና አላማ ጋር አይሄድም። ሰማያዊውን መንግሥት የሚጠብቁና የሚገነቡ ወታደሮች ስለምድራዊው ቢጨነቁ የራሳቸውን ፍላጎትና ሀሳብ ስለሚቃረኑ ጥፋት ይመጣባቸዋል።

ይሄ ጉዳይ በኢትዮጵያ ውስጥ በተደጋጋሚ ታይቷል። በታየበት ጊዜ ሁሉ የታሪክ ስብራት የእድገት እንቅፋት የአብሮ መኖር ጉዳት ብቻ ነው የሆነው፤ ጥቅም አልነበረውም። አሁን በሰከነ መንገድ ማየት የሚያስፈልጉ ጉዳዮች አሉ። ሰሞኑን የጎላው የኦርቶዶክስ ጉዳይ ስለሆነ የኦርቶዶክስን ጉዳይ አነሳለሁ። ከጥቂት ወራት በፊት የሙስሊም ነበር። እንዴት መከራችንን እንዳየን ታስታውሳላችሁ።

የኦርቶዶክስን በሚመለከት ጉዳዩ በእኔ እይታ ቀላል ነው። በጣም ቀላል ነው። በእኔ እይታ ምድራዊነትን ማን አህሎኝነትን እኔነትን ከተተወ፤ ይፈታል ብዬ ነው ማስበው። ከባድ ነው ብዬ አላስብም። በታሪክ እንደምታውቁት የኃይለሥላሴ መንግሥት ወደ ኋላ አካባቢ ነው፤ የኢትዮጵያን ጳጳሳት በተለይ ፓትርያርክ መሾም የጀመረው። ቀደም ሲል ፓትርያርክ ከግብፅ ይመጣ ነበር። የመጨረሻው በንጉሡ ዘመን የመጨረሻው ፓትርያርክ ደርግ እንደመጣ ብዙም አብረው ሊጓዙ አልቻሉም። ጉዳዩ ብዙ ቢሆንም ለኃይለሥላሴ መንግሥት ቃለ መሃላ ፈፅመው ፓትርያርክ የሆኑት አባት፤ ከመጣው አዲስ መንግሥት ጋር መጓዝ ተቸግረዋል።

እሱን በጊዜው በዓይን ያዩ በጆሮ የሰሙ እማኞች በዝርዝር እንዲናገሩት የሚተው ቢሆንም፤ ደርግ ያደረገው ግን ፓትርያርኩን ገድሎ የራሱን ፓትርያርክ መሾም ነበር። ይህ የኢትዮጵያ የትናንትና ታሪክ ነው። ቀጥሎ ኢህአዴግ ሲመጣ በደርግ ጊዜ የነበሩት ፓትርያርክ ኢህአዴግ የሚባል መንግሥት ሲመጣ አብሮ መቀጠል መሥራት በብዙ ምክንያት ተቸገሩ። ኢህአዴግ ከደርግ ሻል ባለ መንገድ ግድያ ሳይፈጽም በደብዳቤ ከአገር አስወጣቸው። እኛ ስንመጣ ግድያውም ትክክል አይደለም፤ የራስ ፓትርያርክን ማሾምም ትክክል አይደለም፤ ከአገር ማወጣትም ትክክል አይደለም ብለን፤ ከአገር ውጭ የነበሩትንና በአገር ውስጥ ያሉትን ለማስታረቅና አንድ ለማድረግ ነው የሞከርነው።

አንዱ መሠረታዊ ልዩነት ይህ ነው። ይህ ተራ ጉዳይ አይደለም፤ በአንድ መንበር ሁለት ሊቃነጳጳሳት አይቀመጡም። በአንድ መንበር አንድ ጳጳስ ሊያውም እስከ ሕይወት ፍጻሜ ድረስ የሚል ቀኖና ሕግ ቢኖርም በሁለቱም አባቶች በጎ ፈቃድ፤ በእኛም ፍላጎትና ድጋፍ ያ ጉዳዩ ተፈትቶ ሁለት ቦታ ተከፍላ የነበረች ቤተክርስቲያን አንድ መሆን ችላለች። ይህ ለየትኛውም የእምነት አባል ኢትዮጵያዊ ክብር ነው። ለየትኛውም ዕምነት አባል ኢትዮጵያዊ መደረግ ያለበት ተግባር ነው። ኦርቶዶክስን ማፍረስ፤ ኦርቶዶክስን ማዳከም፤ ኦርቶዶክስን መጉዳት፤ ጉዳቱ ለኦርቶዶክስ ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም ነው። መከላከል፣ መጠበቅ፣ መደገፍና ማገዝ ያስፈልጋል።

ሁለተኛው ከመንበር በተጨማሪ የነበረው ጉዳይ በአሜሪካን አገር ተሾመው የነበሩ ጳጳሳት ኢትዮጵያ ውስጥ በሲኖዶስ ያልተሾሙ በመሆናቸውና ቁጥራቸው በርከት ያለ በመሆኑ ሲመለሱ እንዴት ይሆናሉ የሚል ጉዳይም ነበር። እነዚያ ጳጳሳት ምንም እንኳን በነበረው ሁኔታ አሜሪካን አገር ቢሾሙም አዲስ ከውጭ የመጡ ሰዎች ባይሆኑም ከጵጵስና በፊት ባሉት ደረጃዎች እዚያው ቤተክርስቲያን ውስጥ ያደጉ ናቸው። እነሱን እንደ ጳጳስ መቀበልና ሰላሙን ማምጣት ካለው ችግር አይብስም፤ መቀበል ይሻላል። የሚደገፍ ነገር ካለ እንደግፋለን በሚል እርቅ ተፈጸመ።

እርቅ ሲፈጸም ደርግ የወረሰው፤ ኢህአዴግ ያልሰጠው፤ ከ40 ዓመት በላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ንብረት የሆኑ አራት ኪሎ ያሉ ሁለት ትላልቅ ሕንፃዎች መንግሥት መልሶ ለኦርቶዶክስ ሰጥቷል። በሰላሙ ምክንያት፣ በአንድነቱ ምክንያት ኦርቶዶክስ ክብር እና ጥቅም እንጂ ጉዳት አታመጣም ብለን የገባነውን ቃል ለመፈጸም፤ የመጀመሪያ ሁለት ሕንፃዎች ከ40 ዓመት በላይ በመንግሥት እጅ የቆዩ ወስደዋል። ሁለተኛው መሬት ነው። አንዳንድ ሰዎች አሁን መንግሥት ኦርቶዶክስን እንደዚህ ያደርጋል፣ እንደዚያ ያደርጋል ሲሉ እሰማለሁ። ግን እንደኛ መንግሥት ኦርቶዶክስን በቅርበት የደገፈ ከንጉሡ ሥርዓት ውጪ ምንም መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም።

መሬት የክልሎችን ትቼ የአዲስ አበባን ብቻ ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ የነበረውን የመሬት ስጦታ ወይም የመሬት ክፍፍል ለማንሳት እሞክራለሁ። ካቶሊክ፣ ሙስሊም፣ ወንጌላዊያን ቃለሕይወትን ጨምሮ፣ መካነየሱስን ጨምሮ ሙሉ ወንጌልን ጨምሮ ትልልቆቹን ጨምሮ በጣም ብዙ ተከታይ ያላቸው ሰቨን አድቬንቲስትን ጨምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የእምነት ተቋማት በሙሉ ከኦርቶዶክስ ውጪ 350ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ወስደዋል። ሙስሊም፣ ካቶሊክ፣ ወንጌላዊያን፣ አድቬንቲስት ተደምረው 350ሺህ ገደማ ካሬ ሜትር መሬት በካርታ ባለፉት አራት ዓመታት ወስደዋል።

ኦርቶዶክስ አንድ ሚሊዮን 45 ሺህ ካሬ ሜትር ወስዳለች። ባለፉት አራት ዓመታት የሁሉ ሃይማኖቶች ተደምሮ ሦስት እጥፍ የሚሆን መሬት በካርታ ተሰጥቷታል። ባለፉት አራት ዓመታት አንድ ሚሊዮን 45 ሺህ ካሬ ሜትር ተሰጥቷታል። የእነዛም 350ሺህ ካሬ ሜትር፤ መንግሥት በአጠቃላይ የሃይማኖት ተቋማትን ይደግፋል፣ ታክስ አይቀበላቸውም፣ ሱቅ ሲከፍቱ ግብር አያስከፍላቸውም ብቻ ሳይሆን መሬት በነፃ፤ በስፋት በካርታ ያቀርብላቸዋል። በሊዝ አይደለም። ለምንድን ነው ያን የሚያደርገው። ተቋማቱ ለአገር በጣም አስፈላጊ ስለሆኑ ነው። ተቋማቱ ቅድም ካልኩት ከዘር፣ ከፖለቲካ ከሌብነት የጸዱ ሆነው ዜጎችን በዚያ መንገድ ቢያንጹ ጠቃሚ ስለሆነ ነው።

የላሊበላ ቤተክርስቲያን ሁላችሁም እንደምታውቁት ልክ እንደ ግድቡ ወይም እንደ ሆነ ልማት፤ የኢትዮጵያ ቅርስ ሀብት ነው ተብሎ በነበረን ቅርርብ ከፕሬዚዳንት ማክሮን ጋር ጥያቄ አቅርበን እርሳቸውም ተስማምተው ለማገዝ ተስማምተው በዩኔስኮ ምክንያት ሰፊ ጊዜ የወሰደ ቢሆንም፤ ድጋፍ አግኝተን ቤተክርስቲያኑን የማደስ ሥራ በቅርቡ ይጀመራል። ይህ በቀጥታ የመንግሥት ጉዳይ ስለሆነ ሳይሆን ቅርስነቱ ተቋሙ አስፈላጊና መደገፍ ያለበት ነው ከሚል እምነት የመጣ ነው።

በአረቡ ዓለም እስከ አሁን ድረስ በተለይም ዩኤ ኦርቶዶክሱም ጴንጤውም በየአዳራሹ በሰዓት እየተከራየ አምልኮውን ከመፈጸም ውጪ የራሱ የሆነ ይዞታ የለውም። የአቡዳቢን መንግሥት ለምነን በጣም ሰፊ ቦታ፤ ስድስት አምስት ሄክታር የሚያህል ቦታ፤ ቦታውን ሰጥቶን ኦርቶዶክስ ይዞታውን ይዞ፤ ለግንባታ ሀብት ለማፈላለግ ጥረት እያደረገች ነው። እርሱንም ማገዝ ያስፈልጋል። ማገዝ አለብን ቅርስ ነው፤ የሁላችንም ቅርስ ነው። የእዛ እምነት ተከታይ መሆን አለመሆን አይፈልግም ቅርስ ነው።

በአረቡ ዓለም ቤተክርስቲያን እንዲኖር ቀድሞ የነበረው ላሊበላ እንዲታደስ፣ የተወረሰ ሕንፃ እንዲመለስ፣ መሬት በስፋት እንዲሰጥ፤ ሁለቱ ሲኖዶሶች እንዲታረቁ ሌሎች አሁን የማልዘረዝራቸውን ድጋፎች ሁሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ሲያደርግ የነበረው የተቋሙን አስፈላጊነት ከልብ ስለሚያምን ነው።

አሁን ደርሶ ሰው ኦርቶዶክስን አልፈለጋችሁም፤ አልደገፋችሁም፤ በማለት የፖለቲካ አጀንዳ ማድረግ አይችልም። በየትኛውም የታሪክ መዝገብ ቢያገላብጥ የብልጽግናን ያህል ሃይማኖት ተቋማትን የደገፈ አብሮ የቆመ መንግሥት ሊያገኝ አይችልም፤ የንጉሦቹ ሌላ ጉዳይ ነው።

በዚህ ምክንያት ተቋሙን እንፈልገዋለን በዚህ ምክንያት ተቋሙን ደግፈነዋል፤ በዚህ ምክንያት ምንም ቅሬታ የለንም፤ ብናደርግ ኖሮ የሚል ቁጭት የለብንም። ሰሞኑን ያጋጠመው ምንድን ነው፤ ከሁለት ወይም ሦስት ዓመት በፊት ሊሆን ይችላል፤ ጊዜውን እርግጠኛ አይደለሁም፤ በኦሮምኛ ቋንቋ ኦሮሚያ ውስጥ መገልገል ባለመቻላችን ብዙ ምዕመን፤ ብዙ አገልጋይ፤ ወደ ሌላ እምነት እየፈለሰ ስለሆነ በቋንቋችን ማገልገል የሚችሉ ሰዎች ይሾሙ የሚል እንቅስቃሴ ነበር። ጥያቄም ይነሳል እንቅስቃሴም ነበር። ምን አደረግን እኛ፤ ይህ ጉዳይ ጥሩ አይደለም በሰከነ መንገድ ተመካከሩ፤ የሚገሰጽ ካለ ገስጹ የሚሾም ካለ ሹሙ፤ የሚመከር ካለ ምከሩ፤ በቤታችሁ ፍቱ አልን። እነሱም እግዚአብሔር ይስጣቸው፤ ቁጭ ብለው ተነጋግረው ተመካክረው አስተካሉት፤ ያ ነገር ጠፋ።

ለዓመት ሁለት ዓመትም የሚሆንም ቢሆን ብዙ ኢሹ አልነበረም። አሁን ተመልሶ ኢሹ ሆነ። አሿሿም ላይ አድልዎ አለ። በአፍ መፍቻ ቋንቋችን ሕገ መንግሥታዊ መብታችን በብዙ ትግል ያገኘነው መብታችን ኤክሰርሳይስ እንዳይደረግ ጫና አለብን፤ የሚል ጥያቄዎች መጡ። ምን አደረግን እኛ የመንግሥት ኃላፊዎች ወክለን ላክን። እባካችሁን አታጋግሉት፤ ቀስ ብሎ በሰከነ መንገድ በምክክር ፍቱት፤ በውይይት ፍቱት ምክንያቱም ጉዳዩ እንዲህ በቀላሉ የሚቋጭ ነገር አይደለም። ቤተክርስቲያን ግን አባቶችን አስቀምጣ ገስጻ መክራ ችግር ካለባትም አርቃ አርማ ብትፈታው የኛ መሻት ፍላጎታችን ነው፤ ብለን ችግሩ በአጋጠመ ሰሞን መጀመሪያ በመንግሥት ምክር ለግሰናል። ምክራችን አልተደመጠም፤ አልተተገበረም። እኛ ማዘዝ አንችልም መምከር ነው የምንችለው። መፍትሔው ተቀራርቦ መነጋገር ነው።

ኦሮሚያ ውስጥ በኦሮምኛ ቋንቋ አገልግሎት ይሰጠኝ ብሎ የሚጠይቅን ምዕመን አይሰጥህም ልለው አልችልም። እኔ አይደለሁም ለኦሮሞ በቋንቋው የመጠቀም መብትን ያጎናጸፍኩት። ያ መብቱ ጋር መቃረን ሳይሆን፤ መፋረስ ሳይመጣ፤ መለያየት ሳይመጣ፤ በንግግርና በምክክር በጊዜ ሂደት ኦቨርናይት ላይሆን ይችላል፤ በጊዜ ሂደት መልክ እያበጁ መሄድ ነው። ለምሳሌ በድፍን ኦሮሚያ አሁኑኑ 100 ሰው ተሹሞ ላይባል ይችላል። ቀስ እያሉ የምዕመኑን ፍላጎት ደረጃ በደረጃ እየመለሱ፤ የቋንቋ፣ የዘር፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ ምናምን ጉዳይ ትልቁን ተቋም እንዳያፈርስ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ጥያቄው በትግራይ ክልል ያሉ ምዕመናን በቋንቋቸው ይገለገላሉ። በትግራይ ክልል ያሉ አባቶች በቋንቋቸው ያስተምራሉ ብቻ ሳይሆን ከዓመት ሁለት ዓመት በፊት የትግራይ ክልል በቃ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ወጥቻለሁ፤ ሲል አንድ ሰው እንኳን ኧረ ባካችሁ አይደረግም አላለም። እንኳን መግለጫ እንኳን ይሄ ሁሉ ግርግር አንድ ሰው እንኳን ለምን ይደረጋል፤ እኛ ከፖለቲካ ነፃ ነን፤ እኛ አብረን የኖርን ነን፤ ብሎ ለመምከር እንኳን ጥረት አላደረግንም። ለምን አሁን የሚል ጥያቄ ይነሳል።

በአማራ ክልል ሰው የሚገለገለው በአማርኛ ነው። በራሱ ቋንቋ፤ ለምን ደቡብና ኦሮሚያ ሲሆን እንደዛ አይደለም፤ የሚል ጥያቄ ይነሳል። ይሄንን መንግሥት በማዳፈን ማለፍ አይችልም። ቁጭ ብሎ በሰከነ መንገድ ተነጋግሮ፣ ተመካክሮ፣ የምእመኑን የሕዝቡን ፍላጎት መመለስ ነው። ምክንያቱም ምእመኑ ሁሉም የኦርቶዶክስ ልጆች ናቸው። ሰሜንም ይሁን፣ ምዕራብም ይሁን፣ ምሥራቅም ይሁን ሁሉም የኦርቶዶክስ ልጆች ናቸው። ቋንቋው ምንም ይሁን በዛች ቤተክርስቲያን ጥላ ስር እስካለ ድረስ፤ ሥርዓቷን፣ ዶግማዋን እስከተቀበለ ድረስ በቃ እሷ እናት ናት። እነሱም ልጆች ናቸው። ለልጆች የሚያስፈልገውን በሕግ አግባብ መምከር ያስፈልጋል።

የመጨረሻ ምክሬ ግን ለሁሉም አባቶች ሁላችሁም የሃይማኖት አባቶች እንደ አባ ማቲያስ ሁኑልን የሚል ነው። ፓትርያርኩ ሁለቱን አባቶች በምናስታርቅበት ጊዜ የወሰዱት በጣም ብልህ የሆነ አቋም ቤተክርስቲያኒቱን ታድጓታል። ወንበሩ ላይ እኔ አለሁበት። ተጨማሪ ሌላ ሰው አይገባም ቢሉ፤ አናስታርቅም ነበር። ችግር የለውም፤ ይምጡ ስላሉ ነው መታረቅ የቻሉት። በመተው፣ በመሸነፍ። የነበረውን ጥላቻ፣ የነበረው ንግግር ሳይሆን በማቀፍ፤ ማቀፍ ስለሚሻል።

አሁንም መገፋፋቱ ምንም ትርጉም የለውም፤

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ጥቅም የለውም። ኢትዮጵያን ይጎዳል። የኢትዮጵያ መንግሥት ይጎዳል። ኦርቶዶክስን ይጎዳል። ጥቅም የለውም። በሰከነ መንገድ ቁጭ ብሎ፣ ተነጋግሮ፣ ተመካክሮ፣ የጎደለ ካለ ሞልተው፤ የሚስተካከል ካለ አስተካክለው፤ እሚታረቅ ካለ አርቀው፤ እሚመከር ካለ መክረው፤ የነበረውን ነገር ማስተካከል ነው የሚሻለው። ምድር ምድር መሸተት ሳይሆን ሰማያዊ ሽታ ነው የሚያስፈልገው።

ምንድን ነው አሁን ይሄ? የግል ክብር አይደለም ይሔ፣ ለእምነት ነው፤ የሚሠራው ለእግዚአብሔር ነው። ለግል ጥቅም፣ ለግል ክብር … አይደለም። ለስልጣን አይደለም። ምንም ፍጅት አያስፈልገውም። ምንም ዘር፤ ምንም ፖለቲካ አያስፈልገውም። እኛ እምንጣላው ለወንበር፣ ለስልጣን ነው። ፖለቲካው ሌላ ትርጉም ነው ያለው። እዚህ ጋር የሚያስፈልገው እንደ አባት ሆኖ፤ እልህ፣ እስኪ አሳይሀለሁ፣ አሳይሻለሁ ተትቶ፣ በሰከነ መንገድ በመወያየት ተነጋግረው ቢፈቱ፤ መንግሥት ለእነርሱ አንድነት፣ ለእነሱ ሰላም፣ ለእነሱ ምክክር ሲያደርግ እንደነበረው ሁሉ አሁንም ከሚጠበቀው በላይ ያደርጋል። ግን መንግሥትን እኔን ካልደገፍከኝ አልሠራህም። ያንን ካልደገፍከው አልሠራህም የሚባል ከሆነ ብዙም ጥቅም የለውም።

ታስታውሱ እንደሆነ ይህ ችግር በሙስሊሞችም አጋጥሞናል። በብዙ ልመናና ምክክር በውስጥ ውይይት እንዲፈቱ ነው ያደረግነው። አሁንም ያለን አቋም አንድ ነው። በተለየ የምንደግፈው በተለየ የምንቃወመው ኃይል የለም። ሁለቱም ኃይሎች ኦርቶዶክሶች ናቸው። ሁለቱም ጋር ጥያቄዎችና እውነቶች አሉ። አንዱ ጋር ብቻ አይደለም ያለው ሁለቱም ጋር አለ። የሕዝብን መብት የሕዝብን በራስ ቋንቋ የመጠቀም ፍላጎት ሳያፍኑ፤ መፍታት ይቻላል። ያንን ካደረጉ፤ ለእነሱም ለእኛም እንደ አገር ጠቃሚ ነው። ከዚያ ውጪ ያለው አማራጭ ብዙም ጠቃሚ አይደለም። ብዙ እጃቸውን የሚያስገቡ ኃይሎች አሉ፤ ብዙ ናቸው።

እዚህ ያላችሁ የካቢኔ አባላት አንዳችሁም፤ እጃችሁን ማስገባት አይፈቀድላችሁም። አንድ ሰው እጁን እንዳያስገባ በዚህ ጉዳይ። እንደ ተቋም ከመንግሥት ጋር ተጋግዘን አንድነታችንን እንጠብቃለን፤ ካሉና መንግሥት የሚያደርገው ነገር ካለ፤ በጣም ዝግጁ ነን። በተናጠል ግን በዘር እየደወልክ፤ በሰፈር እየደወልክ በምናምን እየደወልክ የሚደረግ ጨዋታ፤ ኢትዮጵያን ስለማይጠቅም፤ ስለሚጎዳም እኛም እጃችንን እንሰበስባለን፤ ለእነርሱም ማዘዝ ባንችል ምክራችን እንደ አባ ማቲያስ ሆናችሁ ትታችሁ፤ ተመካክራችሁ ችግራችሁን ብትፈቱ አንድ ብትሆኑ ይሻላል።

አንድ ባይሆኑስ፤ ሁለቱም ቡድኖች ይጎዳሉ። የሚያተርፍ ቡድን የለም በዚህ። አብሮ ለብዙ ዘመናት የኖረ ሰው፤ ችግሩን ተነጋግሮ ፈትቶ፤ ተጠናክሮ መቀጠል ሲገባው መነጋገር ባለመፈለግና በእልህ ቢበተን ሁለቱም ተጎጂ ነው፤ ጥቅም የለውም። ወደዚያ እንዳይሄድ የእኛ ፍላጎት በምክክር በንግግር ችግራቸውን ፈትተው እንዲቀጥሉ ነው።

እንደ መንግሥት ግን የትኛውም መንግሥት አድርጎ የማያውቃቸውን ድጋፎች አድርገናል። እንደ መንግሥት ግን ጣልቃ ገብተን በየትኛውም ሃይማኖት ተቋም ውስጥ እንትናን መሾም አለብህ፤ እንትናን መጣል አለብህ አንልም። እናውቃለን አባቶችም ያውቃሉ፤ በነበሩ ሹመቶች ውስጥ መንግሥት ሳያዝ የሚሾም ሰው አልነበረም። ስም ተሰጥቶ መንግሥት የሚፈልጋቸው ሰዎች ይሾሙ ነበር፤ እኛ ሹመት ውስጥ አንገባም። የእኛ የምንለው አባትም የለም። ሁሉም አባት አባታችን ነው። በጋራ ሆነው እንዲቀጥሉ ነው የምንፈልገው። ከዚህ ውጪ ይሄን ነገር ከኮርሱ ውጪ፤ ከትራኩ ውጪ በጣም በማራገብ የሚወሰደው ጉዳይ አሸናፊ አልቦ ሙግት ስለሆነ ጥሩ አይደለም። ወደ ውጤትም አያመጣም፤ በዚህ አግባብ በሰከነ መንገድ በምክክር መታየት ይኖርበታል።

አጠቃላይ ሰላምን በሚመለከት ያለው እሳቤ ኢትዮጵያ ውስጥ ትንሽ ችግር አለበት። ችግሩ ምንድ ነው፤ አጀንዳ በመፍጠር ሰው እንዲጋደል በማድረግ ያንን በሶሻል ሚዲያ ላይ በጣም በማራገብ መንግሥትን እንጥላለን፤ መንግሥትን እናዳክማለን የሚሉ ሰዎች በስፋት ይጠቀሙበታል። የፖለቲካው ገበያ ብልሽት አንዱ ውጤት እምነትን ዘርን ሰፈርን መጠቀሚያ አድርጎ በሰዎች በንፁሃን ሰዎች ደም ወደ ስልጣን መምጣት መፈለግ ነው።

ይሄን በሌላ መድረክ አንስቼዋለሁ፤ ዛሬ እደግመዋለሁ፤ የደርግ መንግሥት የንጉሡን ሥርዓት የጣለው በኩዴታ ነው። ወታደሮች ተደራጅተው ሥርዓት ጥለው መንግሥት ሆነዋል፤ ከዚያ በኋላ በኩዴታ የመንግሥቱን ሥርዓት እንጥላለን ብለው የመጡ ግሩፖች ሁለት ሦስቴ ተበልተዋል። ምክንያቱም የመንግሥቱ የመጀመሪያው ትልቁ ብቃት ኩዴታ ነው። በሚያውቀው ነገር ልትቀይረው አትችልም። አዲስ መንገድ ያስፈልጋል፡ በራሱ በመጣበት መንገድ መጥተው ተበሉ ብዙዎች፤ መጥፋት የሌለባቸው ሰዎች ጠፉ። ኢህአዴግ ከመጣ በኋላ ያው ታውቃላችሁ በሽምቅ ውጊያ ነው የመጣው ኢህአዴግ፤ ከመጣ በኋላ እነ ፕሮፌሰር ብርሃኑ፣ እነ አቶ ቀጀላ በሽምቅ ኢህአዴግን እንጥላለን ብለው እዛው ቀሩ። ምክንያቱም ኢህአዴግ የመጣበት መንገድ ስለሆነ በዚያ መንገድ ኢህአዴግን ማሸነፍ አይቻልም።

ወደ እኛ ደግሞ ሲመጣ ብዙ፤ ሙከራዎች ይታያሉ፤ አሁን በከተማ ውስጥ ግርግር፤ በብልፅግና ውስጥ ሁለት ሦስት ሰው በመቅጠር፤ ይሄ መንግሥት መቼም አይፈርስም። That I can assure you. እንዴት እንደሚሰራ እናውቀዋለን፣ እንዴት እንደሚረበሽ እናውቀዋለን፤ በዚያ መንገድ የሚያስብ ሰው ካለ፤ እራሱን ይበላ እንደሆን እንጂ ለእኛ ችግር የለውም። ይሄ ነው አደገኛው ፖለቲካ ኢትዮጵያ ውስጥ፤ አዲስ ሃሳብ አዲስ መንገድ ይዞ መጥቶ ነገር ከመለወጥ ይልቅ፤ መንግሥት ሥራ እንዳይሠራ በየቦታው አጀንዳ እየፈጠርክ እያጋደልክ። አንዳንዴ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ወላይታ ሲዳማ ሊሆን ይችላል። አንዳንዴ ግን ወለጋ ሸዋ ሊሆን ይችላል፤ ጎንደር ጎጃም ሊሆን ይችላል። ማቆሚያ የለውም በየሰፈሩ ነው።

አንዳንዴ ኦርቶዶክስና ጴንጤ ይሆናል፤ አንዳንዴ ኦርቶዶክስ በራሱ ይሆናል፤ እንዳንዴ ጴንጤ በራሱ ይሆናል፡ ያው እንደምታዩት ነው። በየቦታው ይሞከራል እና ይሄ ነገር አያዋጣም። አገር ከማፍረስ ሰው ከማበጣበጥ የንፁሃን ደም ከማፍሰስ መጠበቅ ያስፈልጋል። ጉዳዮቻችን በፖለቲካ ንግግር እንጂ በዚያ በመሰለ መንገድ ፍላጎታችንን ማሳካት ብዙም የሚያዋጣ ስላልሆነ ማሰብ ጥሩ ነው። በየጊዜው ጥርጣሬ መዝራት እኩልነት እንደሌለ ማሳየት፤ የውሸት አጀንዳ እየፈጠሩ ሰው ውስጥ መጨመር፤ ይሄ የተለመደው ነው። እያንዳንዱ በፋክት በማጣራት አብዛኛው የሚፈጠሩ አጀንዳዎች ውሸት መሆናቸውን ያው ታውቃላችሁ፤ ሁልጊዜ ስለምንወያይበት አብዛኛው በዚያ መንገድ መሄድ አደገኛ ነው። ለእኛም ለእነሱም ለሁሉም ኢትዮጵያን ለሚፈልግ ኃይል።

ይሄንን የሚያራግቡ ሰዎች ቅጥረኞች መሆናቸውን የማናውቅ ይመስላቸዋል። በብዙ መንገድ ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚፈልጉ ኃይሎች ብዙ ዓይነት ሙከራ ያደርጋሉ። ከሙከራ ውስጥ አንዱ እንደዚህ ዓይነት ያለመተማመን እና አብሮ ያለመቆምን ሃሳብ ደጋግሞ እንዲነገር ማድረግ ነው። ሚዲያዎችም ቢያስቡበት ጥሩ ይሆናል። በእኛ በኩል ሕዝብ እናወያያለን፤ ያሉ እውነታዎችና ዳታዎችን ለሕዝብ እንገልፃለን፤ በአሠራር ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጉዳዮች ካሉ አሠራሮች እናስተካክላለን። ለምሳሌ በቅጥር በሹመት ኢሹ የሚነሳ ከሆነ ሕግ እናወጣለን፤ ምንም ችግር የለውም፤ ሁሉም ሰው እኩል የሚጠቀምባቸውን አሠራሮች እንከተላለን።

ሚዲያን በሚመለከት የመጀመሪያው ሥራ እናስተምራለን፣ እንመክራለን፣ እንገስፃለን። ሁለተኛ ሥራ በሕግ አግባብ እንጠይቃለን። ሚዲያ ነኝ፤ ማለት ሕዝብን ከሕዝብ እምነትን ከእምነት ማባላት የሚፈቀድበት አይደለም። ያንን ለማድረግ ደግሞ አቅም አለን። ያን ለማድረግ የሚያስችል አቅም አለን እንደመንግሥት። አቅሙን መመንዘር አላስፈለገንም ብለን ተውነው እንጂ ያን ለማስፈፀም የሚያስችል በቂ አቅም አለን። ስለዚህ የሚዲያ ተቋማት በኃላፊነት በሕግ አግባብ መሥራታቸውን ማረጋገጥ ጠቃሚ ይሆናል።

ሕግ አስከባሪ አካላት እስካሁን አብዛኛውን ነገር በትዕግስት እንዳላዩ እንዲያልፉ የሚፈለግበት ምክንያት በሕግ አስከባሪ አካላትና በዜጎች መካከል የነበረው ዓይነት ቅራኔ እንዳይቀጥል ነው። ትርፍ ነገር ማድረግ አያስፈልግም፤ በሕግ አግባብ ግን ሰዎች የሚጠየቁበትን መንገድና ሕግ የሚከበርበትን



መንገድ፤ መከተል ያስፈልጋል። እንደው ዝም ብሎ ባላፊ አግዳሚ እንደፈለጉ ተሳድቦ እንደፈለጉ ብሎ መቀጠል አይቻልም። እኔም ትርፍ በሆነ መንገድ ያኛውን መሳደብ የለብኝም፤ ያኛውም ያኛውን መሳደብ የለበትም። ተከባብረን ተደማምጠን በጋራ መኖር ያስፈልጋል። የፕሮክሲ ዋር መሣሪያ እንዳትሆን አገር ትብብርን ማጉላትና ፉክክርን መቀነስ ያስፈልጋል፤ ፉክክር የበዛበት ነገር ኃይለኛ ነው።

ሁሉም ነገር ፉክክር ከሆነ ጥፋት ያመጣል። አብዛኛው ሰው ውስጥ ኃይለኛ ቁጣ ይቀጣጠላል። ቁጣን ሰርፐረስ ማድረግ ያስፈልጋል። የምትቆጣበትን ምክንያት ማወቅ ያስፈልጋል። ዝም ብሎ ከፌስቡክም ከምንም አይቶ ከመቆጣት ፤ ቁጣን ሰርፐረስ ማድረግ ያስፈልጋል። ቁጣ እንደኛ ደግሞ ኮኸሲቭ ፓወር ያለው ሲቆጣ ጥፋቱ እና ዳይሜንሽኑ ከፍተኛ ይሆናል። ቁጣን ማኔጅ እና ኮንትሮል ማድረግ ያስፈልጋል። በጠመንጃ ኃይል ስልጣንንና ፍላጎትን ማሳካት አይቻልም። በተደጋጋሚ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ግድያ እንፈፅማለን እያሉ ከአንዳንድ ኃይሎች ጋር እየተቀናጁ የሚገቡ ቀላል ቁጥር የሌላቸው ሰዎች አሉ። እያደንን ስለምንይዛቸው ነው። አሁን በቅርቡ እንዲህ ዓይነት ሙከራዎች አሉ። ሰው ገድለን የሚሉ አሉ።

ሰው መግደል ኢህሃፓ ደርግ ላይ ሞከረው፤ አልሠራም። የእኛ ግን ይብሳል። ጥሩ ስለማይሆን አስር ጊዜ ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል። ሰው ገድዬ፣ ሰው አሸማቅቄ፣ ዋሽቼ፣ ቀጥፌ የሚባል ቀርቶ፤ ሃሳብ ይጌ በሃሳብ አሳምኜ ይሔን መንግሥት ልቀይር እችላለሁ ሊባል ይችላል። ለስልጣን ላለን ፍላጎት ሲባል ሰው እየበላን መሔድ ትክክል አይደለም። እንደማህበረሰብም ሰው ጠባሳውን አጠፋለሁ ብሎ ቆዳውን አይፍቅም። ጠባሳዎች እዛም እዛም አሉ። ጠባሳን ለመደበቅ፤ ጠባሳን ለማጥፋት ጠባሳን የሚልጥ ሰው ይበልጥ ጠባሳን ያመጣል እንጂ፤ ከነበረው ቁስል አይድንም። ብዙ በሽታ ያለበት ብዙ ቁስል ያለበት አገር፤ ተጨማሪ በጥልቀት እየቆፈሩ ቁስል ማብዛት ጥፋት ነው የሚያመጣው። እኛ እንደመንግሥት እሳትን በእሳት፤ ውሃን በውሃ ማጥፋት የሚል ፕሪንሲፕልን ብቻ አንከተልም።

አንዳንዴ እሳትን እያዩ መሸሽ፤ አንዳንዴ ውሃን እያዩ ከፍታ ቦታ መያዝ፤ አንዳንዴ ውሃን መገደብ፤ አንዳንዴ እሳትን ውሃ አንዳንዴ እሳትን አፈር ማልበስ ያጠፋው ይሆናል። አማራጮችን ጉዳት ለመቀነስ መጠቀም አለብን ብለን እናስባለን። እሳትን በእሳት፤ ውሃን በውሃ በሚባል እሳቤ የሚኬድ ከሆነ ጥፋቱ ብዙ ይሆናል፤ ለዛ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ በቂ ልምድ አለ። ስለሰላም ያለን ግንዛቤ አናሳ የሚሆንበት ምክንያት ችግርን የምናውቀው በፌስ ቡክ ነው። ጦርነትን በዩቲዩብ ነው የምናወቀው፤ ቀረብ ብለን አደጋውን ለማየት ዕድል አላገኘንም። የአንዲት ጠብታ ውሃ ዋጋዋ የሚገባው በረሃ ውስጥ የውሃ ሽታ የናፈቀው ሰው ነው። በርሃ ውስጥ የሚንከራተት ወታደር ነው። የሚንከራተት ረዥም ርቀት የሚጓዝ ነጋዴ ነው። ውሃ አጥቶ ጠብታ ውሃ እንኳ ቢያገኝ ቫልዩ አለው። ሲፈስ ለምናይ ሰዎች ብዙም ቦታ የለውም።

የሞትን አስከፊነት የሚረዱ ሰዎች በሰላም አብረው እየተጓዙ ጓደኛቸው ከጎናቸው ሲቀር ያዩ ሰዎች ናቸው። የሞትን አስከፊ ሁኔታ የሚረዱ ሰዎች ወንድማቸው፣ እህታቸው ሞቶባቸው ለመቅበር እንኳን የሚያግዛቸው ሰው ያጡ፤ የሰው ያለህ፣ ሰው ሞቶብኝ ለመቅበር አልቻልኩም የሚሉ ሰዎች ናቸው። አብረው እየተጓዙ ወንድማቸው ከጎናቸው ወድቆ አፈር ለማልበስ እንኳን ያልቻሉ ሰዎች የሞትን ክፋት ያውቁታል። አሁን በፌስቡክ ለምናይ ሰዎች ግን ቀላል ነው። ከእቤታችን ሲመጣ ግን ከባድ ነው።

የሰላምን ዋጋን በእጅጉ ተገንዝበን፤ ለሰላም የማንሰራ ከሆነ፣ ሁሉም ኃይል ለጥፋት የሚሆን ጉልበት ስላለው ለልማት የሚሆን የለውም እንጂ ለጥፋት ስላለው፣ መጠፋፋት ይሆናል። ይህ እንዳያጋጥም በተቻለ አቅም እኛ እንደመንግሥት በትዕግስት፣ ሁሉንም በማድመጥ፣ ሁሉንም በማቀራረብ፣ ተረጋግቶና አሁን ካለበት ችግር እና የእሳቤ ብልሽት ወጥቶ ወደ ተሻለ ጉዳይ እንዲያመራ ጥረት እናደርጋለን።

አቅማችን በፈቀደ መጠን ለሁሉም በእኩል አደራ እንዳለበት መንግሥት እናገለግላለን። እያንዳንዱ ግሩፕ ይህን ተገንዝቦ መሄድ አለበት። ሲፈልግ መንግሥትን የሚያቀርብ፤ ሲፈልግ የሚገፋ ሳይሆን ሁሉም ሥራ፣ ድርሻ እንዳለበት ተደጋግፎና ተጋግዞ መሄድ እንዳለበት የሚታመን ከሆነ አብዛኛው ችግር ይፈታል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የገጠሙን ፈተናዎች ችግር ቢመስሉም ተምረንበት፣ በስለንበትና ልምድ አግኝተንበት እንደአገር እንድንወጣ ዕድል ያመጡ ናቸው። አሁንም ያሉ ፈተናዎች ተመሳሳይ ናቸው። እያንዳንዱን ፈተና ቆም ብለን ራሳችንን እናይበታለን፤ ችግራችንን እንፈትሽበታለን፤ መውጫ መንገድ እናይበታለን፤ እናድግበታለን። እኛ ዓላማችን እስከ መጨረሻው ማደግ ነው። መቆም አይደለም። በየቀኑ እንመረምራለን፤ በየቀኑ እንማራለን፤ በየቀኑ እንጠይቃለን። በዚያ ውስጥ የሚገኝ እውቀት ካለ እንቀጥላለን እንጂ ቆመን፤ በተገኘ ድል የምንኩራራ፤ ባጋጠመ ችግር የምንፈራ ሰዎች አይደለም።

ያ! ቢሆን እዚህ እንዴት እንደርሳለን። ችግርም ድልም አያቆመንም። ከድላችንም ከችግራችንም እንማራለን፤ እናርቃለን እንመረምራለን እንገሰግሳለን። በዚህ አግባብ ነው የምንሄደው። ከውስጥ ንፅህና ከሌለ፤ ከውስጥ የሃሳብ ችግር ካለ ብዙ ጉዳይ ይበላሻል። በመሆኑም አብዛኞች በአጠረ መንገድ፤ ጉጉትና ፍላጎት አለ። መሻት ጥሩ ነው። ለመሻት ግን ፕሮፐር የሆነ ዕቅድ ከዛ ደግሞ ግን ሥራ ይጠይቃል። በአንዴ ጊዜ ሰውና ሰው አጋጭተህ አጋድለህ አይሆንም። ከፍተኛ ማስ ቤዝ ያለው ዓቅም እየፈጠረ ያለ ኃይል ነው። እና በዚህ መንገድ እያሰቡ ያሉ ኃይሎች በሰከነ መንገድ ማሰብ ይገባል። በምክክርና በንግግር ማድረግ ይገባል።

የጀመርናትን የዴሞክራሲ ጭላንጭል አብሮ ማስፋት ነው ጥሩ። አሁን እኮ ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ ዶክተር በለጠ፤ አቶ ቀጀላ አሉ። በቀጣይ 10 እና 15 ሰው ሊኖር ይችላል። ይህ ጥሩ ልምድ ነው። የአገርን ኢኮኖሚ፤ የአገርን ሠላም በጋራ የምናይበት አውድ ፈጥረን ካየንና አብሮ መምራትን ከተለማመድንና ከሄድን ቀላል ነገር ነው። በእርግጠኝነት አቶ ቀጀላ እና ዶክተር በለጠ ይህ ነገር ተፈጥሮ አብሮ ከመስራታችሁ በፊት አብን እና ኦነግ ሲባል የምታስቡትን ነገር አስቡት። ሰው ሲቀራረብ፤ ሲነጋገር፣ በንግግር ሲያምን፤ ሃሳብ ሲለዋወጥ ብዙ ነገር ይማማራል። ለንግግር በር መክፈት አለብን። ሁል ጊዜ ለግጭት መሆን የለበትም። ለይቅርታ እና ለመተው ልባችን ክፍት መሆን አለበት።

አንዳንድ ጊዜ ተሸንፈን ብዙዎችን ለማሻገር፤ ዝቅ ብለን ከፍ ለማድረግም የምናስብና የምንሠራ ካልሆንን በስተቀር በሁሉም ጉዳይ እኔ የምለው ብቻ ካልን አደገኛ ነገር ነው። ኢትዮጵያን የመሰለ ትልቅ አገርና ብዙ ሕዝብ ያለበት አገር እንድንመራ ዕድል ስናገኝ ብዙ ትዕግስት፣ መማር፣ ማስተዋል፣ ብዙ መጠየቅ፣ ብዙ ራስን መፈተሽ፣ እያሻሻሉና እያረሙ መሄድ የሚጠይቅ ስለሆነ አሁን ያለውንም ችግር በዚሁ አግባብ እያየን መፍትሄም እያበጀን እንሄዳለን።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የሆቴል ዘርፍ ኢንቨስትመንትን በዓለም አቀፍ የተወዳዳሪነት ደረጃ እውን የማድረግ ጥረት

አንተነህ ቸሬ

በኪነጥበብ፣በስፖርትና ዘርፎች ስኬታማ የሆኑ ግለሰቦች በንግድና ኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ ተሰማርተው ተጨማሪ ስኬቶችን ሲያስመዘግቡ ማየት የተለመደ ተግባር ነው።ይህ እውነት በኢትዮጵያም ገቢራዊ ሆኖ ይታያል። 27 የዓለም ክብረ-ወሰኖችን መስበር የቻለው የሩጫው ዓለም ንጉሥ፣ አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ በግብርና፣ በሪልስቴት፣ በትምህርት፣ በሆቴልና ቱሪዝም እና በመዝናኛ ዘርፎች እያከናወነ የሚገኘው ስራ የዚህ መሰል ተግባር ቀዳሚ ማሳያ ተደርጎ ይጠቀሳል። ከ22 ዓመታት በላይ በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች በልዩ ልዩ የኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ ተሰማርቶ የሚገኘው ‹‹ኃይሌና ዓለም ኢንተርናሽናል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር››፣ የስራ እድል ፈጠራን ጨምሮ በሀገራዊ ምጣኔ ሀብት ውስጥ ያለው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው።

አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ ‹‹ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ›› (Haile Hotels and Resorts Group) በተሰኘው ተቋሙ ስር በሚተዳደሩ ሆቴሎችና ሪዞርቶች አማካኝነት የሚያከናውነው የሆቴልና ቱሪዝም ኢንቨስትመንት ደግሞ የሀገር ገፅታን መገንባትን ጨምሮ፣ ቱሪስቶችን በመሳብ፣ ለዜጎች የሥራ እድል በመፍጠርና ለአገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቶችን በማቅረብ ለሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት ትልቅ አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል። የ‹‹ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ›› ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ መልካሙ መኮንን ስለተቋሙ የሆቴልና ቱሪዝም ኢንቨስትመንት የስራ እንቅስቃሴ ለ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ ማብራሪያ ሰጥተዋል።



አቶ መልካሙ መኮንን

**የሆቴልና ቱሪዝም ኢንቨስትመንት የሀገር ገፅታን መገንባትን ጨምሮ፣ ቱሪስቶችን በመሳብ፣ ለዜጎች የሥራ እድል በመፍጠርና ለአገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቶችን በማቅረብ ለሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት ትልቅ አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል።**

### የተቋሙ የኢንቨስትመንት ተግባራት

ከ12 ዓመታት በፊት በሐዋሳ ከተማ በሚገኘው ‹‹ኃይሌ ሪዞርት ሐዋሳ›› የሆቴል ዘርፍ አገልግሎት መስጠት የጀመረው ‹‹ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ››፣ ኢትዮጵያ በሆቴልና ቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ላስመዘገበቻቸው ስኬቶች ዋነኛ ተዋናይና ምሳሌ መሆን የቻለ ተቋም ነው። በኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ ስር ካሉት ሆቴሎችና ሪዞርቶች መካከል አሁን አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት የሐዋሳ፣ አርባ ምንጭ፣ አዳማ፣ ባቱ፣ ሱሉልታ (ያያ ቪሌጅ) የጎንደር እና በቅርቡ ስራ የጀመረው ባለአምስት ኮከቡ የአዲስ አበባው ‹‹ኃይሌ ግራንድ አዲስ አበባ›› ሆቴሎችና ሪዞርቶች ናቸው። በፀጥታ ችግር ምክንያት ጉዳት ከደረሰባቸው ሁለት ሆቴሎችና ሪዞርቶች መካከል በባቱ ከተማ የሚገኘው ሆቴል እድሳትና ጥገና ተደርጎለት ወደ ስራ የተመለሰ ሲሆን፤ ሌላኛው ጉዳት ያስተናገደው የሻሸመኔው ሆቴል ደግሞ ከቀድሞ አገልግሎቱ በላቀ አቋም ወደ አገልግሎት እንዲመለስ እየተሰራ ይገኛል። የአራት ኮከብ ደረጃ ያላቸውና በግንባታ ላይ የሚገኙ የወላይታ ሶዶ፣ የደብረ ብርሃን እና የጅማ ሆቴሎች እንዲሁም በፀጥታ መደፍረስና በሌሎች ችግሮች ምክንያት ግንባታው ተቋርጦ የሚገኘው ባለሦስት ኮከቡ የኮንሶ ሆቴል የግሩፑ ተጨማሪ ሆቴሎች ናቸው። የወላይታ ሶዶው ሆቴል በዚህ ዓመት መጨረሻ ላይ ይጠናቀቃል። በቀጣይም ግሩፑ በወልቂጤ ከተማ ሆቴል ለመገንባት መሬት ተረክቧል።

በስራ ላይ የሚገኙት የኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች እስካሁን ለአንድ ሺ 700 ዜጎች ቋሚ የሥራ እድል ፈጥረዋል። የሆቴልና ቱሪዝም ስራው እየሰፋ ሲሄድ በሚፈጠረው የግብዓት አቅርቦትና የገበያ ትስስር አማካኝነት ደግሞ ሌሎች ተጨማሪ የኅብረተሰብ ክፍሎችም በቀጥታና በተዘዋዋሪ የስራ እድል ተጠቃሚ ይሆናሉ። አሁን በግንባታ ላይ የሚገኙት ሆቴሎች በግንባታ ወቅትና ግንባታቸው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ ተጨማሪ የስራ እድሎችን ይፈጥራሉ። ቱሪዝም በመንግሥት ትኩረት ከተሰጣቸው የምጣኔ ሀብት ዘርፎች መካከል አንዱ መሆኑ ለሆቴል ዘርፍ ኢንቨስትመንት ትልቅ እድልን ይፈጥራል።

### የሆቴሎቹ ልዩ መገለጫዎች

በኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ ስር የሚገኙት ሆቴሎችና ሪዞርቶች በደንበኞች ዘንድ ተመራጭ እንዲሁም በዘርፉም ስኬታማ ለመሆን እንዲችሉ የሚከተሏቸው ልዩ መገለጫዎችና አሰራሮች አሏቸው። ከእነዚህ መገለጫዎቻቸው መካከል አንዱ፣ ሆቴሎቹና ሪዞርቶቹ ለቤተሰብ መዝናኛ እንዲሆኑ በሚገባ ዲዛይን የተደረጉ መሆናቸው ነው።

ለሆቴሎቹና ሪዞርቶቹ ግንባታ የሚመረጡት የመሬት አቀማመጦች ሰፋ ያሉና ልዩ የተፈጥሮ ገጽታዎችን ማዕከል ያደረጉ ናቸው። ሆቴሎቹና ሪዞርቶቹ ሁሉንም አገልግሎቶች (መዝናኛ፣ ስራ፣ ጤናና ውበት መጠበቂያ ...) ከፍተኛ በሆነ ጥራት በአንድ ቦታ አካተው ለማቅረብ የሚያስችሉ (All Inclusive Service Providers) መሆናቸውም ከሌሎች መሰል አገልግሎት ሰጪ የዘርፉ ተቋማት ልዩ የሚያደርጋቸው ባህርያቸው ነው።

ሀገር በቀል የአገልግሎት አሰጣጥ ባህልን ወደ ንግድ (ቢዝነስ) የመቀየር ስኬትና ልምድም የሆቴሎቹና ሪዞርቶቹ መለያ ባህርይ ነው። ተቋሙ የእንግዶች ደህንነትን ጨምሮ ፈፅሞ ለድርድር የማይቀርቡ ጥብቅ መርሆች አሉት። በሁሉም ደረጃዎች ያሉት የሆቴሎቹና ሪዞርቶቹ ሰራተኞች በላቀ ንቃትና ትህትና ለእንግዶች ፍላጎቶች መሟላት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው መስራታቸው የዚህ ስኬትና ልምድ ባለቤት ለመሆን አብቅቷቸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ የአገልግሎት ጥራት ዘላቂ በሆነ መንገድ እንዲጠበቅ የሚያደርግና ደንበኞች በሁሉም የግሩፑ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል በኮርፖሬት ደረጃ የሚመራ የጥራት ዋስትና መርሃ ግብር (Quality Assurance Program) አለው። ይህ መርሃ ግብርም ከግሩፑ ልዩ ባህርያትና መገለጫዎች መካከል አንዱ ተደርጎ ይጠቀሳል።

ሆቴሎቹና ሪዞርቶቹ በአንድ አካል ባለቤትነትና መለያ ስር የሚተዳደሩ (Chain Hotels) ናቸው። ይህም ሆቴሎቹን በዚህ የአደረጃጀትና አመራር ዓይነት የሚንቀሳቀሱ ግንባር ቀደም ሀገር በቀል ሆቴሎች (Local Chain Hotel) ያደርጋቸዋል። ይህ የሆቴሎቹ አደረጃጀትና አስተዳደር ‹‹ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ›› ወደፊት በዘርፉ ተስፋ የሚጣልበት እንዲሁም ለሌሎች አርዓያ መሆን የሚችል ተቋም እንዲሆን ያስችለዋል። ይህም ተቋሙ ‹‹መገለጫዬ ነው›› ብሎ በልዩነት የሚጠቅሰው ሌላው መለያው ነው።

### የ12 ዓመታት ዐበይት ስኬቶች

ከ12 ዓመታት በፊት በሐዋሳ ከተማ በሚገኘው ‹‹ኃይሌ ሪዞርት ሐዋሳ›› የሆቴል ዘርፍ አገልግሎት መስጠት የጀመረው ‹‹ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ››፣ በሆቴልና ቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ያሳካቸው ስኬቶች ሀገሪቱ በዘርፉ ያስመዘገበቻቸው እድገቶች ማሳያዎች ናቸው። ተቋሙ የተወዳዳሪነት ደረጃው ከኢትዮጵያ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲሆን በማለሙ በዘርፉ ብዙ እመርታዎችን ማሳየት ችሏል። ከተቋሙ ዐበይት ስኬቶች መካከል የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እና የሆቴል አመራር ተጠቃሽ ናቸው። ከዚህ ቀደም የማይቻል የሚመስለውን የአገልግሎት አሰጣጥ በአንድ ስያሜና አስተዳደር ስር ከሚተዳደሩ ዓለም አቀፍ ሆቴሎች በተሻለ መልኩ እውን ማድረግ ችሏል። የስራ ሂደቶቹን በማዘመንና በማሻሻል ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ያደረገው ጥረት ለሌሎች ሆቴሎች ምሳሌ መሆን የሚችል አሰራር ነው። ብዙ ሆቴሎችን በአንድነት መምራት መቻልና ስራውንም ለሌሎች የዘርፉ ተዋንያን በማስተዋወቅና በማስረፅ ረገድ ስኬት ማስመዝገብ የቻለ ድርጅትም ነው።

የ‹‹ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ›› ሆቴሎችና ሪዞርቶች ለሚሰጧቸው አገልግሎቶች በርካታ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሽልማቶችንና እውቅናዎችን አግኝተዋል።

በ‹‹ቡኪንግ ዶት ኮም›› (Booking.com)፣ በ‹‹ትሪፕ አድቫይዘር›› (Trip Advisor) እና በሌሎች ዓለም አቀፍ የእንግዳ አስተያየት መሰብሰቢያና ሆቴል መያዣ (Booking) ድረ ገፆች አማካኝነት ሽልማቶችን አግኝተዋል። ለአብነት ያህልም በ‹‹ቡኪንግ ዶት ኮም›› የሐዋሳ እና አርባ ምንጭ ኃይሌ ሪዞርቶች ጥራት ያለው አገልግሎት ከሚያቀርቡ ምርጥ ዓለም አቀፍ ሆቴሎች መካከል በመካተት ተሸልመዋል። ባለአራት ኮከቦቹ የግሩፑ ሆቴሎች በ‹‹ትሪፕ አድቫይዘር›› በአገልግሎት ልህቀት በየዓመቱ እውቅና ያገኛሉ። ሪዞርቶቹ የሆቴል ግብይት ባለሙያዎች ማኅበርን የ‹‹ምርጥ ሁሉን አቀፍ አገልግሎት አቅራቢ ሪዞርቶች›› ሽልማትንም አሸንፈዋል። ከዚህ በተጨማሪም ተቋሙ ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴርም በተለያዩ ጊዜያት የላቀ አገልግሎት ሽልማቶችን አግኝቷል። የ‹‹ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ›› ሆቴሎችና ሪዞርቶች በየክልሎች በሚዘጋጁ የአገልግሎት ልህቀት እውቅናና ሽልማቶች ላይም በተደጋጋሚ እውቅናዎችን አግኝተዋል።

### የሆቴል ዘርፍ ተግዳሮቶችና መውጫ መንገዶች

የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ልማት እንደሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች ሁሉ በርካታ ተግዳሮቶች ያሉበት ዘርፍ እንደሆነ ተደጋግሞ ይገለፃል። ‹‹ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ››ም በ12 ዓመታት የስራ እንቅስቃሴው ሂደት የተለያዩ ችግሮች አጋጥመውታል። ከእነዚህ ተግዳሮቶች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ብቁ የሆነና ሙያዊ ስነ ምግባር የተላበሰ የሰው ኃይል እጥረት ነው። ዘርፉ የእንግዶች/የደንበኞች ደህንነት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥበት እንደመሆኑ ይህን ተግባር በብቃት ለመወጣት ለአገልግሎቱ የሚመጥን ብቁ የሰው ኃይል ማግኘት አስፈላጊ ግብዓት ነው።

የሆቴል አገልግሎትን በጥራት ለማቅረብ በሚስችሉ ግብዓቶች አቅርቦት ዙሪያ ያለው ውጣ ውረድ፣ የሀገር ውስጥ ኅብኚዎች ቁጥር ማነስና ኅብኚዎቹን በማበረታታት ረገድ የሚስተዋሉ ድክመቶች፣ የሰላምና ፀጥታ መደፍረስ እንዲሁም የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ በ ‹‹ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ›› የስራ እንቅስቃሴ ላይ መሰናክል የፈጠሩ ሌሎች ችግሮች ናቸው።

ተቋሙ ያጋጠሙትን ችግሮች ለማለፍ የተለያዩ አሰራሮችን ይተገብራል። በ‹‹ይቻላል›› መንፈስና በቡድን/በቅንጅት የመስራት ባህል፣ ከችግሮችና መሰናክሎች ይልቅ የመውጫ መንገዶችና መፍትሄዎች ላይ የማተኮር ስልት፣ ፈተናዎችን እንደመልካም እድልና አጋጣሚ የመጠቀም ጥበብ እንዲሁም ቁርጠኛ በሆነ ተከታታይና ዘላቂ የመሻሻልና የማደግ መርህ (ከትናንት ዛሬ፣ ከዛሬ ደግሞ ነገ መማርና መሻሻል) ላይ ተመስርቶ የመስራት ልምድ ‹‹ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ›› የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች በብቃት የሚያልፍባቸው መርሆቹ ናቸው። እነዚህ መርሆቹም ተቋሙ በኮሮና ወረርሽኝ ወቅት አንድም ሰራተኛ ሳይቀነስ እና ሆቴሎቹንና ሪዞርቶቹን ሳይዘጋ እንዲቀጥል፤ የአሰራር ስርዓቶቹን እንዲፈትሽ፤ የማኅበራዊ ኃላፊነት ተግባራቱን እንዲያጠናክር አስችለውታል።

### የወደፊት እቅዶች

አገልግሎት እየሰጡ ያሉ እንዲሁም በግንባታና መልሶ ግንባታ ላይ የሚገኙ 12 ሆቴሎችንና ሪዞርቶችን ያካተተው ‹‹ኃይሌ ሆቴሎችና ሪዞርቶች ግሩፕ›› በምስራቅ አፍሪካ ሆቴሎችን በማልማትና በማስተዳደር በዘርፉ መሪ የሆነ ድርጅት እውን የማድረግ ርዕይ አለው። በኢትዮጵያ ብዙ ሆቴሎችን በማልማትና በማስተዳደር መሪ የሆነው ይህ ተቋም፣ ሆቴሎችንና ሪዞርቶችን ከመገንባትና ከማስተዳደር በተጨማሪ ሌሎች ባለሀብቶች የገነቧቸውን ሆቴሎችንና ሪዞርቶችን በስሙ በማስተዳደር የአገልግሎት መለያውን (Brand) ከኢትዮጵያ አልፎ በጎረቤት ሀገራት ጭምር የማስፋፋት እቅድ አለው። ይህን እቅድ ለማሳካት በሚያስችለው ጥሩ አፈፃፀም ላይም ይገኛል።

ጎሜ

# ያለማገልገል “ትሩፋቶች”

ግርማ መንግሥቴ

**አንድ ሰው ወንበሩ ላይ እስከ ተቀመጠ ድረስ መቀመጥም አለማገልገልም አይችልም። መሆን የሚችለው መቀመጥና ማገልገል ነው። ወይም፣ አለመቀመጥና አለማገልገል ብቻ ነው።**

ከሁሉም በፊት አንባቢ “ትሩፋቶች” የሚለውን ቃል ከቅንፍ አውጥቶ ከዚህ ጽሑፍ አውድ አኳያ በፈለገው ሊቀይረውና ሊበይነው የሚችል መሆኑን፤ ከፈለገም “ጦሶች”፣ “ሰቆቃዎች”፣ “ጉስቁልናዎች”፣ “ስቃዮች” . . . ወዘተ፤ አልያም፣ ገራገር በሆነ መልኩ “ውጤቶች” (ውጤት በሁለቱም በኩል ሊሆን ስለሚችል)፣ “ጉድለቶች”፣ “ክፍተቶች”፣ . . . ወዘተ ሊለው የሚችል መሆኑን በቅንፍ አስቀምጦ ማለፍ ተገቢ በመሆኑ ይህንኑ አድርገን ወደ ጉዳያችን እናምራ።

በርእሳችን አማካኝነት ይፋ እንዳደረግነው፣ የእለቱ አቢይ ርእሰ ጉዳያችን የሕዝብ አገልግሎት (ተግባሩ) እና ተያያዥ የሆነው የሕዝብ አገልጋይነት (ሙያው) ነው።

እንደሚታወቀው፣ አገልግሎት አቅጣጫው ሁለት ነው። አገልግሎት ሰጪ (ባለሙያ(ዎች)፣ ተቋማት . . .) አሉ፡፡ አገልግሎት ተቀባይ (ግለሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ሕዝብ፤ ተቋማት . . .) አሉ። በመሆኑም የአገልግሎት ወሰን ዱካው ከዚህ በመለስ ሊባል የሚችል አይደለም ማለት ነው።

በመሰረቱ፣ “ሕዝባዊ አገልግሎት” ሲባል ቃላትን ለማሽሞንሞን ተብሎ የተሰደረ ሳይሆን ግብር ከፋዩ ህብረተሰብ በሚከፍለው ግብር ከተቋቋሙት ተቋማት የሚያገኛቸውን አገልግሎቶች ለማመልከት ነው። በማንኛውም አይነት ፍልስፍናም ይሁን ሳይንስ፣ ግብር ከፋይ ህብረተሰብ ተገቢውን አገልግሎት የማግኘት ሙሉ፣ ምንም ያልተሸራረፈ መብት አለው።

እንደማንኛውም የአለም አገራት ኢትዮጵያም ሕዝባዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን አቋቁማ አገልግሎት እየሰጠች ትገኛለች። ጥያቄው፣ እነዚህ ተቋማት ምን ያህል አላማቸውን አሳክተዋል፤ ምን ያህልስ ሕዝቡን አገልግለዋል? የሚል ነው። ለእነዚህ ተቋማት ደንበኛ ንጉስ ነው ወይስ እርኩስ? የሚለውንም ልንቃኝ እንገደዳለን።

ብዙ ጊዜ እንደሚሰማው ሕዝቡ ከተቋማቱ የሚፈልገውን ያህል አገልግሎት በብዛትም፣ በጥራትም እያገኘ አይደለም። በአጠቃላይ ያለው ነገር፣ “ደንበኛ ንጉስ ነው” የሚለው ሳይሆን፤ “ደንበኛ ርኩስ ነው” የሚል ይመስላል።

ሁሉም እንደሚያውቀው፣ ማገልገል ሃላፊነት ብቻም ሳይሆን ግዴታም ነው። አንድ ሰው ወንበሩ ላይ እስከ ተቀመጠ ድረስ መቀመጥም አለማገልገልም አይችልም። መሆን የሚችለው መቀመጥና ማገልገል ነው። ወይም፣ አለመቀመጥና አለማገልገል ብቻ ነው። በቃ፣ ሌላ ምርጫ የለም። ካለ ለመስማት ሁላችንም ዝግጁዎች ነን። በኢኮኖሚክስ ሕግ መሰረት ሁለቱንም (ገንዘብንና የፈለጉትን እቃ፤ ለምሳሌ፣ ሳሙናው 50 ብር ቢሆን፣ ሳሙናውን ለማግኘት 50 ብር ለባለ ሳሙናው መስጠት የግድ ይሆናል) ማግኘት እንደማይቻለው ሁሉ፣ በአገልጋይነት ዘርፍም ሁለቱንም መሆን (መቀመጥና አለማገልገል) አይቻልም።

ላለለት ማገልገል መባረክ ነበር፤ ለፈቀደለት ማገልገል መታደል ነበር። ላለለት ማገልገል ሀላፊነትን መወጣት ነበር፤ ላለለት ማገልገል መሰልጠን ነበር። ይሁን እንጂ፣ ያለው ሁሉ ሲታይ የተገላቢጦሽ ነው። እዚህ ሀገር አለማገልገል ያስኮፍሳል። አለማገልገል ሲያሾምና ሲያሸልም እንጂ ሲያስጠይቅ ማየት አልተቻለም። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ይህ የትም ቢኬድ የሚያጋጥም ክስተት ነውና ለማንም ብርቅ አይደለም።

ዛሬ፣ ከ’ግር እስከ ራሱ እንደሚባለው፣ ከትንሹ (ግን ደግሞ ወሳኙ) ተቋም፣ ቀበሌ ጀምሮ በየደረጃው ወደ ላይ ቢወጣ እንደልብ የሚገኘው (“ሰርቪስ” የሚባለው) “አገልግሎት” ሳይሆን 12ቱ የስነ ምግባር ደንቦች (መርሆች) ናቸው። በመሆኑም፣ ለአገልግሎት ፈላጊው በእነሱ (መርሆቹ) ተፅናንቶም ይሁን ተሳልቆ ከመመለስ ውጪ ሌላ እድል የለም።

ከ“ስብሰባ ላይ ናቸው” ጀምሮ ሕዝባዊ አገልግሎትን የሚያጨናግፉ እንከኖች በርካቶች ሲሆኑ፣ ግልፅ የሆነ እጅ መንሻን (ጎቦ) በይፋ እስከ መጠየቅ ድረስ ይሄዳል። የዚህ ማረጋገጫው ከአገልጋዩ ባለሙያ ለተገልጋዩ እንግዳ የሚቀርቡ “አስተያየቶች” ናቸው።

ይህ ጸሐፊ አገልግሎት ፍለጋ አንድ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ሄዶ በእንግልት ላይ ሳለ ከሌላ ተንገላች ጋር ድንገት ለመገናኘት ችሎ ሁለቱም የሆድ የሆዳቸውን መጫወት ጀመሩ፡፡ እኚሁ አገልገሎት ፈላጊ በአንድ ወቅት አገልግሎት ሰጪው (12ቱን የስነምግባር መርሆዎች ከጀርባው ባለው ግድግዳ ላይ የለጠፈው ባለሙያ) “አንቺ ደግሞ ሰው የሚርበው፣ የሚጠማው . . . አይመስልሽም። ሁል ጊዜ የምታውቂው እንዲህ አድርጉልኝ፣ ይሄንን ስሩልኝ . . . ማለት ብቻ ነው።” እንዳላቸውና አሁን እየደረሰባቸው ያለው መንገላታት ለርሳቸው እንግዳ ደራሽ እንዳልሆነ የነገሩት እየተነጋገርንበት ስላለው “ያለማገልገል ትሩፋቶች” አንድና ተገቢ የሆነ ማሳያ ነው።

ይህ ጸሐፊ ራሱ ከቀበሌ ይሰጠው ዘንድ ለጠየቀው ሰነድ “ፕሪንተሩ ጠዋት ጠዋት ነው የሚሰራው”፤ “ፍላሹን ሰው ይዞት ሄዷል፤ እስኪመለስ ጠብቅ።” ወዘተ እና የመሳሰሉት የአገልግሎት ሰጪ ባለሙያ መልሶች ሁሌም ከአእምሮው የማይጠፉ የአገልግሎት አሰጣጣችን የኋልዮሽ ጉዞ ማሳያዎች ናቸው።

ዛሬ ዛሬ አገልግሎት ተቀባዮች (ፈላጊዎች) በእግር ከመሄድ በእጅ መሄድ ከመፍትሄ ላይ እንደሚያደርስ ሲናገሩ መስማት አዲስ ነገር አይደለም። “ለፈጣን አገልግሎት ማግኘት ብቸኛው መፍትሄ በእጅ መሄድ ነው” የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሱ የቆዩ ይመስል “አንድና አንድ መፍትሄው በእጅ መሄድ ብቻ ነው። በእጁ ለመሄድ ፍቃደኛ ካልሆነ፣ ያ ሰው ተገትሮ ይቀራታል እንጂ አገልግሎት አገኛለሁ ብሎ አያስብ” ሲሉም ይደመድማሉ። ይደምድሙ እንጂ እንደ ሀገርና ሕዝብ ሲታሰብ ግን መሄድ የሚያስፈልገው በእግር እንጂ በእጅ ሊሆን አይገባም። በእጅ መሄድ እንደ ግለሰብ መፍትሄ ቢመስልም፣ እንደ ሀገር ግን አንድ ራሱን የቻለ ትልቅ ውድቀትና አንድ ራሱን የቻለ ነቀርሳ ነው። ያጠፋል እንጂ አያለማም።

ይህ በእጅ የመሄድ ነገር ሌላ ገጠመኝንም ያስታውሳል። በአንድ ወቅት አንድ መንጃ ፍቃድ ለማውጣት ወደ መንጃ ፍቃድ ማሰልጠኛ ያቀና ጓደኛዬ የከተማ ውስጥ ፈተናን ሊያልፍ አልቻለም። ቢል፣ ቢሠራ፣ ቢለፋ . . አልሆንልህ አለው፤ ማለፍ አልቻለም። በኋላ ቢቸግረው፣ “ምንድን ነው ምክንያቱ፣ ለምን አላልፍም፣ ምን እያደረኩ ነው ሁሌ የምትጥለኝ?” ይለዋል። ፈታኙም ምንም ሳያቅማማ፣ ሳይፈራና ያለበትን ሙያዊ ሀላፊነት ከግምት እንኳን ሳያስገባ “አንተ መቼም አታልፍ። እጅህ ይንቀጠቀጣል።” እንዳለው አጫውቶኛል።

ይህ ብቻ አይደለም፤ አገልግሎት አሰጣጥን አደጋ ላይ ከጣሉትና አገልግሎት ተቀባይን ለእንግልት ከዳረጉት አንዱ ”መላ አለው?” የሚለው አስተሳሰብና ድርጊት ነው። (“መላ አለው” ማለት ጥቅም ያስገኛል ወይ ለማለት ነው።)

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ 7 አባላት ያሉት የፀረ ሙስና ብሄራዊ ኮሚቴ በማቋቋም በፓርላማ ሲያፀድቁ «ሙስና የሀገርና የደኅንነት ሥጋት ሆኗል» ያሉበት ምክንያት የዚሁ፣ እንደ ቀላል ሲታይ የነበረው ”መላ አለው?” አስተሳሰብ መስረፅና በቅርፅ፣ ይዘቱና ሽፋኑ አገራዊ እየሆነ የመምጣቱ ጉዳይ እንጂ ሌላ አይደለምና የሕዝባዊ አገልግሎት ጉዳይ ከምር ያሳስባል።

በነገራችን ላይ፣ በ”መላ አለው?” አስተሳሰብ መመራት፣ ሕዝባዊ አገልግሎትን ለግል ጥቅም ማዋል፣ በሙስና መዘፈቅ . . . በየትኛውም መመዘኛ ሕገ ወጥነት ሲሆን፤ ለሕግ የበላይነት ያለመገዛትና ሕገመንግስታዊ ስርአትን በኃይል የመናድ ተግባር ብቻ ሳይሆን የመደፍጠጥም እንቅስቃሴ አካል ነው (እዚህ ጋር አፃፃፉ በ’97 ሲወጡ የነበሩ ጽሑፎችን ከመሰለ ይቅርታ)። ባይሆን ኖሮማ 7ቱ የብሄራዊ ኮሚቴ አባላት ሹመታቸው በፓርላማ ባልፀደቀ ነበር። ያለማገልገል “ትሩፋቶች”ም ስቃይና መከራ፤ ውጣ ውረድና እንግልት ባልሆኑ ነበር። የዜጎች የመገልገል ዲሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ መብቶችም በነጭ ባልተሰረዙም ነበር። ስራዎች በአግባቡ በተሰሩና ምርትና ምርታማነት እንደ ሮኬት እየተምዘገዘገ በገሰገሰም ነበር። “ቀልጣፋ አገልግሎት . . .” የሚለውም ከስላቅ በተረፈ ነበር። ኢትዮጵያም የሞተላት ቀርቶ የገደላት ባልበላም ነበር። . . . ነበር። . . . ነበር።

እዚህ ላይ ተቋማት ላይ አተኮርን እንጂ፣ “የትራንስፖርት አገልግሎት አለ?”፣ “የሕግ አገልግሎት አለ?”፣ “የፀጥታ አገልግሎት አለ?”፣ ወደ ጋምቤላና ቤንሻንጉል አካባቢ ሄደን “የኢትዮቴሌኮም አገልግሎት አለ?”፣ “የብድር አገልግሎት?”፣ “ማህበራዊ አገልግሎት” (ለምሳሌ፣ ህክምና፣ ትምህርት) . . . ወዘተ እያልን ብንጠይቅ ምላሹ ምን ሊሆን እንደሚችል መልስ የሚሰጥ አለ?

“የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን ማዘመን የሚያስችል የሶስትዮሽ ስምምነት ተፈረመ” የሚል ዜና ለአየር በቅቶ የሰማነው በዚሁ በያዝነው አመት ነው። ዝርዝሩ ይቅርና እንደው “ጉዳዩ ምን ላይ ደረሰ?” ብለን ብንጠይቅ መልስ የሚሰጠን (“የመልስ አገልግሎት ሰጪ” የሚባል ካለ) አለ?

እንደሚታወቀውና በሕግም እንደተደነገገው “ትምህርት የሕዝብ አገልግሎት ነው።” ትምህርት የህዝብ አገልግሎት ከሆነ ያለበት ሁኔታ ምን ይመስላል? ከሕዝብ መሰረታዊ መብቶች አንዱ የሆነው ትምህርት በአገልግሎቱ አማካኝነት የተገኙትንስ ትሩፋቶች (ልዩ ፍላጎትን ጨምሮ) አንድ፣ ሁለት . . . በማለት ቆጥሮ የሚነግረን አለ?

እንደው ለመሆኑ፣ የኮቪድ-19ኙን መከሰት ተከትሎ የነበረው ህዝባዊ አገልግሎት የት ገባ? ወይስ ክስተቱ ራስንም ስለሚያሰጋ ነው (እከሌ ከእከሌ ሳይባል) ያ ሁሉ ርብርብ? የግል ሳይባል የመንግስት . . . ሁሉም አገልግሎትና አቅርቦት ላይ ሲረባረብ የነበረው እንቅስቃሴ ለምን እንደ አንድ መልካም አጋጣሚና ተሞክሮ ተወስዶ ሊቀጥል አልቻለም? ብለን ብንጠይ የምናገኘው መልስ ምን ሊሆን እንደሚችል ለማንም ግልፅ ነው ወይም አይደለም። ብቻ አንድ ነገር ግልፅ ሲሆን፣ እሱም ሊቀጥል የሚገባው አሰራር ወደ ኋላ የሽምጥ ጋልቦ፣ አስቀድሞ ከነበረበትም አልፎ ወዲያ ተመልሷል። (በአንድ ወቅት ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ “የከተማ ሕዝባዊ አገልግሎት አሰጣጥ በአዲስ አበባ” በሚል ርዕስ አዘጋጅቶት በነበረው የውይይት መድረክ ላይ በሰፊው ሲያነጋግር የነበረው ምንድን ነበር?)

በሌላው አለም ሕዝብና አገርን ለማገልገል ጥድፊያ ነው። አንድ ሀገራዊና ህዝባዊ ፋይዳ ያለው ተግባር (በውትድርና ሳይቀር) ፈፅሞ ለማለፍ ሽሚያ ነው። ስምን ከመቃብር በላይ አኑሮ ለመሄድ ትንቅንቅ ነው። አሻራን ለማሳረፍም እንደዛው። እዚህ ግን፣ በተለይ ዛሬ ዛሬ . . . የዚህ አይነቱ በመልካም ስነምግባር የታጀበ ተግባር አጉል ባህል ሊሆን (ካልሆነ ማለት ነው) ትንሽ ነው የቀረው። ለምን? ጥያቄው ይኸው ነው።

ማንም እንደሚገነዘበው፣ ሕዝባዊ አገልግሎት የለም ማለት ቅንነት የለም ማለት ነው። ሕዝባዊ አገልግሎት የለም ማለት አስተዋይነት የለም ማለት ነው። ሕዝባዊ አገልግሎት የለም ማለት አናርኪዝም ሰፍኗል ማለት ነው። ሕዝባዊ አገልግሎት የለም ማለት ህግ፣ ደንብና መመሪያ ተጥሷል ማለት ነው። ሕዝባዊ አገልግሎት የለም ማለት አለቃና ምንዝሩ (በድናቸው እንጂ) በቦታቸው የሉም ማለት ነው። ሕዝባዊ አገልግሎት የለም ማለት ዋልጌነት ተንሰራፍቷል ማለት ነው። በየትኛውም መመዘኛ፣ ሕዝባዊ አገልግሎት የለም ማለት የዜጎች ሰብአዊ መብት ተጥሷል ማለት ነው። በመሆኑም፣ እዚህ ገፅ ላይ በዚህ መልኩ እንፅፍ ዘንድ አስገድዶናል ማለት ነውና ጉዳዩ ለነገ የሚባል፣ በይደር የሚተው . . . አይደለም።

አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ፣ ጉዳዩ የተበላሸው ጉዳዮች በአገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ መከናወናቸው ቀርቶ ወደ ቁርጥና ክትፎ፤ ውስኪና ጎርዶን ሲዛወሩ ነው። ያኔ ነው አሉ ጉዳዩ ውሉን የሳተውና በዛው ስሩን የሰደደው።

እርግጥ ነው፣ በአገልግሎት አሰጣጡ ዘርፍ ለውጥ ያመጡ ወይም ያሻሻሉ ተቋማት የሉም ማለት አይቻልም፤ አሉ። ከእነዚህም አንዱ የኤሌክትሪክ አገልግሎትን እንደ ማሳያ መውሰድ ይቻላል።

የአገልግሎት አሰጣጥ ለውጡን እኛ ነዋሪዎቹ ከማየታችንም በተጨማሪ በአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮሙኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ አቶ በቀለ ክፍሌ ሰሞኑን ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለፁት፤ “ሶፍትዌሩ ሁለቱ ድርጅቶች በሚኖራቸው ግንኙነት የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር በመሆኑ፤ ተደጋጋሚ ችግር የሚያጋጥምበትን አካባቢ ለይተው መፍትሔ ማምጣት እንዲችሉ የማድረግ የእገዛ ስራ የሃይል አቅራቢ መስሪያ ቤቱ መስራቱን እና አሁን ላለው የተሻለ አገልግሎት የራሱን ሚና መጫወቱን” መግለፃቸው መስሪያ ቤቱ በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ መሻሻል እያሳየ መሆኑን ያመለክታል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት (ኢፕድ)ም ከእነዚሁ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ተግባራቸውን በከፍተኛ ደረጃ ካሻሻሉት መካከል ስለ መሆኑ በሚመለከታቸው ሁሉ እየተመሰከረለት ይገኛል።

ባጠቃላይ፣ በአገራችን ያለው ህዝባዊ አገልግሎት አሰጣጥ የሚያኮራ ደረጃ ላይ ሊገኝ ቀርቶ ገና ጅምር ላይ ያለ ነው የሚመስለው። “ተሻሻለ” ሲሉት ተመልሶ እንዘጭ ይላል። “ዘመነ” ሲሉት ተመልሶ እዛው ነው። ጭራሹንም ከሙስና ጋር እጅና ጓንት በመሆን በጋራ በመስራት ተገልጋዩን ህብረተሰብ ላልተፈለገ ስቃይና እንግልት እየዳረገ፤ ጊዜና ጉልበት እየበላ . . . የሚገኝ መኖሩን መካድ አይቻልም። በመሆኑም አስቸኳይ መፍትሄን፣ ፍቱን መዳኒቱ . . . መፈለጉ የሁላችንም፤ በተለይም የሚመለከታቸው ሁሉ ሃላፊነት ነውና ዛሬውኑ ወደ ተግባር ልንገባ ይገባል። ይህንን ማድረግ ካልቻልን እኛንና ሌሎች በርካታ ልፋቶቻችንን ሁሉ ጠራርጎ ሊወስዱብን ይችላልና ጊዜው አሁን ነው።

# የዘመን ጥበብ

## የእናት መጽሐፍ፤ ሳይንስ፣ ጥበብ፣ ፍልስፍና፣ አግራሞት

**ዋለልኝ አየለ**

የመጽሐፉ ስም:- እናት
ደራሲ:- ይሁኔ አየለ (ዶክተር)
የሕትመት ዘመን:- 2015 ዓ.ም
የገጽ ብዛት:- 406
የመሸጫ ዋጋ:- 500 ብር

ከመጽሐፉ ዋጋ ልነሳ። በመጽሐፉ የጀርባ ሽፋን ላይ «ገቢው ሙሉ በሙሉ የእናቶችን ሸክም ለሚያቃልሉ ተግባራት የሚውል።» ይላል።

ፀሐፊው ዶክተር ይሁኔ አየለ ይባላሉ። የሥነ ምግብና ጤና ተመራማሪ ናቸው። በሥነ ምግብና ጤና ላይ የሚያተኩሩ መጽሐፎችና የተለያዩ መጣጥፎች አሏቸው።

ይህኛውን መጽሐፍ ግን ለየት የሚያደርገው በእናት እና ከእናት ጋር የተያያዙ የጤና፣ የፍልስፍና፣ የማህበራዊ ሕይወት መስተጋብር... ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መሆኑ ነው። መጽሐፉ በንዑስ ርዕስ «የሴት ልጅ ስንክሳር፤ ከቤተሰባዊ ሕይወት እስከ ማኅበራዊ ሐለዮመንበርት» የሚል አለው። የመጽሐፉን ሽፋን እና ሙሉ ይዘቶች ወደኋላ በዝርዝር እንመለስበታለን።

መጽሐፉ የሚሸጠው እንደማንኛውም መጽሐፍ ከመጻሕፍት መደብሮች በመግዛት አይደለም። በሦስት ሰዎች ስም የተከፈተ የባንክ አካውንት አለ። የመጽሐፉ ገቢ ለደራሲው አይደርስም። መጽሐፉን የሚፈልጉ ሰዎች በተከፈተው የጋራ የባንክ አካውንት ከ500 ብር ጀምሮ (የአንዱ መጽሐፍ ዋጋ) የሚፈልጉትን ያህል መግዛት ይችላሉ፤ በተለያየ ችግር ውስጥ የሚገኙ እናቶችን እየረዱ ነው ማለት ነው።

ወደ መጽሐፉ ይዘት ከመግባታችን በፊት ስለደራሲው ዶክተር ይሁኔ አየለ ጥቂት ልበል።

ዶክተር ይሁኔ አየለን የማውቃቸው በማህበራዊ ትስስር (ፌስቡክ) ገጻቸው ነው። በመድረክ፣ በቴሌቭዥን፣ በጋዜጣ፣ በማህበራዊ ገጾችም ሆነ በየትኛውም የመገናኛ አማራጭ ብዙ ምሁራንን አውቃለሁ። የዶክተር ይሁኔ በተለየ የሚገርመኝ ግን ሳይንስን ያህል ረቂቅና ውስብስብ ነገር እጅግ በጣም ቀላል በሆነ ቋንቋ ማስረዳት መቻል ነው።

ብዙ በአካባቢያችን የሚገኙ የተክል፣ የእንስሳትና የተለያዩ ዘአካላት በአካባቢያዊ መጠሪያቸው ብናውቃቸው እንኳን ሳይንሳዊ ስማቸውን አናውቀውም። የዘርፉ ባለሙያዎች ደግሞ በሳይንሳዊ ስማቸው ቢያውቋቸው እንኳን አካባቢያዊ ስማቸውን አያውቁትም። ዶክተር ይሁኔ ግን «ይሄ ማለት ይህኛው ማለት ነው» በማለት በብዙ የጥናት ማጣቀሻዎች አስደግፈው ያስረዳሉ።

በልማዳዊ አጠራር የሚጠሩ የተለያዩ የበሽታ ዓይነቶችን በሳይንሳዊ ስማቸው ጠቅሰው ያስረዳሉ። ልብ የማይባሉ አካባቢያዊ የባህል ምግቦችን ሳይንሳዊ ጠቀሜታ ሲያስረዱ «በርገርና ፒዛ ለምኔ» ያሰኛል። በአጠቃላይ የዶክተር ይሁኔን መጽሐፍና መጣጥፎች ሳነብ ከሳይንስ ያለን ርቀት ነው የሚታየኝ።


ወደ መጽሐፉ ይዘቶች እንግባ። ይዘቶቹን በጥቂት በጥቂቱ ጥቅል ሀሳባቸውን ለመግለጽ እንጂ ሙሉውን ለመናገር አይደለም። አንዱ ገጽ ብቻ ከአምስት በላይ መጽሐፎች፣ የተለያዩ የጥናት አድራሻዎች የሚጠቀሱበት ነው። መጽሐፉ አንድ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን የቤተ መጽሐፍ ማውጫ ነው ማለት ይቻላል።


የመጽሐፉ የፊት ለፊት ሽፋን ላይ ልጅ ያዘለች አንዲት እናት ትታያለች። ይቺ እናት ልጅ አዝላ ከኋላ ደግሞ የሆነ ትልቅ ቋጥኝ ትጎትታለች። ረቂቅ የሚባል ምስል አይደለም፤ መልዕክቱ ለማንም በቀላሉ የሚገባ ነው። ምክንያቱም ከከተሞች ወጣ ብንል በአብዛኛው የአገራችን አካባቢዎች የምናየው ይህን የእናቶችን ስቃይ ነው። በጀርባቸው ልጅ አዝለው በፊታቸው ደግሞ የሆነ ነገር ይታቀፋሉ። ወይም ልጅ ታቅፈው በጀርባቸው ደግሞ ሌላ ነገር ያዝላሉ።

መጽሐፉ ዘጠኝ ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው ምዕራፍ ተማጽኖና አዋጅ ነው። የእናትን ውለታ መክፈል ባይቻልም ለእናት ተገቢውን ዋጋ መስጠት እንዳለብን የሚያሳይ ነው።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሴቶችን በተመለከተ የተጻፉም ሆነ በአፍ የሚነገሩ ልማዶች ሁሉ አልቀሩም። በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ፣ በሕዝብ ሥነ ቃል ውስጥ፣ በተለያዩ ዘፈኖች ውስጥ ሴትና እናትን በተመለከተ ያሉ የግጥም መልዕክቶች፣ ገጣሚያን፣ የልቦለድ ፀሐፊዎች ሴቶችን የገለጹበት ሁኔታ፣ ሃይማኖታዊ ጥቅሶች... በእነዚህ ሁሉ አጋጣሚዎች ሴቶች እንዴት እንደተገለጹ ያሳያል።

የሚገርመው ደራሲው የጠቀሷቸው ማጣቀሻዎች አንዳንዶቹ ሴትን(እናትን) አስመልክቶ የተጻፉ አይደሉም፤ እግረ መንገድ የተገለጹ ናቸው። ደራሲው ዶክተር ይሁኔ ግን አንዲት ዓረፍተ ነገር ብትሆን ራሱ እናትን በተመለከተ የተገለጹ ነገሮችን ልብ ብለዋል።




መጽሐፉን ማንበብ ሳይንስን ማወቅ ነው፣ የሰው ልጅ የጥበብ ሥራዎች ማወቅ ነው፣ ፍልስፍና ነው። የሚገርመው ግን መጽሐፉን ማንበብ መዝናኛም ጭምር ነው። መዝናናት ሲባል ለብዙው ትዝ የሚለው ቀልድ ሳይሆን አይቀርም። የሆነ የማናውቀው ያልለመድነው አስገራሚ ነገር ስናገኝ እንደመማለን፣ ተዝናናን ማለት ነው። የመጽሐፉ አንዳንድ ሳይንሳዊ ገለጻዎች እንደዚያ ናቸው። ይዘነው እየኖርን የማናውቀው ተፈጥሮ አለን። እሱን ሲነግረን እንደመማለን።

በሰው ልጅ ዝግመተ ለውጣዊ የመኖር ሂደት ውስጥ የተፈራረቁ የባህልና አኗኗር አብዮቶችን ይነግረናል። ለምሳሌ በጥንታዊ የኅብረተሰብ ዕድገት ውስጥ የሴት የበላይነት የነበረበት ሥርዓት ነበር። በጎሳ መሰል ሥርዓት ውስጥ የመሪነት ቦታው የሴቶች ነበር። ውርስ የእናት ዘር ሐረግን ተከትሎ ይሄድ ነበር። ባሎች መኖሪያቸውን በሴት አማቾቻቸው ዘንድ ያደርጉ ነበር።

እንግዲህ አሁን ያለው ባህልና ልማድ በተለያዩ የባህል አብዮቶች መፈራረቅ የመጣ ነው ማለት ነው። በሴትና በወንድ መካከል ያለው ልዩነት ሥነ ሕይወታዊ (ባዮሎጂካል) ብቻ ሳይሆን ሰው ሰራሽ የሆኑ ልዩነቶች ናቸው።

የዶክተር ይሁኔ መጽሐፍ እንደሚነግረን፤ ኢምሊ ማርቲን የተባለች የሴታዊት ተሟጋች (ፌሚኒስት) ተፈጥሯዊ የሆነውን የወንድ ነባዘርና የሴት እንቁላል ያላቸውን ሕይወታዊ ተዋፅዖ ተመራማሪዎቹ አድሎ አድርገውበታል ብላ ትሞግታለች። እሷና የዘመኗ ፌሚኒስቶች (ሴት ግዴ ይለዋል የዶክተር ይሁኔ አማርኛ) የተፈጥሮ ሳይንስ ተመራማሪዎችን ይሞግቱ ነበር። የተፈጥሮ ሳይንሱን ተመራመርን የሚሉት በብዛት ወንዶች ናቸው፤ እነርሱ ደግሞ የባህል ጫና አለባቸው፤ ስለዚህ የባህል ጫናው በሳይንሱ ላይም ተፅዕኖ አድርጎበታል የሚል ሙግት ነበራቸው።

እነዚህንና የመሳሰሉትን ከጥንት እስከ ዛሬ ያሉ ሳይንሳዊ ጥናቶችንና የባህል አብዮቶችን ጭምር ነው መጽሐፉ የሚነግረን።

አሁን ያለው የሴትና የወንድ የበላይነትና የበታችነት ልማድ ጥንታዊ መሠረት አለው። በተለይም የወንድ የበላይነት ጥንታዊውን የአደን ሕይወት መሠረት ያደረገ ነው። የሰው ልጅ በአደን ይኖር በነበረበት ጊዜ አውሬ መግደል የወንዶች ነበር። ይህ ልማድ እየተወራረደ እዚህ ደርሶ አሁንም በብዙ የአገራችን ክፍል የዱር ሥራዎች የወንዶች ናቸው።

እናት መጽሐፍ እንደምትነግረን፤ ይህ የወንዶች የአደን የበላይነት በሴት ተመራማሪዎች ደግሞ ተቀባይነት የለውም። የሴት ተመራማሪዎች እንደሚሉት፤ የሰውን ልጅ አሁን ወዳለበት ከፍተኛ ለውጥ ያመጣው አደን ሳይሆን የሴቶች ሥራ የሆኑት ናቸው።

እነዚህ የሴቶች ሥራዎች፤ መልቀም፣ መሰብሰብ፣ መፈለግ፣ መለየት፣ መፈልፈል፣ መቀጥቀጥ፣ መፍጨት፣ ተንከባክቦ ማሳደግና የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህን ሥራዎች መጀመር እጅን ለጉዞ ከመጠቀም ነፃ አወጣው። አጎንብሶ ከመሄድ በሁለት እግር ቀጥ ብሎ መሄድን አስከተለ። ስለዚህ ሴት ተመራማሪዎቹ በሥልጣኔ ሂደት ውስጥ የሴቶች ድርሻ የበለጠ ነው የሚል ሀሳብ አላቸው።

የማህበራዊ ሕይወት ማሰሪያ ነው የሚባለውን በልቶ ማደርን ብንወስድ፤ ሥጋ በቀላሉ የሚበላሽ ነው። ለረጅም ጊዜ የሚቀመጠው በሴቶች ሽምጠጣና ለቀማ የሚገኙት የዕፅዋት ምግቦች ናቸው የሚሉ ተመራማሪዎችም አሉ።

በአደን የጀመረው የወንዶች የበላይነት አመለካከት በእስያም ሆነ አውሮፓ አገራት ውስጥ የነበረ ነው። የሥልጣኔ ቁንጮ ላይ ናቸው የሚባሉት አገራት ብዙ የማይታመኑ የሚመስሉ ኋላቀር የሆኑ አመለካከቶች ነበሩ፤ እንደ ቻይና ባሉ አገራት ሴቶች በባዕድ አምልኮ ይወገዱባቸው ነበር። እንደ እንግሊዝ ባሉ አገራት ውስጥ የነበሩ አመለካከቶችን መጽሐፉ አስቀምጧል። የዴሞክራሲ ፈጣሪ ናት የምትባለዋ ግሪክ ለሴት አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ፈላስፎች ነበሯት።

የልጆች በአባት መጠራት የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሉት ይነግረናል የዶክተር ይሁኔ መጽሐፍ፤ ከእነዚህ ምክንያቶች አንዱ የሰውን ልጅ የጥንት ዘመን አኗኗር የሚገልጽ ነው። ይሄውም፤ ወንድ ከሴቷ ጋር ሥምረተ ሥጋ (ወሲብ) ከፈጸመ በኋላ ላይገናኙ ይችላሉ። ባለው የዘጠኝ ወር ቆይታ ውስጥ ሊረሳ ይችላል። በዚህ ምክንያት የአባትየው ስም እንዳይረሳ ይደረጋል ማለት ነው። ከዚህ ልማድ የተቀዳ «አባትነት እምነት ነው» የሚባል አባባል አለ።

የመጽሐፉ አንዱ ጠቀሜታ «አሜን!» ብለን የተቀበልናቸውን ልማዳዊ አስተሳሰቦች በሳይንሳዊ ጥናቶች ውድቅ የሚያደርግ መሆኑ ነው። ለምሳሌ፤ መካንነት ወይም አንድ ዓይነት ፆታ ብቻ መውለድ የሴቷ ችግር ተደርጎ ነው የሚወሰደው። መጽሐፉ ላይ በተቀመጠው መረጃ፤ አንዲት በተከታታይ ሴት ብቻ የምትወልድ እናት ብትኖር ችግሩ የእሷ አይደለም። የወንድነትን ፆታ የያዘው «y» የሚባለው ሀብለ በራሂ የሚገኘው በወንዱ ነባዘር ውስጥ ነው። መጽሐፉ እንዲህ ዓይነት ልማዳዊ አስተሳሰቦችን የሚያጠሩ ሳይንሳዊ ማብራሪያዎችን የያዘ ነው።

በመጽሐፉ ውስጥ ከሚገርሙኝ ነገሮች አንዱ ሰለጠኑ በሚባሉ አገራት ያሉ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ናቸው። ሴትን የሚበድል ነገር የሚፈፀመው ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ እንደሆነ ነው ብዙ ሰዎች የሚያምኑት። ለምሳሌ በቋንቋችን ውስጥ ለሴቶች አሉታዊ ትርጉም ያላቸው ብዙ ቃላት አሉ። ይህ ግን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የሰለጠኑ ናቸው በሚባሉትም አገራት ያለ ነው።

እንዲያውም አንድ ትርጉሙን ልብ ብየው የማላውቀው የእንግሊዝኛ ቃል የላቲን ትርጉሙ ተብራርቶ ሳየው ገርሞኛል። የሴት የመራቢያ አካል የእንግሊዝኛ ቃሉ (ቫጀይና) የላቲን ቃል ነው። ትርጉሙም የጎራዴ አፎት እንደማለት ነው። የጎራዴ አፎት ማለት ጎራዴው የሚቀመጥበት ከቆዳ የሚዘጋጅ ከረጢት ነገር ማለት ነው። ምናልባት የወንዱን የመራቢያ አካል እንደ ጎራዴ በማየት፤ የሴት የመራቢያ አካል ለወንዱ ጎራዴ ማስቀመጫ እንደማለት ነው ብለው ይመስላል። እንዲያ ከሆነ ሴትን ልጅ ዕቃ የማድረግ መልዕክት አለው ማለት ነው።

ወደ አማርኛው ስንመጣ የሥርዎ ቃሉ ትርጉም ስለማይታወቅ ለጊዜው አሉታዊ ትርጉም የለውም። ዳሩ ግን በምሳሌያዊ ንግግሮችና በፈሊጣዊ ቃላት ውስጥ ሴቶችን ዝቅ ያለ ግምት እንዲሰጣቸው የሚያደርጉ ቃላት ብዙ ናቸው። ሴቴ፣ ሴታሴት፣ ሴትላ... በሚሉ መነሻ ቃላት የሚገለጹ ቃላትና ሐረጎች ብዙ ጊዜ ለስድብና የአንድን ነገር ቀላልነት ለመግለጽ የሚያገለግሉ ናቸው።

እንግዲህ የእነዚህ ነገሮች ሁሉ ውጤት ነው እናትን ያህል ነገር ተገቢውን ክብር እንዳታገኝ ያደረገ። በልማድና በዘፈቀደ የሚባሉ ነገሮች ሲወርዱ ሲወራረዱ መጥተው በተፈጥሮ የሆኑ ሁሉ መሰለን። ተፈጥሯዊ ሁኔታውን እንኳን እንዳናስተውል አደረገን።

ለምሳሌ በሰው ልጅ መፈጠር ውስጥ ከወንዱ ነባዘር በላይ የሴቷ እንቁላል ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ነው ሳይንሱ የሚያሳየው። አብዛኛው የሰውነት ክፍል ቅርጽ የሚሠራው ከሴቷ እንቁላል ነው። ቀደም ሲል በነበረው አመለካከት ደግሞ አብዛኛው የሰውነት ቅርጽ የሚሠራው በወንዱ ነባዘር ውስጥ ነው የሚሉ ሳይንቲስቶች ነበሩ።

መጽሐፉ እንዲህ ተፈጥሮን ከልማድ እያፋጨ አንዴ ያዝናናል፣ አንዴ ያሳዝናል፣ አንዴ ያስደምማል። የሳይንስና የማህበራዊ ሕይወት መስተጋብር መሆኑ ቀርቶ ልክ እንደ ልቦለድ ቀልብ አንጠልጣይ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ «እውነት ይሄ ይደረግ ነበር?» እያልኩ ለማረጋገጥ የተጠቀሱ አድራሻዎችን ይዤ ወደ በይነ መረቡ ዓለም እገባለሁ። መጽሐፉ ብዙ ነገሮችን ለማንበብ ተንኳሽ ነው።

መጽሐፉ በሳይንሳዊ ጥናቶች የታጨቀ ስለሆነ እንዲህ ባይባል፣ ይሄ ባይጻፍ ለማለት አያስደፍርም። ዳሩ ግን አንዳንድ ማህበራዊ መስተጋብር ላይ ከተገለጹት በግሌ የማልስማማባቸው ደግሞ አሉ። ምናልባት ፀሐፊው በሴት ልጆች ላይ የሚደርሱ ማህበራዊ ጫናዎች በጣም ስለሚያሳስቧቸው ቢሆንም በሁሉም ጥፋቶች ግን ወንዶች የሚበረታቱ አይደሉም።

ለምሳሌ፤ ሴሰኝነት የሚወገዘው በሴቶች ብቻ እንደሆነ ነው ፀሐፊው የጻፉት። ምናልባት ከአካባቢ አካባቢ ቢለያይም ሴሰኝነት በወንድም በጣም የተወገዘ ነው። «ሸርሙጣ» የሚለው ነውር የስድብ ቃል ለሴት ብቻ የሚያገለግል ሳይሆን ለወንድ ጭምር የሚያገለግል ነው። በሚስቱ ላይ የሚማግጥ፣ ብዙ ሴቶችን ለሥምረተ ሥጋ የሚጠይቅ ወንድ በዚሁ ቃል ነው የሚሰደብና የሚወገዝ።

ድንግልናን በተመለከተ ጫናው በሴት ልጅ ላይ እንደሚበረታ ግልጽ ነው። ቢሆንም ግን ወንድ ልጅም ቢሆን ከጋብቻ በፊት ወሲባዊ ግንኙነት እንዲያደርግ አይበረታታም። በሃይማኖታዊ ሥርዓቱም ካየን (ለምሳሌ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት) በተክሊል የሚጋቡት ሴቷ ብቻ ሳይሆን ወንዱም ድንግል ከሆነ ነው።

ምናልባት በወጣቶች ዘንድ ወንድ ድንግል ሆኖ መቆየት እንደሌለበት ይወራ ይሆናል፤ ከጋብቻ በፊት ግንኙነት ማድረግ እንዳለበት ይገፋፋት ይሆናል። እንደ ባህልና ልማድ ካየነው ግን ከጋብቻ በፊት ሁለቱም ድንግል እንዲሆኑ ነው የሚበረታታው። ችግሩ ግን በተፈጥሮ የሴቶች መለያ ምልክት ስላለው የወንዶች ለማጭበርበር ዕድል መፍጠሩ አልቀረም።

በአጠቃላይ፤ መጽሐፉ ለሴቶች ሙሉ ሰው መሆን የሚታገል መጽሐፍ ነው። ከሰፈር እስከ ጠፈር ያሉ ልማዶችን ከሳይንሳዊ እውነታው ጋር እያመሳከረ የሚያብራራው በሴቶች ላይ የተሠራውን ግፍ ለማሳየት ነው። ጠንካራና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ የአገራችንን ሴቶች ታሪክ ፈልፍሎ በማምጣት ሌሎች ሴቶች እንዲፈጠሩ አድርጓል። እንዲያውም ይህኛው ምዕራፍ (ምዕራፍ 4 የአገራችን ብርቱ ሴቶች በጨረፍታ) የሴቶች ጉዳይ ላይ የሚሰሩ አካላት ብዙ ነገር ሊጠቀሙበት የሚገባ ሰነድ ነው።

በመጨረሻም እናቶችን ካሉባቸው ችግሮች(በልማዳዊ አመለካከት) ለማውጣት ምን መደረግ እንዳለበት የመፍትሔ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል።

መጽሐፉን መግዛትና ማንበብ፤ አንድም እናትን መርዳት ነው፤ ሁለትም ዓለምን ማወቅ ነው።

መማራቸው ከጠቀመን ሰዎች አንዱ ዶክተር ይሁኔ አየለ ናቸውና ያሳቡት ይሳካ እንላለን!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ትኩረት ከልመና ጎን ለጎን ራሳቸውን ለሚደጉሙት

**ሰላማዊት ውቤ**

‹‹የሚደግፈኝ ልጅም ሆነ ዘመድ የለኝም።የምተዳደረው በልመና ነው።ቢሆንም በልመና ባገኘኋት ጥቂት ሳንቲም ጥጥ ገዝቼ እየፈተልኩ ልቃቂት በመሸጥ ኑሮዬን እደጉማለሁ›› ይሄንን የነገሩን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አምስተኛ በር መታጠፊያ ላይ በሚገኘው ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን ደጃፍ ያገኘናቸው እናት ወይዘሮ ማስተዋል ቁምልኝ ናቸው።ብዙ ልቃቂት ሲሸጡ አልፎ አልፎ ጋቢ በማሰራት ዳጎስ ባለ ብር ሸጠው ይጠቀማሉ።በማህበር የሚያደራጃቸው ቢያገኙ በጥጥ ሥራው ለዘለቄታው ተሰማርተው ከልመና መውጣትም ይፈልጋሉ።

አሁን ላይ እኚህ እናት ብቻ ሳይሆኑ በርካታ ሴቶች ከልመና ጎን ለጎን የተለያዩ የእጅ ሥራዎችን ሲሰሩ መታየታቸው እየተለመደ መጥቷል። ብዙዎቹ ሴቶች እንደነገሩን ተግባሩን የሚያከናውኑት በልመና ቁጭ ሲሉ የሚያጠፉትን ረጅም ጊዜ ለመጠቀም ብቻ ሳይሆን በየቀኑ በልመና የሚያገኙትን ትንሽ ሳንቲም በመደጎም የዕለት ጉርሳቸውን ለመሸፈንም ነው።

በዚሁ በስድስት ኪሎ እቴጌ መነን የሴቶች አዳሪ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት መሶብና ሌሎች የስንደዶ ስፌት ሥራዎችን ሲሰሩ ያገኘናቸው ሌላዋ እናት ወይዘሮ ሩቅያ አሰፋ አምስት ልጆቻቸውን የሚያስተዳድሩት ከልመናው ጎን ለጎን ይሄን የስፌት ሥራ እየሰሩ መሆኑን ይናገራሉ። ልጆቻቸው ለምግብ እንጂ ለሥራ ስላልደረሱ ለመንገደኛም እየሸጡ ገቢ ያገኛሉ።የዕለት ጉርሳቸውን የሚሸፍኑትና የሚደጉሙት በዚሁ ገቢ ነው።የስፌት ግብዓቱን ከልመና በሚያገኙት ገንዘብ ነው የሚሸምቱት። ሆኖም አንደንዴ አንድ ብር ሁለት ብር እየተባለ የሚጠራቀመው የልመና ሳንቲም አልሞላ ሲልና ከሥር ከሥር ለልጆች ዳቦ መግዣ ሲወጣ ቀኑን በሙሉ ጊዚያቸውን ያለስራ የሚያሳልፉበት ጊዜ አለ ። በመሆኑም በቋሚነት የሚያደራጅና በሙያው እንዲሰማሩ የሚያደርጋቸው አካል ቢያገኙ የሰው ፊት ከሚያሳየውና ከሚያፀይፈው ልመና እወጣለሁ ብለው ያስባሉ።

የሰላሳ ዓመቷ ወይዘሮ ዘርትሁን መለሰ ከደራ ከመጣች ዓመታት ማስቆጠሯን ትናገራለች። የሶስት ልጆችም እናት ናት። ልጆቿን ለማሳደግ ስትል ለዓመታትም በልመና ሥራ ተሰማርታ ቆይታለች። በዚህ ወቅት ማንነታቸውን ማታውቀው ሰዎች የምትለምንበት ቦታ መጥተው ከልመናው ጎን ለጎን ያላትን የስፌት፤ የዳንቴልና ሌሎች የእጅ ሥራ ሙያዎች ተጠቅማ ኑሮዋን እንድትደጉም ግንዛቤ ፈጠሩላት።ሁለት ሦስቴም ስንደዶና የዳንቴል ክር እየገዙ ሰጧት።በስንደዶው ይሄን ከመከሯት ለአንዷ የመኪና መቀመጫ ሰፌድ በመሥራት ነው ለመጀመርያ ጊዜወደ ሥራው የገባችው።መሶብ ወርቅ፤መሶብና የዳንቴል ያልጋ ልብሶችና መሸፈኛዎች በመሥራት ደህና ገቢ አገኘች።ይሄን ያዩትና ግንዛቤ ፈጥረውላት የነበሩት ሰዎች ለ15 ቀን ስልጠና እንድትወስድ አደረጓት።ስልጠናው ከዳንቴልና ከክር፤ እንዲሁም ከስንደዶ የተለያዩ የፕላስቲክ ከረጢቶችን በመተካት አካባቢን ሳይበክሉ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቦርሳዎችና ስፌቶች ማምረት የሚያስችል ነበር።አሁን ላይ በእጅ ሥራው ሙሉ በሙሉ ከልመና መውጣት ችላለች።ሽሮ ሜዳ አካባቢ እንዲሁም የንግስ በዓላት በሚሆኑበት ጊዜ ንግሱ በሚከናወንበት ሥፍራ ተገኝታ ምርቶቿን በመሸጥም ትተዳደራለች።አንድ ቦርሳ እስከ 500 ብር ትሸጣለች።በተለይ እንደ ጥምቀት ባሉት በዓላት የውጭ አገር ቱሪስቶች በብዛት ይገዟታል።ልጆቿንም ትምህርት ቤት ማስገባት ችላለች።ከማይመችና በጥገኝነት ትኖርበት ከነበረው የግለሰብ ቤት ወጥታ የራሷን ምቹ ቤት መከራየት ችላለች።ዘርትሁን ‹‹ይሄ አንዲት በልመና ተሰማርታ ለነበረች ሴት ቀላል ለውጥ አይደለም፡ ››ትላለች።አክላም ሌሎችም በተለይም አቅምና ጤና ያላቸው ሰዎች በሙያው ቢሰማሩ በቀላሉ ከልመና መውጣት እንደሚችሉም ተሞክሯን ማሳያ አድርጋ ትመክራለች።

> **አሁን ላይ እኝህ እናት ብቻ ሳይሆኑ በርካታ ሴቶች ከልመና ጎን ለጎን የተለያዩ የእጅ ሥራዎችን ሲሰሩ መታየታቸው እየተለመደ መጥቷል።**

የ‹‹ገላዬ ደያስ ሀንድ ክራፍት›› ድርጅት መስራችና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ገላዬ ደያስ ብዙ ሴቶችንና እናቶችን ከልመና የሚያወጣ የተቀደሰ ተግባር እንደ አገርም ሆነ አብዝቶ የልመና ተግባር በሚፈፀምባት አዲስ አበባ በመዟዟር ግንዛቤ እየፈጠሩ የጀመሩ ናቸው። ወይዘሮዋ ከ10 ዓመት በላይ በበርካታ ማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎች ተሰማርተው ሲሰሩ የቆዩ ናቸው። ሥራውን ከ2002 ጀምሮ እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ በትጋት ሲሰሩት ቆይተዋል።እንደ አገር ከአንድ ሺህ በላይ ሴቶችና እናቶችን ግንዛቤ በመፍጠር በተለያዩ የእጅ ስራዎች አሰልጥነዋል።ከነዚህ አብዛኞቹ ከተለያዩ ክልሎች ፈልሰው ከነልጆቻቸው ወደ አዲስ አበባ የመጡና በጉለሌ፤በአዲስ ከተማ፤እንዲሁም በልደታ ክፍለ ከተሞች በልመና ሥራ የተሰማሩ ነበሩ።ሴተኛ አዳሪ ሆነው ጎዳና የወጡና በልመና ስራ የተሰማሩም ይገኙበታል።አሁን ላይ ካሰለጠኗቸው ሴቶችና እናቶች ከግማሽ በላዩ በጥጥ ፈትል፤ በሹራብ፤ ኮፊያ፤ በቦርሳ፤ በስንደዶ ስፌትና በሌሎች የተለያዩ የእጅ ሥራዎች በመሰማራት የራሳቸውንና የልጆቻቸውን የዕለት ጉርስ ከመሸፈን አልፈው ከልመና መላቀቅ ችለዋል። በሽሮ ሜዳና በተለያዩ ሥፍራዎች ምርቶቻቸውን በመሸጥ በሚያገኙት ገቢም ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ከመላክ አልፈው የተሻለ ሕይወት እየመሩ ይገኛሉ።አሁን ላይም ይሄ ተሞክሮ በተለያየ መንገድ በመስፋቱ እናቶችና ሴቶች ከልመና ጎን ለጎን የእጅ ሥራ ሙያውን ሲያከናውኑት ይታያሉ።

ሥራው ለግለሰቦቹ ብቻ ሳይሆን ለአገርም ዘርፈ ብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች አሉት። በተለይ የሚያመርቱት ቦርሳ ለረጅም ዓመት ሳይበላሽ በመቆየቱ በምርታማነት ላይና በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድረውን የፕላስቲክ ከረጢትን የሚተካ ነው።ሆኖም እናቶችን የዕለት ጉርስ፤ መጠለያ የሌላቸው፤ ልጆቻቸውን ማስተማር የማይችሉና ሌሎች ውስብስብና ዘርፈ ብዙ ችግሮች ስላሉባቸው እሳቸው ከዚህ ቀደም በፈጠሩት ግንዛቤ ብቻ በቀላሉ ከልመና ይወጣሉ ብለው አይጠብቁም። በእርግጥ በእጅ ሥራው መስክ ሳይሆን በሌሎች መስኮች በመንግስት ደረጃ እናቶችና ሴቶችን ለመደገፍ የሚሰሩ ሥራዎች ቢኖሩም በአብዛኛው እነዚህን በልመና የተሰማሩትን አያካትትም። በመሆኑም ከመንግስት ጋር ሥራውን እናቶቹና ሴቶቹ ዘላቂ ለውጥ በሚያመጡበት ሁኔታ በቅንጅት ለማከናወን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፤ለከተማዋ ሴቶችና ህፃናት ቢሮ እንዲሁም ለአካባቢ ጥበቃ አቅርበው ነበር፡ ነገር ግን እስከ አሁን ምላሽ አላገኙም፡፤ እኛም ከልመና ባሻገር ወይዘሮ ገላዬ በፈጠሩላቸው ግንዛቤ ራሳቸውን የሚደጉሙት በቅንጅት ይታገዙ መልዕክታችን ነው።

# ዓለም አቀፍ

## ጆ ባይደን የአሜሪካን ምርጥ የጦር ጄቶች ለዩክሬን አልሰጥም አሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን እጅግ ዘመናዊ ናቸው የሚባሉትን አሜሪካ ሰራሽ ኤፍ-16 የጦር ጄቶችን ለዩክሬን አሳልፈው እንደማይሰጡ ገለጹ።

ጆ ባይደን ትናንት "ኤፍ-16 ጄቶች ለዩክሬን ይሰጣሉ ወይ?" በሚል ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ "በፍጹም" የሚል አጭር መልስ ሰጥተዋል።

ጆ ባይደን ይህን ከማለታቸው አንድ ቀን ቀደም ብሎ ጀርመንም በተመሳሳይ ተዋጊ ጄቶቿን ለዩክሬን አሳልፋ እንደማትሰጥ ይፋ አድርጋ ነበር።

ዩክሬን በበኩሏ የአየር ክልሏ በሩሲያ በተደጋጋሚ እየተጣሰ ስለሆነ ያን ለመቋቋም የግድ ዘመናዊ ተዋጊ ጄቶች ያስፈልጉኛል እያለች ነው።

"ኤፍ-16" ተዋጊ ጄቶች በዓለም ላይ አስተማማኝ ከሚባሉ የአየር ላይ ውጊያ ጄቶች የሚመደቡ ሲሆን፣ እነዚህኑ ጄቶች ከአሜሪካ ባሻገር ቤልጂየም እና ፓኪስታን ታጥቀዋቸዋል።

ዩክሬን አሁን እየተጠቀመችባቸው ያሉት ብዙዎቹ የጦር ጄቶች በሶቭየት ኅብረት ጊዜ የተመረቱ ናቸው።

እነዚህ ያረጁ ያፈጁ ጄቶች አገልግሎት ላይ ይውሉ የነበረው ዩክሬን ነጻነቷን ከማወጇ በፊት ነው።

በዚህም የተነሳ ዩክሬን ሩሲያን በአየር ልትቋቋማት ተስኗታል።

ዩክሬን ምዕራባውያን ዘመናዊ ጄቶችን ሊሰጡኝ ይገባል ስትል ቀን ተሌት ብትወተውትም ጆ ባይደን ይህን ልመና ጆሮ ዳባ ልበስ ብለውታል።

ፕሬዝዳንቱ ከጄቶች በሻገር ግን በሌሎች ወታደራዊ ዘርፎች ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ለዩክሬን እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል።

አሜሪካ ባለፈው ሳምንት ለዩክሬን 'ኤብራምስ' የሚባሉ እጅግ ዘመናዊ 31 የጦር ታንኮችን እንደምትሰጥ ቃል ገብታ እንደነበረ ይታወሳል።



**'ኤፍ 16' ዓለም ላይ አሉ ከሚባሉ የጦር ጄቶች አንዱ ነው**

ይሁንና እነዚህ ታንኮች ዩክሬን ጦር ሰፈር ለመድረስ ቢያንስ አንድ ዓመት ይወስድባቸዋል።

የአሜሪካንን እርዳታ ተከትሎ ጀርመን እና ዩናይትድ ኪንደግምም ተመሳሳይ ወታደራዊ ድጋፍ ለመስጠት ቃል ገብተዋል።

ጀርመን ለዩክሬን እሰጥሻለሁ ያለቻት 'ሊዮፓርድ-2' የሚባሉትን ዘመናዊ ታንኮች ነው።

የጀርመን መራሔ መንግሥት ኦላፍ ሾልዝ ለአንድ የአገሬው ጋዜጣ እንዳሉት "ከሊዮፓርድ ታንኮች በተጨማሪ የአየር ጄቶችን ወደ ዩክሬን የመላኩ ነገር የማይመስል ነው።"

ሾልዝ ጨምረው እንዳስረዱት ተዋጊ ጄቶችን ለዩክሬን መስጠት ሁኔታዎችን ይበልጥ ማባባስ ይሆናል።

ሞስኮ ምዕራባውያን ዩክሬንን በመጠቀም የራሳቸውን ጦርነት ከሩሲያ ጋር እያደረጉ ነው ስትል ትከሳለች።

የፈረንሳዩ ኢማኑኤል ማክሮን ለዩክሬን በምንሰጠው ድጋፍ "ይህን አናደርግም የምንልበት ሁኔታ አይኖርም" ብለዋል።

ይሁንና ለዩክሬን በሚደረጉ ድጋፎች ውስጥ ጦርነቱን ማቀጣጠል እንዳይኖር ጥንቃቄን ይሻል፤ ዩክሬን ራሷን የመከላከል አቅምንም ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል ብለዋል።

ሌሎች እንደ ኔዘርላንድስ ያሉ የአውሮፓ ኅብረት አባል አገራት ተዋጊ ጄቶችን ወደ ኪዬቭ ለመላክ ገና ውሳኔ ላይ አልደረሱም።



በፓኪስታኑ የመስጊድ ውስጥ የቦምብ ፍንዳታ የሞቱት ሰዎች

## በፓኪስታኑ የመስጊድ ፍንዳታ የሞቱት ሰዎች ቁጥር ወደ 100 ከፍ አለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ፓኪስታን ውስጥ በሰሜን የአገሪቱ ክፍል በሰዎች በተሞላ አንድ መስጊድ ውስጥ ትናንት በደረሰ የቦምብ ፍንዳታ የሞቱት ሰዎች ቁጥር ቢያንስ 100 መድረሱ ተነገረ፡፡ ሌሎች 150 የሚደርሱ ደግሞ መቁሰላቸው ተገልጿል፡፡

ኺበር ፓኽቱንኽ ክፍለ ግዛት ዋና ከተማ በሆነችው ማዕከላዊ ፔሻዋር በደረሰው ፍንዳታ፣ ተጎጂ የሆኑ ሰዎችን ከህንጻው ፍርስራሾች ውስጥ የማፈላለጉ ሥራ መቀጠሉም ተነገሯል፡፡ እጅግ አደገኛ እንደነበር የተነገረለት ፍንዳታ የህጻንውን ጣሪያ ማፈራረሱ ተመልክቷል፡፡

ጥቃቱ ጉዳት ከደረሰባቸው መካከል አብዛኞቹ የክፍለ ግዛቲቱ ፖሊሶች መሆናቸው ሲገልጽ፣ አደጋው የደረሰበት መስጊድ፣ በደህንነትና የመንግሥት ባለሥልጣናት የሚዘወትር መሆኑም ተነግሯል።

እስካሁን ለፍንዳታው ኃላፊነቱን የወሰደ ወገን አለመኖሩ የተገለጸ ሲሆን ፤የፓኪስታኑ ታሊባን ለአሜሪካ ድምጽ የላከውን ጨምሮ ባወጣው መግለጫ በሰኞው ፍንዳታ እጁ እንደሌለበት አስታውቋል፡፡